# ማ ው ጫ

ገፅ

ከአንባቢያን ............................................................... 2
የዝግጅት ክፍል ማስታወሻ .............................................. 4
ርዕሰ አንቀፅ ............................................................... 5
ኢኮኖሚ ..................................................................
የኮንስትራክሽን ዘርፍና የልማት ትግላችን...................................... 7
ፖለቲካ ..................................................................
ስትራተጅያዊ ትርምስ በተቃዋሚዎች ጎራ...................................... 18
ማህበራዊ ...............................................................
የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና ................................................ 33
ዓለም አቀፍ .............................................................
የፀረ ሽብርተኝነት ትግልና ........................................................ 45
ከኢህአዴግ አምባ .......................................................
ለመልካም አስተዳደር እመርታ .................................................. 63
ከዚህም ከዚያም ........................................................
የማይበገር የንባብ... ............................................................ 72

## አዲስ ራዕይ

**በየሁለት ወሩ፣** በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጀ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ማብራሪያና ትንታኔ ይዛ የምትቀርብ የኢህአዴግ የትንታኔ መፅሄት ነች።

1ኛ ዓመት ቅፅ 1 ቁጥር 003 ሃምሌ - ነሃሴ 1998

አዘጋጅ፡- የኢህአዴግ ህዝብ ግንኙነት ክፍል

አሳታሚ፡- ኢህአዴግ

አድራሻ፡- ስልክ 011 - 123 - 43 - 01

የመ.ሳ.ቁጥር፡- 80007

ፋክስ፡- 011 - 123 - 43 - 00/122 - 12 - 34

*E-mail: abyot.np@ethionet.et*





# ከአንባቢያን

## የስኬት መሳሪያ

አዲስ ራዕይ መፅሄት የምትጥምና አቅም የምትገነባ ሆና አግኝቻታለሁ። የኢህአዴግ አባላትን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም አንባቢያን አመለካከትና አስተሳሰብ የምታንፅ፣ ወርቃማ ይዘት ያላት መፅሄት ናት። በአጠቃላይ በሀገራችን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና አለማቀፋዊ ጉዳዮች ላይ የምታቀርበው ትንታኔ የተስተካከለ አመለካከት ለመያዝና የለውጥ መሳሪያ ሆኖ ለማገልገል የምታስችል ናት።

በቀጣይ በመፅሄቷ ዙሪያ በስፋት ውይይት እየተደረገ ሲሄድና የተስተካከለ አመለካከት ስንይዝ የጠሩ ግቦች እንነድፋለን። የጠራ ራዕይም ይኖረናል። ውጤታማ የተባሉ ስልቶችንና ዘዴዎችን ስንከተልም ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ለውጥ ስናመጣና ውጤት ባስመዘገብን ቁጥር ህዝባችን ይጠቀማል። ህዝባችን የለውጡ ተጠቃሚ በሆነ ቁጥር ከጎናችን ይቆማል። ህዝባችን ከጎናችን በቆመ ቁጥር የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲ ግቦቻችን እውን ይሆናሉ። ለዚህ ደግሞ አዲስ ራዕይ መፅሄት የስኬት መሳሪያ ሆና እንደምታገለግል ጥርጥር የለውም።

አለባቸው አማረ

ሰሜን ሸዋ (ሰላድንጋይ)

## የትግል ስንቅ

አዲስ ራዕይ ጥሩ ነች ማለት ይቻላል። አንገብጋቢ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የምታቀርበው መረጃና ትንታኔ፣ በኢህአዴግ አቋሞች ላይ ግልፅ የሆነ መልዕክት የምታስተላልፍ መሆኗም ተወዳጅ ያደርጋታል። እንደ አንድ የትግል ስንቅ ልትታይ የምትችል ነች።

በተረፈ ሁለት ነገሮች መስተካከል አለባቸው። አንደኛው የፊደል ስህተት መፈጠሩ ☞

# በርቱ

ቁጥር 2 አዲስ ራዕይ መፅሄትን ከሰው እጅ አይቼ ነው የገዛኋት፡፡ በውስጧ በርካታ ቁም ነገሮች አካታለች፡፡ ትንታኔዎቹ በመረጃ የተደገፉ መሆናቸው በሳል መፅሄት ያደርጋታል፡፡

መፅሄቷ ተጀምራ የምታቆም እንዳትሆን ማድረግ ይገባችኋል፡፡ በተረፈ በርቱ!

መኮንን ከበደ (ነቀምት)

# የተሻለች ነች

አዲስ ራዕይ ቁጥር 2፣ ከመጀመሪያው እትም የተሻለች ነች፡፡ መጠኗም ለአያያዝ የተመቸ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የሻዕቢያ የአፍሪካ ቀንድ የትርምስ ስትራቴጂ እና በቴሌኮም የልማት ዘርፍ የቀረቡት ትንታኔዎች አርክተውኛል፡፡

ሀይሉ (ከሞጣ)

# ትንታኔዎቹ አስፈላጊ ናቸው

አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ላይ የቀረቡ ትንታኔዎች ከቁጥር አንድ የጠነከሩ ናቸው፡፡ ትንታኔዎቹ አስፈላጊና የኢህአዴግን አቋም በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

የሻዕቢያ የትርምስ ስትራቴጂ፣ የኢህአዴግ ጉባኤ ሂደቶችና ዋና ዋና መርሆዎች ምን እንደነበሩ የሚያሳየን ፅሁፍ ጭምር ወድጄዋለሁ፡፡ ጊዜያችሁን ጠብቃችሁ መምጣቱን ግን አትርሱት፡፡

ሀብቴ ከበደ (ከሚዛን)

# «ቁም ነገር አዘል ነች»

አዲስ ራዕይ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? እኔ ደህና ነኝ፡፡ በመቀጠል እኔ አዲስ ተሳታፊ ነኝ፡፡ ሊያደርገኝም የቻለበት ምክንያት አዲስ ራዕይ መፅሄት ቁም ነገር አዘል ስለሆነች ነው፡፡ ይህም ማለት የኢህአዴግን ትክክለኛ አቅጣጫ የያዘችና ኢህአዴግ የሚዳስሳቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና አለም አቀፋዊ ጉዳዮች ዙሪያ የምታብራራ ስለሆነች እኔም ወደፊት የማልለያችሁና ተሳታፊያችሁ እንደምሆን እርግጠኛ





# የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ

አዲስ ራዕይ ቅፅ 1 ቁጥር 2 ታትማ ወደ አንባቢያን እጅ ከገባች ጀምሮ በርከት ያሉ አስተያየቶች ደርሰውናል፡፡ አስተያየቶቹ በስልክ፣ በፋክስ፣ በደብዳቤና በኢ-ሜይል የመጡ ናቸው፡፡

ከተለያዩ አንባቢያን የደረሱን እነዚህ አስተያየቶች በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ረድፍ የሚታዩ አስተያየቶች ኢህአዴግ አቋሞቹን በየጊዜው ግልፅ የሚያደርግበትና በሰፊ መረጃ የተደገፈ ትንታኔ ይዞ መቅረብ መቻሉ ተገቢ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህ ጎራ ውስጥ ከሚሰለፉ አስተያየቶቻችሁ መካከል መፅሄቷ ለተማሩ የኢህአዴግ አባላት ብቻ ሳይሆን አጋር ለሆኑ የግንባሩ ወዳጆችና ደጋፊዎች በስፋት የማዳረሱ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ትክክለኛ ሃሳብ ነው፤ በሁሉም አካባቢ ተግባራዊ መሆን ይገባዋል፡፡

በሁለተኛው ጎራ የሚመደቡ የአንባቢያን አስተያየቶች ደግሞ በመፅሄቷ ላይ ተጨማሪ ትንታኔዎችና አዳዲስ አምዶች ቢከፈቱ የሚሉ ይገኙበታል፡፡ አዳዲስ አምዶች ቢከፈቱ የሚሉ አንባቢያን ከጠቆሟቸው አምዶች መካከል በታሪክ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ መፅሀፍት የሚገመገሙበትና፣ የአጋር ድርጅቶችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ አምዶች ቢከፈቱ ያሏቸው ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ጠቃሚ ሃሳቦች ናቸው፣ ወደፊት እናጠናቸዋለን፡፡ ሁሉም አንባቢያን ለሰጣችሁን አስተያየቶች ምስጋናችን የላቀ ነው፡፡ ሁሉንም ማምጣት አስቸጋሪ ስለሆነ በደብዳቤ ለደረሱን የተወሰኑትን በከአንባቢያን አምድ አውጥተናቸዋል፡፡ ተሳትፏችሁን እናደንቃለን፡፡ መፅሄቷ በናንተ ተሳትፎ የበለጠ ጎልታ እንደምትወጣ አንጠራጠርም፡፡ ነገር ግን አሁንም ቢሆን በምናቀርበው ትንታኔ ላይም ይሁን ከሌላ አቅጣጫ በታያችሁ ሃሳቦች ላይ ተመስርታችሁ ሰፋ ያለ ትንታኔ ያለው ፅሁፍ በመላክ በኩል ተሳትፏችሁ አነስተኛ ነው፡፡ በዚህ አቅጣጫ ጠንካራ ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡ መድረኩ ለሁሉም ክፍት ነውና!!

በቁጥር 3 እትማችን እንደተለመደው ወቅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ አቅርበናል፡፡ የሀገራችን ተቃዋሚዎች ከምርጫ በፊትና ማግስት ምን ሁኔታ ውስጥ ናቸው? በውስጣቸው የተፈጠረው ስትራቴጂያዊ ትርምስ ምንጩ ምንድነው? ኢህአዴግ በተቃዋሚዎች መንደር ያለውን ትርምስ እንዴት ይመለከተዋል? አንዱ የትንታኔ ፅሁፍ እዚህ ላይ አትኩሯል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፍ አስገራሚ በሆነ ፍጥነት እያደገ ነው፡፡ በርካታ ዜጎች የስራ እድል አግኝተዋል- ዘርፉ በመስፋፋቱ፡፡ የዘርፉ እድገት መሰረቱ ምንድነው? በዘርፉ እየታዩ ያሉ ችግሮች ምንድናቸው? እንዴትስ ይፈታሉ? ሌላኛው በዚህ እትም የቀረበ ትንታኔ ነው፡፡

በሞቃዲሾ ትርምስ ነግሷል፡፡ በሻዕቢያ የሚደገፈውና በአለም አቀፍ አሸባሪ ቡድን መሃንዲስነት ሞቃዲሾ ላይ ሰሞኑን ገኖ የወጣውና ራሱን የሸሪአ ፍርድ ቤቶች ብሎ የጠራው ቡድን ማነው? በሶማሊያ የሚታየው ትርምስ ምንጩ ምንድነው? በሶማሊያ የሚገኙ የተለያዩ ቡድኖችና ሃይሎች አሰላለፍ ምን ይመስላል? ትርምሱ በኢትዮጵያ ላይ ምን የሚፈጥረው ተፅዕኖ አለ? በጉዳዩ ላይ ምን አይነት አቅጣጫ ነው የምንከተለው? ... እነዚህንና የመሳሰሉትን ርዕሰ ጉዳዮች የዳሰሰ ትንታኔም የዚህ እትም አካል ነው፡፡

ሌሎች ጠቃሚና ወቅታዊ ትንታኔዎች ተካተው ቀርበዋል፡፡ ሁሉንም ፅሁፎች በሚገባ ማንበብና በየአደረጃጀቱ በጥሞና መወያየት የናንተ ድርሻ ነው፡፡ የምትልኩልን አስተያየቶች መናሻ አድርገን ደግሞ ቀጣዩን እትም የበለጠ አዳብረን ማቅረብ ደግሞ የኛ ድርሻ ነው፡፡ ለእናንተ ግን ተጨማሪ ድርሻ መስጠት ፈልገናል፡፡ መፅሄቷን በየአካባቢያችን ማስተዋወቅ፣ አዳዲስ ደምበኞችን ማፍራት፣ መፅሄቷ በአባላት ብቻ ሳትወሰን በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ተነባቢ እንድትሆን ማብቃት፡፡ ስለዚህ ፃፉልን፡፡ መልካም ንባብ፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጉባኤያችን ስኬት በአባላት የነቃ ተሳትፎ ላይ ይመሰረታል!

ስድሰተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችንን ለማካሄድ የተጀመረው ዝግጅት እየተጠናቀቀ እነሆ በጉባኤው ዋዜማ ላይ እንገኛለን፡፡ ስድስተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በመልካም አስተዳደር እመርታ በማስመዝገብና በልማቱ መስክ የተገኘውን እድገት ቀጣይ የማድረግ ግብ ያለውና ድርጅታችንን ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግር የሚጠበቅ ነው፡፡

5ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ያፀደቃቸውን እቅዶችና የቀየሳቸውን አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ ባለፉት ሶስት አመታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ድሎች አስመዝግ-በናል፡፡ በአገራችን ታሪክ ለሶስት ተከታታይ አመታት በአማካይ ከ9.5% በላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ለአራተኛ ጊዜ ተመሳሳይ እድገት ማረጋገጥ እንዲቻልም በሁሉም መስክ ርብርብ በመደረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከእድገቱ ሁሉም የአገራችን ህዝቦች በተለይም ደግሞ ለልማትና እድገት ባእድ ሆነው የኖሩት አርሶአደሮችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ጥቂት በማይባሉ ቦታዎች በአስር ሺዎች ብር የሚቆጠር አመታዊ ገቢ ማግኘት የጀመሩ አርሶአደሮች ማየት ጀምረናል፡፡ ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ህዝባችን  ቁጥርም እየቀነሰ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የልማት ስትራተጅና ፖሊሲዎቻችንን ትክክለኛነት በገሃድ ይመሰክራል፡፡

ጠባብነትና ትምክህት አንድ አካል አንድ አምሳል እስኪመስሉ ድረስ ተጣምረው በአገራችን የተጀመረውን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ርብርብ ለማደናቀፍ ያደረጉት ጥረት፣ ያገኘውን ጥቅም ላለማስነጠቅ ከኢህአዴግና ከመንግስት ጎን ተሰልፎ  በተንቀሳቀሰው የህዝባችን ትግል ከሽፎ የተጀመረው መድብለ ፓርቲ ስርዓት ቀና መንገድ ይዞ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ሌላው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስትራተጅና ፖሊሲዎቻችን ትክክለኛነት ማረጋገጫ ነው፡፡

በሌላም በኩል ድርጅታችን ኢህአዴግ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ውስጠ ድርጅት አቅሙ በተጠናከረበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በታታሪነታቸውና በስነምግባራቸው

☞





ግንባር ቀደም የሆኑ አርሶአደሮች፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም የተለያዩ ባለሙያዎችና ወጣት ምሁራን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኘሮግራማችንን ተቀብለው ለተግባራዊነቱ ለመታገል የድርጅታችን አባላት ሆነዋል፡፡ እኒህ አባላት ከሃያ ሺ በላይ መሰረታዊ ድርጅቶችና ከ150 ሺ በላይ በሆኑ ህዋሳት ተደራጅተው ድርጅታዊ ተልእኮአቸውን ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከወዲሁም እጅግ የሚያበረታታ ውጤት በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአራቱ ክልሎች ከሚገኙት አርሶአደር አባሎቻችን ውስጥ ከ90% በላይ የሚሆኑት በክረምቱ የግብርና ልማት ላይ በግንባር ቀደምነት መሳተፍ ጀምረዋል፡፡

በእንደዚህ አይነት ድሎች ታጅቦ የሚካሄደው የኢህአዴግ 6ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ የአገራችንን ቀጣይ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አቅጣጫዎች በሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮች ዙሪያ አመራር ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከጉባኤው ግብ እንደምንረዳው ፈጣንና ህዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማት ለማረጋገጥ የሚደረገው ርብርብ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ መስክ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ሰፊ ጥረት ይደረጋል፡፡

6ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ካለፉት ጉባኤዎቻችን በተለየ ሁኔታ አጋር ድርጅቶች፣ ደጋፊ ምሁራንና ልማታዊ ባለሃብቶች፣ እንዲሁም የውጭ አገር ፓርቲዎች የሚታደሙበትና ሰፋ ያለ ተሳትፎ የሚደረግበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከምንገኝበት ድርጅታዊ ሁኔታ አኳያም በቅርብ ድርጅታችንን የተቀላቀሉ አዳዲስ አባላት በውክልና የሚሳተፉበት ሁኔታ እንደሚኖር ይገመታል፤ ከዚህ አኳያም በየብሔራዊ ድርጅቱ የሚካሄደው የወኪሎች ምርጫ አዳዲስ አባላትን ግምት ውስጥ በሚያስገባ አኳኋን እንደሚተገበር ይጠበቃል፡፡

በጉባኤ ዋዜማ ላይ እንደመገኘታችን ሁሉ የጉባኤያችን ስኬት በአባላት የነቃ ተሳትፎ ላይ እንደሚመሰረት የተገነዘበ ብቁ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባናል፡፡  የድርጅታችን አባላት ጉባኤያችን እንዲሳካ ብቃትና ጥራት ያላቸውን ወኪሎች ከመምረጥ አንስቶ በቅድመ ጉባኤ መድረኮች በንቃት መሳተፍ፣ የቅድመ ጉባኤ ስራችንን አጠናቀን ወደ ጉባኤ መግባት ብቻ ሳይሆን በጉባኤያችን የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በድህረ ጉባኤ መድረክ ተግባራዊ ለማድረግ ከወዲሁ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

የኢህአዴግ 6ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ለመልካም አስተዳደር እመርታ!

## ኢኮኖሚ

# የኮንስትራክሽን ዘርፍና የልማት ትግላችን ታላቅ የእድገት ውጤትና ምንጭ የሆነ ዘርፍ

ከነጋ ደምሰው

የኮንስትራክሽን ዘርፍ በታዳጊ ኢኮኖሚዎች እንደታየው ታላቅ የእድገት ምንጭና ውጤት የሆነ ዘርፍ ነው፡፡ የህዝቡ ኑሮ እየተሻሻለ ሲሄድ በአዲሱ ትውልድ ከሚሰሩ ቤቶች በተጨማሪ ሌላውም ቤት ያልነበረው ቤት ለመስራት የነበረውም ለማሻሻል ሰፊ የኮንስትራክሽን ስራ የሚካሄድበት ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ እድገት ሲመጣ መንገዶች፣ የሃይል ማመንጫ ጣቢያዎችና የመሳሰሉት የመሰረተ ልማት ስራዎች በሰፊው ስለሚገነቡ ከፍተኛ የኮንስትራክሽን እን-ቅስቃሴ ይኖራል፡፡ ልማት ሲፋጠን የፋብሪካዎች፣ የንግድ ቤቶች ... ወዘተ ግንባታ ይፋጠንና የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ እድገት ያስመዘግባል፡፡ በሌላ አነጋገር የኮንስትራክሽን ዘርፍ የአንድ ታዳጊ ኢኮኖሚ ጤንነትና እድገት የሚለካበት ቴርሞ ሜትር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከኮንስትራክሽን ስራ ዉጪ የሚካሄድ ልማት የለምና ኢኮኖሚው በፍጥነት በሚያድግበት ወቅት አንጻ ተጨባጭ መለኪያው የኮንስትራክሽን ዘርፍ እድገት ይሆናል፡፡ ኮንስትራክሽን የእድገትና የልማት ውጤት ነው የሚባልበት ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

ኮንስትራክሽን የልማት ውጤት ብቻም ሳይሆን የልማት ምንጭም ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ስራ ለማካሄድ ሲሚንቶ ብረታ ብረትና ሌሎች የግንባታ እቃዎችን ይጠይቃል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሲጠናከር የኮንስትራክሽን እቃዎች የማምረት ስራም አብሮ ስለሚያድግ የእድገት ምንጭ ይሆናል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሲያድግ ብዙውን ጊዜ አብረው የሚሄዱ የቤት ቁሳቁሶች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ አልጋ ወዘተ) ፍላጎትም አብሮ ያድግና እነዚህን የሚያመርቱ ተቋማት በከፍተኛ ፍጥነት እንዲያድጉ ምክንያት ይሆናል፡፡ የእድገት የመጨረሻ መለኪያው የህዝቡ ኑሮ መሻሻል ነው፡፡ የህዝቡ ኑሮ መሻሻል ደግሞ መጀመሪያ በምግብ ቀጥሎ በልብስ ቀጥሎም በመጠለያ አቅርቦት ይለካል፡፡ ኮንስትራክሽን የህዝቡ የመጠለያ ፍላጎት የሚረጋገጥበት ዘርፍ ስለሆነ ትልቅ የህዝብ ልማትና እድገት ምንጭ ነው ሊባል ይችላል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ የሰው ሃይል ለመቅጠር የሚችል ዘርፍ ነው፡፡ ለምሳሌ የቻይና የኮንስትራክሽን ዘርፍ

☞

ከ30 ሚሊዮን በላይ ሰራተኞች የቀጠረ መሆኑን ስናጤን ምን ያህል የስራ እድልን ሊፈጥር እንደሚችል መገንዘብ እንችላለን። ሰፊ የስራ እድል መፈጠሩ ራሱ ከፍተኛ የእድገት ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። ኮንስትራክሽን ከፍተኛ የእድገት ምንጭ የሚሆነውም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ነው።

ባለፉት ሶስት ዓመታት የአገራችን ኢኮኖሚ ተከታታይና ፈጣን እድገት በማሳየቱ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የበኩሉን ከፍተኛ ተጽእኖ በማሳረፍ ላይ ይገኛል። የህዝቡ ገቢ በተለይም በትርፍ አምራች አካባቢዎች ያለው አርሶ አደር ገቢ በመጨመሩ ገቢውን ጥቅም ላይ ለማዋል ቤት የመስራት ጉዳይ እንደ አንድ ትልቅ አማራጭ የሚታይበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል። በከተሞች ከፍተኛ የቤት እጥረት ያለ በመሆኑ ይህንን ችግር የመቅረፍ ከፍተኛ ግፊት ይታይል። ይህም ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከፍተኛ የመሰረተ ልማትና የማሕበራዊ ልማት ስራ እየተሰራ መሆኑ፣ ግብርና መር የልማት ስትራቴጂውን ተከትሎ የኢንዱስትሪ ልማትም በማፋጠን ላይ ስለሚገኝ የኮንስትራክሽን ዘርፍ በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድግበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

የኮንስትራክሽን ዘርፍ እያደገ ያለበትን ፍጥነት ለመገንዘብ የሲሚንቶን ሁኔታ ብቻ ማየት በቂ ሆኖ ይገኛል። በአገር ውስጥ ያሉት ጥቂት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ሲያመርቱ 1.5 ሚሊዮን ቶን አካባቢ ማምረት ይችላሉ። እስካለፈው ዓመት ድረስ የአገር ውስጥ የሲሚንቶ ፍላጎት ውሱን ስለነበረ ፋብሪካዎቹ ያመረቱትን በሙሉ መሸጥ ተስኗቸው ከማምረት አቅማቸው ውስጥ የተወሰነውን ብቻ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ነበር። ነገር ግን ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እድገት ጋር በተያያዘ በያዝነው ዓመት የሲሚንቶ ፍላጎት በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ የተነሳ ፋብሪካዎቹ የማምረት አቅማቸውን በሙሉ የተጠቀሙበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህም ሆኖ በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሲሚንቶ እጥረት ታይቷል። በሚቀጥለው ዓመት የሲሚንቶ ፍላጐታችን እስከ ሶስት ሚሊዮን ቶን እንደሚደርስ በመገመቱ 1.5 ሚሊዮን ቶን ያህል ሲሚንቶ ከውጭ ለማስገባት ዝግጅቱ ተጠናቋል። በአገራችን የሲሚንቶ ፍላጐት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሆኑን በመገንዘብ መንግስትና የግል ባለሃብቶች አዳዲስ ፋብሪካዎችን የማቋቋምና ነባሮቹን የማስፋፋት ስራ ላይ እየተረባረቡ ይገኛሉ። በመቋቋም ላይ ያሉት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከሁለት እስከ ሶስት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ የማምረት ስራ ሲጀምሩ በአገር አቀፍ የሚመረተው ሲሚንቶ

☞





በዓመት ከ6 ሚሊዮን ቶን የማያንስ እንደሚሆን ይገመታል።

የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ የስራ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ምክንያት ሰፋ ያለ የኮንስትራክሽን ስራ በሚከናወንባቸው እንደ አዲስ አበባ ባሉት ከተሞች የቀን ሰራተኞች ደሞዝ ከመጨመሩም ባሻገር በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ስራ በቀላሉ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተገኘው የስራ እድል ለመጠቀም ዝግጁ በመሆን ረገድ ከማንም በላይ ሴቶች ግንባር ቀደም በመሆናቸው (ዘርፉ በተለምዶ የሴቶች ዘርፍ ተብሎ የሚታወቅ ባይሆንም) በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች በዘርፉ ተሰማርተው ይገኛሉ። ስራ ፈላጊው ወጣት ወደ ዘርፉ በትጋት አለመግባቱ፣ ቢያንስ ሴቶች በገቡበት መጠን ሲገባ አለመታየቱ አሳሳቢ ጉዳይ ቢሆንም የኮንስትራክሽን ዘርፍ የከተማ ስራ አጥነትን በመቅረፍ ረገድ ዓይነተኛ መሳሪያ መሆኑን በተጨባጭ በማረጋገጥ ላይ ይገኛል።

## የኮንስትራክሽን ዘርፋችን እድሎችና ውሱንነት

እስካሁን በተግባር እየታየ እንዳለው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለከፍተኛ እድገት በር እየከፈተ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው እድገቱ የሲሚንቶ ፍላጐትን በመጨመር የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ በርከት ብለው እንዲቋቋሙና የሲሚንቶ ምርታችን በከፍተኛ መጠን የሚጨምርበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል። እንደሲሚንቶው ሁሉ ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ ያላነጋገረ ቢሆንም ከዘርፉ እድገት ጋር ተያይዞ የእንጨትና ብረታ ብረት፣ የኤሌክትሪክ እቃዎች ወዘተ ፍላጐትም በከፍተኛ መጠን ጨምሯል። እነዚህን ምርቶች የሚያመርቱ ተቋሞች የሚስፋፉበትና አዳዲሶችም የሚቋቁሙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል። በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን እንደተቀመጠው ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ማንም ከገመተው በላቀ ፍጥነትና ስፋት የሚስፋፉበት፣ የኢንዱስትሪ እድገታችንም ተያይዞ የሚፋጠንበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በተለይም የቤቶች ግንባታ መስፋፋት የተወሰነ ገንዘብ አጠራቅመው ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ ዜጐችም ጥሩ እድል እየፈጠረላቸው ይገኛል። በንግድ ስራ ተሰማርተው የተወሰነ ገንዘብ ያጠራቀሙና ይህንን በመጠቀም የንግድና የመኖሪያ ቤት ለመስራት ወይም ለመግዛት የሚፈልጉ ነጋዴዎችን አደራጅቶና አስተባብሮ ማንቀሳቀስ

☞

ከተቻለ ገንዘባቸውን በልማት ስራ ላይ የሚያሰማሩበት፣ የንግድ ስራቸውንና ኑሮአቸውን የሚያሻሽሉበት ጥሩ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ በመንግስት ደሞዝ ወይም በግል ኩባንያዎች ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞችም በረጅም ጊዜ የሚከፍሉት ብድር ከተሰጣቸውና በአግባቡ ከተደራጁ ገንዘባቸውን በመቆጠብ የቤት ባለቤት ለመሆን የሚችሉበት እድል ተመቻችቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት ጥሩ ገቢ ያገኘ አርሶ አደርም ገንዘቡን ጥቅም ላይ ለማዋልና ኑሮውን ለማሻሻል የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ባጭሩ ሂደቱ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ገንዘብ አጠራቅመው በልማት ስራ ላይ የማዋል፣ የቤት ባለቤት የመሆን እድል የሚከፍትላቸው ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፍ እድገት ለስራ ፈላጊው በተለይም በከተማ ላለው ስራ ፈላጊ ወገንም እጅግ ከፍተኛ የስራ እድል የሚፈጥርለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚያስፈልጉ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ሲስፋፉ የስራ እድል አብሮ ይፈጠራል፡፡ የኮንስትራክሽን ስራው ራሱ በ10ና በ100ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች በቀጥታ ስራ መፍጠር የሚችልና መፍጠርም የጀመረ ነው፡፡ ከኮንስትራክሽን ስራ ጋር ተያይዘው የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን በመስራት መስኩም ሰፊ የስራ እድል መፍጠር ይቻላል፤ መፍጠርም ተጀምሯል፡፡ ስለሆነም የከተማው ህዝብ የቤት ባለቤት በመሆን መልኩ ብቻ ሳይሆን የቤት ባለቤት መሆን ያልቻለውም ሰፊ የስራ እድል በማግኘቱ ከድህነት የሚላቀቅበትና በአገራችን ከተሞች ያለውን ስራ አጥነት ከመቅረፍ አኳያ ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ይታያል፡፡ በዚህ ዙሪያ በሺዎች የሚቆጠሩ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች የሚያብቡበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡ ዘርፉ ልማትን በማፋጠን፣ ድህነትንና ስራ አጥነትን በማስወገድ ረገድ ይህን ያህል የሚያጓጓ እጅግ ተስፋ ሰጪ እድል የሚከፍት ቢሆንም ከተለያዩ ችግሮች ነፃ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ዘርፉ ካሉበት ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ሃይል ችግር ያለበት መሆኑና ከዚህ ጋር ተያይዞም የስራው ጥራት ደካማነትና የሚጠይቀውም ወጪ ከፍተኛ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ወጣቱ የኮንስትራክሽን ስራን አሳንሶ የማየትና በተለይም በአንዳንድ ከተሞች በሚፈጠረው የስራ እድል በበቂ መጠን ለመጠቀም የዝግጅት መጓደል ይታያል፡፡ ከሰለጠነ የሰው ሃይል ችግር ተለይቶ የማይታየው ሌላው ችግር ስራው በርካታ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አነስተኛና መካከለኛ ኩባንያዎች ማሰማራትን የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ ያሉን ኩባንያዎች ግን በሁሉም ደረጃዎች በቁጥር አነስተኛ

☞





ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ምክንያት በአገራችን የሚከናወነው የኮንስትራክሽን ስራ የሚጠይቀው ወጪ መሆን ከሚገባው በእጅጉ የላቀ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ ጥራቱ የሚፈለገውን ደረጃ ያልያዘ ከመሆኑም ባሻገር በብቃት ጉድለትና በኩባንያዎች ቁጥር ማነስ ምክንያት የኮንስትራክሽን ስራዎች እንዲጓተቱና ባንድ ጊዜ ሰፊ ስራ ለመስራት ከባድ ችግር የሚያጋጥምበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ዘርፉ ሰራ አጥነትን በመቅረፍ ረገድ እጅግ በጣም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ሲችል በቂ የሰለጠነና በአግባቡ የተደራጀ ሃይል በመጓደሉና አልፎ አልፎም ስራው እያለ፣ የዝግጁነት መጓደል ችግር በማጋጠሙ በሚፈለገው መጠን ሳንጠቀምበት የምንቀርበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

በዘርፉ እያጋጠመ ያለው ሌላው ችግር ቤት ፈላጊውን በአግባቡ አደራጅቶና አንቀሳቅሶ ውጤት ማስመዝገብ ላይ ያለ ችግር ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የተወሰነ ገንዘብ ለማጠራቀም የቻሉ አርሶ አደሮች ገንዘባቸውን ጥቅም ላይ ለማዋል ከሚፈልጉባቸው መስኮች አንዱ የከተሞች ቤት ስራ ነው፡፡ አነስተኛ ነጋዴውም ሆነ በደመወዝ የሚተዳደረው ቤት የመስራት ከፍተኛ ፍላጐት አለው፡፡ ይሁንና እያንዳንዳቸው በተናጠል ቤት ለመስራት ቢሞክሩ ወጪው ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር የሚሰራ ኩባንያ ለማግኘትና ተቆጣጥሮ ለማሰራት በፍፁም የማይቻል ይሆንባቸዋል፡፡ በርካታዎቹ ከገቢያቸው በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ መክፈል ቢችሉም ባንድ ጊዜ ቤት ለመስራት የሚያስችል ገንዘብ ለማውጣት አይችሉም፡፡ ይህንኑ ለማካካስ የባንክ ብድር ማግኘት አስፈላጊ ቢሆንም በተደራጀ አኳኋን የሚያገኙበት እድል አልተፈጠረላቸውም፡፡

የግል ባለሃብቶች በኮንስትራክሽን ዘርፍ ተፈላጊ በሆኑ ምርቶች ዙሪያ ከፍተኛ እጥረት እየተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ የጀመሩት ባለፈው ዓመት ነው፡፡ በመሆኑም እስካለፈው ዓመት ድረስ በሲሚንቶ ፋብሪካዎችና መሰል ድርጅቶች ማቋቋም ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስብና የሚፈልግ ባለሃብት ቍራሹን አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ዘርፉ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለውና ትርፍ ሊገኝበት የሚችል ዘርፍ መሆኑን የግል ባለሃብቶች በአሁኑ ወቅት መገንዘባቸውና ሰፋ ያለ የኢንቨስትመንት ስራ መጀመራቸው በጠንካራ ጐንነቱ የሚጠቀስ ቢሆንም አዳዲስ ፋብሪካዎች ተመስርተው ምርት ማምረት እስኪጀምሩ ድረስ ጊዜ መጠየቁ ስለማይቀር እስከዛው ድረስ የኮንስትራክሽን እቃዎች እጥረት በማጋጠሙ፣ እነዚህን እቃዎች ከውጭ ለማምጣት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መጠየቁ የማይቀር ሆኗል፡፡

☞

## እድገቱ የፈጠራቸው ችግሮችን እየፈቱ እድገትን ማፋጠን

በአገራችን ፈጣንና ተከታታይ እድገት የማስመዝገብ ልምድ የለም። ከደርግ ውድቀት ወዲህ በነበሩት ዓመታት ከመቼውም ጊዜ የተሻለ እድገት የተገኘ ቢሆንም በአማካይ በ5% እና 6% መካከል የነበረ በመሆኑ ይህን ያህል ፈጣን ነበር ማለት አይቻልም። ከዚያ ባሻገር እድገቱ የሚዋዥቅ፣ አንድ ዓመት ፈጣን እድገት ታይቶ በሚቀጥለው ከዜሮ በታች የሚሆንበት ነው የነበረው። ፈጣንና ተከታታይ እድገት ማምጣት የተጀመረው ባለፉት ሶስት ዓመታት ነው። በመሆኑም ባለፉት ጊዜያት ህዝቡ የኢኮኖሚ ችግር ሲል እድገት ባለመመዝገቡ የሚከሰት ችግርን ማለቱ ነበር። ፈጣን እድገት ራሱ የራሱ ችግሮች እንደሚያስከትል ህዝቡ ሊገነዘብ የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። ይሁንናም በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፈጣን እድገት ማረጋገጥ የሚቻለው የእድገት ችግሮችን እየፈጠኑ በፍጥነት በመፍታት ብቻ ነው።

በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ዋናው ተዋናይ የግል ባለሃብቱ ነው። የግል ባለሃብቱ የሚያመርተው ምርት በገበያ ተሸጦ ትርፍ የሚያስገኝለትን እንደሆነም ይታወቃል። በገበያ እጥረት የማይታይበትን ምርት ካመረተ እንደሚከስር ስለሚያውቅ እጥረት መታየት እስኪጀምር ወይም እጥረት እንደሚያጋጥም በእርግጠኝነት መተንበይ የሚቻልበት ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ አዲስ ተቋሞችን አይገነባም። እጥረት መታየት ሲጀምር የሚገነባው ተቋም ደግሞ በወቅቱ ስለማይደርስ ለተወሰነ ጊዜ እጥረቱ ሊቀጥል ወይም ሊባባስ ይችላል። ስለሆነው በአንድ ዘርፍ ፈጣን የሚኖር ዕድገት እጥረትን ሲያስከትል የግል ባለሃብቱ እጥረት የሚታይበትን ነገር ለመሸፈን ይሯሯጣል፤ እስከዛዉ ድረስም እጥረቱ ይባባሳል። አዳዲስ ተቋሞች ሲያቋቁም እጥረቱ በመትረፍረፍና በዋጋ መውደቅ የሚገለጽበት ሁኔታም ያጋጥማል። ፈጣንና ተከታታይ እድገት ሲኖር በአንድ አካባቢ የተፈጠረ የምርት እጥረት ሲቃለል በሌላ አካባቢ እየተፈጠረ እጥረቱን ለመሸፈን ኢንቨስትመንቱ ከአንድ ዘርፍ ወደ ሌላው በሰፊው በመጉረፍ በድምሩ ፈጣን እድገት እውን ይሆናል። የገበያ ኢኮኖሚ አለመመጣጠንን (በፍላጐትና አቅርቦት መካከል) በፍጥነት በመፍታት ነው ፈጣንና ተከታታይ እድገት ሊያስመዘግብ የሚችለው። በአገራችን ኢኮኖሚ በአጠቃላይ በኮንስትራሽን ዘርፍ ደግሞ በተለይ እየታየ ያለው ችግር ይኸው ነው።

☞





የአገራችን ኢኮኖሚ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስለሆነ ከላይ ከተጠቀሰው የፈጣን እድገት ዑደትና አለመመጣጠን ነፃ ሊሆን አይችልም። ይሁንና ኢህአዴግ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ክልል ልማታዊ መንግስት ተቋቁሞ የገበያ ጉድለት በሚታይባቸው መስኮች አቅም በፈቀደው መጠን ጣልቃ በመግባት አለመመጣጠኑን ለማለዘብ መሞከር አለበት ብሎ ያምናል። ይህ መርህ ለኮንስትራክሽን ዘርፍም ይሰራል። በመሆኑም መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል።

የግል ባለሃብቶች በኮንስትራክሽን ዘርፍ የታየውን እጥረት ተገንዝበው እጥረቱን ለማስወገድ ብሎም ትርፍ ለማግኘት በሚሰማሩበት ወቅት የሚያጓትታቸው ነገር ፋብሪካዎችን ለማቋቋምና ስራ ለማስጀመር ጊዜ የሚወስድ መሆኑ ብቻ አይደለም። የሰለጠነ የሰው ሃይል በበቂ መጠን ከሌለ ፋብሪካዎች ሲቋቋሙ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ተገዝቶ ኩባንያዎች ቢመሰረቱ አጥጋቢ ውጤት ሊገኝ አይችልም። የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረትን በመቅረፍ ረገድ መንግስት ወሳኝ ድርሻ አለው፣ ሊኖረውም ይገባል።

ከዚህ በመነሳት መንግስት በአሁኑ ወቅት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ነው። ዘርፉ በብዛት የሚፈልገው የሰው ሃይል በቴክኒሻንና በከፊል የሰለጠነ የሰው ሃይል ደረጃ ያለ በመሆኑ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞች የሰለጠኑ ወጣቶችን በተለያዩ በመንግስት በሚካሄዱ የግንባታ ፕሮጀክቶች እንዲሳተፉና የተግባር ስልጠናም እንዲያገኙ በመደረግ ላይ ነው። ከዚህ አኳያ በምሳሌነት የሚጠቀሱት የአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በነዚህ ፕሮጀክቶች የጀርመን ሙያተኞች ተቀጥረው ግንባታውን በማከናወን ሂደት የኛን ወጣቶች የተግባር ስልጠና እንዲሰጡ ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞቻችን ጋር በመቀናጀት ተቋማቱ የሚሰጡት ስልጠና ጥራቱ እንዲሻሻልና መጠኑም በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር እየተደረገ ነው። ሌሎች በመንግስት የሚካሄዱ የግንባታ ፕሮጀክቶችም በተመሳሳይ መልኩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆን ሰፋፊ የተግባር ላይ ስልጠና ማእከላት እንዲሆኑ እየተደረገ ነው። የኮንስትራክሽን እድገቱን ራሱን በመጠቀም እጅግ ሰፊ የሰው ሃይል ስልጠና ስራ እየተሰራ ነው።

የሰው ሃይሉን ከማሰልጠን ጐን ለጐን የሰለጠነው የሰው ሃይል በአነስተኛና ጥቃቅን የኮንስትራክሽን ድርጅቶች እንዲደራጁ እየተደረገ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ተቋሞችን ለማደራጀት የሚያስፈልገው ስልጠናና ብድር ወዘተ. እየተሰጠው በፕሮጀክቶቹ ግንባታ

☞

ላይ እንዲሳተፍና በሂደቱ ተቋሞቹ ተጠናክረው የሚወጡበት ሁኔታ እንዲፈጠር እየተደረገ ነው። ከነዚህ ተቋሞች ውስጥ አንዳንዶቹ ተጠናክረው መካከለኛ አልፎ አልፎም ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የሚሆኑበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ተብሎ የሚገመት ሲሆን የተቀሩት በአነስተኛ ተቋምነት እንደሚቀጥሉ ይታሰባል። ይህ ሂደት ያለማቋረጥ ቀጥሎ አዳዲስ ተቋሞችና የሰለጠነ የሰው ሃይል የማፍራቱ ስራ ይጠናከራል ተብሎም ይገመታል። በሌላ አነጋገር እድገቱ የፈጠረው ችግር በራሱ በእድገቱ የሚፈታበት አቅጣጫ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል።

የኮንስትራክሽን ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ሙያተኞችና ታላላቅ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችንም ይጠይቃል። በመሆኑም በዩኒቨርሲቲዎቻችን የሚመረቁ መሃንዲሶችን በከፍተኛ ደረጃ ለመጨመር ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ጥራቱን ለማሻሻል ከጀርመን ሙያተኞች ጋር በመሆን ሲደረግ የነበረው ዝግጅት በመጠናቀቁ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ጥራቱን የማሻሻል ሰፊ ስራ ይሰራል ተብሎ ይጠበቃል። በአገሪቱ ያሉ ታላላቅ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ብቃት ለማሻሻል የሚያስችል የስልጠናና የውስጣዊ አሰራር ማሻሻል ስራ ለመስራት ከውጭ ሙያተኞች ጋር በመተሳሰር ዝግጅት በመደረግ ላይ ያለ ሲሆን ፕሮግራሙ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ መሆን እንደሚጀምር ይገመታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የኮንስትራክሽን ስራ እድል በሚፈጠርበት ወቅት እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ስራ ፈላጊ ወጣቶች በእድሉ በበቂ ደረጃ ሳይጠቀሙ የሚቀሩበት ሁኔታ ተስተውሏል። ይህ ችግር ወጣቶቹ ረዘም ላለ ጊዜ ስራ አጥ ሆነው በመቆየታቸው ያዳበሯቸው አንዳንድ በጐ ያልሆኑ ጠባያት በመኖራቸውና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ስራ የማማረጥ ዝንባሌ ስላለ የተፈጠረ ችግር ነው። በርግጥ ይህ ችግር በአገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ እንደዋነኛ ችግር ሊቀመጥ የሚችል አይደለም። የስራ ዕድሉ ሲገኝ ያለማቅማማት ሊጠቀሙበት ዝግጁ የሆኑ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ስላሉ ከአጭር ጊዜ አኳያ እነዚህን ወጣቶች በማሳተፍ ችግሩ ሊወገድ ይችላል። ለዘለቄታው ግን የስራ ማማረጥ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት ህዝቡና ኢህአዴግ ሊታገሉበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ የሚያመላክት ነገር ተደርጐ ሊወሰድ ይገባዋል።

ቤት ፈላጊዎች በአግባቡ ባለመደራጀታቸው የተፈጠረው ችግር፣ የኮንስትራክሽን ዘርፉ አሁን ከሚታየውም እድገት በላይ እንዳይታይ እንቅፋት መሆኑ ቀደም ሲል ☞





ተጠቅሷል። ገበያውና የግል ባለሃብቶች ይህንን ችግር በራሳቸው ሊቀርፉት አይችሉም። የገበያ ጉድለት ያለበት ጉዳይ ስለሆነ መንግስት ጣልቃ ሊገባበት የሚችልና የሚገባውም ጉዳይ ነው። መንግስት ይህንኑ በመገንዘብ ለበርካታ ዓመታት ዝግጅት ሲያደርግበት ቆይቷል። በመጠነኛ ዋጋ ቤቶችን አሰርቶ ከፍለው በመግዛት ወይም ተበድረው ለመክፈል ለሚፈልጉ ሰዎች የማስተላለፍ አሰራር በአዲስ አበባ ከተማ በመሞከር ከዚሁ በተገኘው ልምድ ላይ በመመስረት ስርዓቱን በአገሪቱ በመላ ለማስፋፋት ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል፣ ጠቃሚ ልምድም ተገኝቷል። በመሆኑም ይህንን አሰራር ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ከየክልሉ በተመረጡ ዋና ዋና ከተሞች ለማስፋፋት የሚያስችል ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ስርዓቱ ሁለት የተሳሰሩ ባህርያት ያሉት ይሆናል ተብሎ ይገመታል። በመጀመሪያ ደረጃ ቤት ለመስራት ፍላጐት ያላቸው አርሶ አደሮች፣ አነስተኛ ነጋዴዎች፣ የመንግስት ሠራተኞች ወዘተ ፕሮግራሙ ተገልፆላቸው ፈቃደኛ የሆኑት ይመዘገባሉ። መንግስት ቤቶች አሰርቶ ከጨረሰ በኋላ ለተመዘገቡ ሰዎች እንዲተላለፉ ይደረጋሉ። የቤቶችን ዋጋ ባንድ ጊዜ ከፍለው ለመውሰድ የሚችሉ (የተወሰኑ አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎች ወዘተ) ከፍለው እንዲወስዱ ይደረጋል። ይህንን ለማድረግ የማይችሉቱ በመጀመሪያ ከቤቶቹ ዋጋ እስከ 20% የሚሆነውን ከፍለው፣ የቤቱን ካርታ በባንክ በማስያዝ ከባንክ ተበድረው የሚከፍሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። እጅግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በመጠነኛ ወለድና (ከባንክ ወለድ ባነሰ መጠን) በረጅም ጊዜ ሊከፍሉ የሚችሉበት እድል ይመቻቻል፤ ለነዚህ ክፍሎች የሚመጥኑ ቤቶችም በተወሰነ መጠን እንዲሰሩ ይደረጋል።

ከላይ የተጠቀሰው አሰራር የሚመለከታቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የቤት ባለቤት በመሆን ወይም የተሻለ ቤት በማግኘት ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ገንዘባቸውን ቆጥበው በአቅማቸው ለልማት ስራ እንዲውል በማድረግ ልማታችን እንዲፋጠን፣ የከተሞች ውበት እንዲሻሻልና የከተሞች የመጠለያ እጥረት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እንዲቀረፍ ያደርጋል። አቅሙ እያላቸው በተናጠል ቤት በማሰራት ለመጠቀም ያልቻሉትን መንግስት እንዲደራጁ በማድረግ የተፈጠረውን ማነቆ እንዲወገድ ለማድረግ ያስችላል።

ከላይ የተጠቀሱት የቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች እንደሌሎቹ በመንግስት የሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች ሁሉ እዚያው ሳሉ ሰፊ በተግባር ላይ የተመሰረተ የሰው ሃይል ስልጠናና የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ማቋቋም ስራ የሚፈጸምበት ይሆናል። በሌላ ☞

አነጋገር እድገቱ የፈጠረውን የሰለጠነ የሰው ሃይልና የተቋማት ችግር እድገቱን ራሱን በማፋጠን ሂደት ለመፍታት የሚያስችል ይሆናል፡፡ ይህ ስራ በከተሞች ያለውን ስራ አጥነት በመቅረፍ ረገድም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በኮንስትራሽን ስራ የሚቀጠሩ ሰዎች ከአጭር ጊዜ አኳያ የቤት ባለቤት ባይሆኑም የስራ እድል አግኝተው በሂደት የቤት ባለቤት የሚሆኑበት ወይም በሚያገኙት ገቢ ቤት ተከራይተው የተሻለ ኑሮ የሚኖሩበት ሁኔታም ይፈጠራል ተብሎ ይገመታል፡፡ በሌላ አነጋገር በቤቶች ግንባታ ዙሪያ የሚፈጠረው የስራ እድል በሂደት ተጨማሪ የቤቶች ግንባታ ጥያቄን በማስነሳት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እድገት ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል፡፡ የህዝቡን የመግዛት አቅም በመጨመር የተለያዩ ሸቀጦች እጥረት ተከስቶ እነዚህን እጥረቶች ለማስወገድ የግል ኢንቨስትመንት እንዲበራከትና የኢንዱስትሪ ፈጣን እድገት ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግም ያስችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት መንግስት እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች ገበያው ራሱ ሊፈታቸው የማይችልና መንግስት የግድ ጣልቃ ሊገባባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የኮንስትራክሽን እቃዎችን በተመለከተ የተፈጠረው ችግር ግን በመሰረቱ ገበያው ራሱ ሊፈታቸው የሚችልና የሚገቡ ናቸው፡፡ በገበያው እጥረት ሲታይ የግል ባለሃብቶች ዘግይተውም ቢሆን ኢንቨስት አድርገው ይፈቱታል፡፡ እጥረት ካልታየ ወይም እንደሚታይ እርግጠኛ ካልተሆነ የግል ባለሃብቶች ኢንቨስት አያደርጉም፤ ስለሆነም ቀጣይ እድገት አይኖርም፡፡ ስለሆነም መንግስት ከገበያ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ባህሪ የሚፈጠሩ የአቅርቦትና የፍላጐት አለመጣጣምን ማስቀረት ቢፈልግም አይችልም፣ ከሞከረም ውጤቱ እድገትን ማቀጨጭ ነው የሚሆነው፡፡ የግል ባለሃብቶች ከእጥረቱ ተነስተው ኢንቨስት እንዳያደርጉ በማሰናከል በአጠቃላይ የእድገቱን ፍጥነት መቀነስን ያስከትላልና፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር አለመጣጣሙ ከአጭር ጊዜ አኳያ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ማለዘብ ብቻ ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በበለጠ ለመረዳት መንግስት የሲሚንቶ ምርትን በተመለከተ የተከተለውን ፖሊሲ መመልከት ይጠቅማል፡፡ መንግስት አጠቃላይ የኢኮኖሚውን እድገት ግምት ውስጥ በማስገባት ከጥቂት ዓመታት በኋላ እጥረት ሊያጋጥም ይችላል ብሎ በመገመት በዘርፉ የግል ባለሃብቶችን ለማበረታታት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ይሁንና

☞





ዘርፉ የሚጠይቀው ኢንቨስትመንት በጣም ከፍተኛ በመሆኑና በወቅቱ በአገሪቱ ያሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅም አምርተው መሸጥ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ የወደቁበት ሁኔታ ስለነበረ ደፍሮ የሚገባ የግል ባለሃብት ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ችግሩን በመጠኑም ለማለዘብ የሙገር የመንግስት የሲሚንቶ ፋብሪካን በማስፋፋት ምርቱን በእጥፍ እንዲጨምር ለማድረግ እቅድ ተይዞ ጥናቱና ዝግጅቱ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ ይሁንና የሲሚንቶው እጥረት ማንም ከገመተው ፍጥነት እጅግ በላቀ ሁኔታ በመከሰቱ በዚህ ደረጃ የእጥረቱን ጉዳት ለማለዘብ ሊያደርግ ያቀደው ዝግጅት በወቅቱ ሳይደርስ ቀርቷል፡፡ መንግስት ከፍተኛ እጥረት መከሰቱን ሲገነዘብ የግል ባለሃብቶች በሰፊው ኢንቨስት አድርገው እስኪፈቱት ድረስ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቅ ቢሆንም ሲሚንቶ ከውጭ ሊገዛ የሚችልበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡ በመሆኑም ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ እጥረቱ ከአጭር ጊዜ አኳያ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ማለዘብ ይቻላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ኢህአዴግ የቀየሰው የልማት ስትራቴጂ በተሣካ ሁኔታ ተግባራዊ መሆን በመጀመሩ አገራችን በታሪክም ለመጀመሪያ ጊዜ ለሶስት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይ እድገትን ለማስመዝገብ በቅታለች፡፡ በቂ የኢኮኖሚ እድገት ባለመኖሩ የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ላይ የተመሰረተ ልምድ ያለው ህዝብና መንግስት ፈጣን እድገት የሚፈጥራቸውን ችግሮች በራሱ በእድገቱ እንዲፈቱ በማድረግ የእድገቱን ቀጣይነት የማረጋገጥ ስራ እንዲሰራና ልምድንም እንዲያካብት የሚጠይቅበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሚቀጥሉት ዓመታት እንደምናስበውና እንደምንመኘው ፈጣንና ተከታታይ እድገቱ የሚቀጥል ከሆነ የገበያ አለመመጣጠኖችን መፍታትና እነዚህን አለመመጣጠኖች በእድገት ምንጭነት የመጠቀም ጉዳይ የዕለት ተዕለት ስራችን ሆኖ ይቀጥላል፡፡ የፈጣን እድገት ችግሮችን የመፍታት ትግልን የመሰለ የተቀደሰ ትግል የለም ማለት ቢቻልም ዞሮ ዞሮ ትግል መሆኑ ስለማይቀር በትክክለኛ ስልትና ስትራቴጂ ሊመራ የሚገባው ይሆናል፡፡

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ እንደታየው ሁሉ ይህንን ትግል በተሳካ ሁኔታ ለመፍታት በመጀመሪያ ደረጃ የመንግስትና የግል ባለሃብቶችን ድርሻ በትክክል ለይቶ እያንዳንዱ ወገን የየራሱን ድርሻ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የልማት ስትራቴጂዎቻችን

# ስትራተጂያዊ ትርምስ በተቃዋሚዎች ጐራ

ከከበበው ዘለቀ

ከአንድ አመት በፊት የነበረው ሁኔታ ተቃዋሚዎች በምርጫው ያገኙት ያልተጠበቀ ውጤት ላይ የተመሰረተ ከፍተኛ መነሳሳትና ከልክ ያለፈ በራስ መተማመንና እብሪተኝነትን ያንፀባረቁበት ወቅት ነበር:: የኢትዮጵያን ህዝብ ከዳር ዳር ለአመፅ አነሳስተን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን እንደረምሳለን ብለው የተማመኑበት ብቻ ሳይሆን ይህንን የሚያደርጉበት ቀን ቆጥረው በይፋ ያወጁበት ወቅት ነበር:: ዛሬ ከአንድ አመት በኋላ ሁኔታቸውን ስናየው የአመፅ ሙከራቸው ከሸፎ፣ ፉከራውና ቀረርቶው በእጅጉ ቀንሶ በአንፃሩ ትርምስ ውስጥ እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል:: ሂደቱንና ፍፃሜዎችን አንድ በአንድ ቆጥሮ በመዘገብ መልኩ ማስቀመጥ ቢቻልም በጥልቀት ለመረዳት የሚቻለው የሃይሎቹን አሰላለፍና የተከተሉዋቸ-ውን ስልቶችና ስትራተጅዎችን በመመርመር ነው:: በተቃዋሚዎች ጐራ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን ስትራተጅያዊ ትርምስ በዚሁ አኳኋን እንደሚከተለው መተንተን ይቻላል::

## በምርጫው ወቅት የታየው የተቃዋሚ ሃይሎች አሰላለፍ

ተቃዋሚዎች በምርጫው ወቅት እንኳን ሌላ ራሳቸውም ከገመቱት በእጅጉ የተሻለ ድምፅ እንዳገኙ ይታወቃል:: ይሁንና በወቅቱ በተቃዋሚዎች ጐራ የተሰለፈው ሃይል በአላማውም በይዘቱም አንድ ወጥ ሃይል ነበር ማለት አይቻልም:: እጅግ የሚበዛው ተቃዋሚዎችን የመረጠው መራጭ ህዝብና የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና ዋና አን-ቀሳቃሾች የየራሳቸው አላማና መነሻ ያላቸው ከሞላ ጐደል የተለያዩ የሚባሉ ወገኖች ናቸው:: በተቃዋሚ ሃይሎች አመራርና ዋና አንቀሳቃሾች ጐራም ውስጥ ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ከሁለት ተቃራኒ ጫፎች የሚቃወሙ ሃይሎች እንደነበሩ ይታወቃል::

☞





የተቃዋሚ ሃይሎች ዋነኛ አንቀሳቃሾችና መሪዎች የሚባሉት ግፋ ቢል በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህ ህገ መንግስታዊ ስርአቱን አጥብቀው የሚጠሉና የምርጫውን ሂደት ስርአቱን ለመናድ ሊጠቀሙበት ቆርጠው የተነሱ ናቸው:: በአንድ በኩል ፌዴራሊዝምን በመርህ ደረጃ የሚፃረሩ፣ በብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ስርአት ኢትዮጵያን የሚያጠፋ ወይም ያጠፋ አድርገው የሚቆጥሩ የገነገነ ትምክህተኛ አመለካከት ያላቸው መሪዎችና አንቀሳቃሾች የተሳተፉባቸው ትምክህተኛ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰልፈዋል:: በሌላ በኩል የብሄረሰብ መብት መከበርን መፈክር በማንሳት ከቻሉ በአገር አቀፍ ደረጃ የበላይ ለመሆን፣ ይህ ካልተቻለም አገሪቱን ለመበታተንና በየብሄራቸው የጠባብ ቡድናቸውን አምባገነንነት ለማረጋገጥ ቆርጠው የተነሱ የገነገነ ጠባብነት የተጠናወታቸው ሃይሎችም ተሰልፈዋል:: እነዚህ ሀይሎች ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ከሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚቃወሙ ስለሆኑ የሚያስተሳስራቸው የጋራ ፕሮግራም የሌላቸው መስለው ሊታዩ ይችላሉ:: ይሁንና መነሻቸው ምንም ይሁን ምን፣ ሁለቱም ህገ መንግስታዊ ስርአቱን አምርረው በመጥላታቸውና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በመናድ አጀንዳ ዙሪያ የጋራ አቋም ይዘዋል:: በመሆኑም በምርጫው ሂደት እነዚህ ተቃራኒ የሚመስሉ ሃይሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በአንድ የተቃውሞ ጐራ ተሰልፈው ታይተዋል::

ከሁለት ተቃራኒ አመለካከት ተነስቶ በአንድ የተቃውሞ ጐራ የተከማቸው የአመራርና የዋና አንቀሳቃሾች ሃይል በዚህ ጐራ እንዲሰለፍ ያደረጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ ያለፈው ስርአት ቅሪት የሆኑና የኛ ነው የሚሉት ስርአት ተንዶ በምትኩ አዲስ ህገ መንግስታዊ ስርአት መፈጠሩ ያልተዋጠላቸውና መቼም ቢሆን የማይዋጥላቸው በተገኘው እድል ስርአቱን ለመናድ ከመሞከር ወደኋላ የማይሉ ሰዎች ቁልፍ ሚና ነበራቸው:: ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ባለፉት 15 አመታት ተስፋ ሳይቆርጡ ስርአቱን ሲታገሉ የነበሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ለስርአቱ ያላቸው ጥላቻ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ስርአቱን ማፍረስ እንደማይቻል ተገንዝበው አኩርፈው ዳር ተቀምጠው የነበሩ ናቸው:: በምርጫው ውድድር ሂደት ተስፋ ቆርጠው ዳር ተቀምጠው የነበሩት ቀዳዳ የተገኘ መስ-ሎዋቸው የተቃውሞ ጐራውን በከፍተኛ ወኔ በመቀላቀላቸው የአመራርና የዋና አንቀሳቃሽ ሃይሉን ቁጥር አበራክቶታል::

☞

ያለፈው ስርአት ከፍተኛ ባለስልጣኖች ወይም አንቀሳቃሾች ባይሆኑም በተለያዩ የጠባብና የትምክህተኛ ድርጅቶች ውስጥ ታቅፈው የነበሩ አዲሱ ስርአት ከአመለካከታቸው ጋር የማይጣጣም ስለሆነ ስርአቱን አምርረው የሚጠሉና የሚቃወሙ ወገኖችም በጐራው ውስጥ ተሰልፈዋል። በነዚህም ሰዎች ዙሪያ በአንድ በኩል ባለፉት 15 አመታት ስርአ-ቱን ያለማቋረጥ የተፋለሙና ስርአቱን አምርረው ቢጠሉም ተስፋ ቆርጠው አኩርፈው ከቆዩ በኋላ በምርጫው ሂደት ቀዳዳ የተገኘ መስሎዋቸው ጐራውን በስሜት የተቀላቀሉ ይገኙባቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ዋነኛዎቹ የተቃውሞ ሃይሎች በተጨማሪ በተለያየ የግል ቂምና ቁርሾ የተቃዋሚን ጐራ ተቀላቅለው ያጠናከሩ በቀላሉ የማይታዩ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል። በስርአቱ ውስጥ የሚታይ የተለያዩ ጉድለቶች አስቀይሟቸው ከስርአቱ ጋራ የተራራቁ (alienated) በርካታ ሰዎች በተለይም ከወጣቶች አካባቢ የጐራው ዋነኛ አን-ቀሳቃሽ ሆነው የተሰለፉ እንደነበሩም ይታወቃል። ባጭሩ በምርጫው ሂደት ተስፋ ቆርጦ ዳር ቆሞ የነበረውም፣ ባለማቋረጥ ሲፋለም የነበረውም አንድ ላይ በመቀላቀሉ፣ ከጠባብነትም ከትምክህትም በመነሳት ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለመናድ የተነሳው በአንድ ጐራ በመ-ሰባሰቡ ይኸው ሃይል ከወትሮው በተለየ ሁኔታ እንዲበራከትና በከፍተኛ ስሜት እንዲነሳሳ አድርጐታል። በመሆኑም ለወትሮው ግፋ ቢል በመቶዎች ይቆጠር የነበረው ይኸው ሃይል በምርጫው ሂደት በሽዎች ምናልባትም በአስር ሽዎች የሚቆጠር ሃይል ለመሆን በቃ።

ይህ ሃይል በምርጫው ሂደት አሳካለሁ ብሎ ያሰበው አላማ አንድና ግልፅ ነበር። የምርጫው ውድድር የሚፈጥረውን ሁኔታ በመጠቀም ህዝቡን በስርአቱ ላይ ማነሳሳት፣ በዚህ ላይ በመመስረትም ከተቻለ ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በተገኘው አማራጭ መንገድ መናድና ሙሉ በሙሉ ማፈራረስና ካልሆነም ስርአቱ ተመልሶ ሊጠገን በማይችልበት መልኩ በማዳከም መዋቅራዊ ለውጦችን ማምጣትና በዚህ ላይ በመመስረት ስርአቱን የማፈራረስ ተግባር ደረጃ በደረጃ ማከናወን የሚል ግልፅ አላማ ነው የያዙት። የተቃዋሚው ጐራ በምርጫው ወቅት ከነበሩት ጠንካራ ጐኖች አንዱ በውስጡ የነበሩ እጅግ በርካታ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው አንድና ግልፅ የጋራ አላማ ይዞ፣ ሁሉንም እንቅስቃሴ ይህንኑ አላማ ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን ለመቃኘት መሞከሩና ከሞላ ጐደልም ለመቃኘት በመቻሉ ☞





ነው።

በምርጫው ወቅት ድምፁን ለተቃዋሚዎች የሰጠውና ከዚህ አኳያም ሲታይ ቢያንስ በጊዜያዊነት ወደ ተቃዋሚ ጐራ ገብቶ የነበረው ሃይል ግን ከላይ የተጠቀሰው ብቻ አል-ነበረም። ድምፁን ለተቃዋሚዎች የሰጠው ህዝብ በሽዎች ሳይሆን በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ ነበር። እንደዚህ አይነቱ መራጭ በከተማ ብቻ ሳይሆን በተወሰነ ደረጃ በገጠርም ነበር የታየው። ይኸው መራጭ ህዝብ በኋላ በግምገማም እንደተረጋገጠው ተቃዋሚዎችን ከመደገፍ ይልቅ ኢህአዴግን እንደተቃወመ ሊታወቅ ይገባል። ተቃዋሚዎች እንኳን ለህዝቡ ለራሳቸውም በውል የማይታወቅ ፕሮግራም ይዘው በቀረቡበት ሁኔታ ህዝቡ ፕሮግራማቸውን አይቶና አምኖበት እንዳልመረጣቸው ግልፅ ነው። ስለዚህም ህዝቡ በወሳኝነት የሰጠው ኢህአዴግን የመቃወም ድምፅ (Protest Vote) ነው። ኢህአዴግን ተቃውሞ ድምፅ የሰጠባቸው በርካታ ምክንያቶች ነበሩ።

በገጠሩ አካባቢ ህዝቡ በተወሰነ ደረጃ ከማዳበሪያ ዋጋ መጨመርና የብድር መመለስ ችግር ጀምሮ በየአካባቢው እስከሚታዩ የተለያዩ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችና ተቃውሞዎች ነበሩት። ከዚያም ባሻገር ኢህአዴግ ጥያቄያችንም ሆነ ብሶታችን በአግባቡ አያዳምጠንም፣ አዳምጦም አጥጋቢ ምላሽና መፍትሄ አይሰጠንም የሚል በተጨባጭ እውነታ ላይ የተመሰረተ ቅሬታ ተስተውሏል። በዚህ ምክንያት በኢህአዴግ ላይ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ቀላል ባልሆነ ደረጃ ታይቷል። ዋናውና መሰረታዊ ችግር ይህ ሆኖ ሳለ በዚህ ላይ በመመስረት በተቃዋሚዎቹ የተነዛ የተለያየ የጠባብነትና የትምክህተኝነት አመለካከት፣ እንዲሁም የሃሰት ተስፋና የማደናገሪያ ቅስቀሳም የበኩሉን ድርሻ ተጫውቷል።

በከተሞች በተለይም በወጣቱ አካባቢ በገጠሩ እንደታየው አይነት ተቃውሞና በኢህአዴግ ላይ ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያ ታይቷል። ይልቁንም በከተሞች አካባቢ የታየው ተቃውሞ ከገጠሩም የሰፋና በይበልጥ ስር የሰደደ ነበር። የስራ አጥነት ችግር፣ ኢህአዴግ ለገጠሩ ህዝብ ካልሆነ ለከተማው ህዝብና ወጣት ደንታ የለውም በሚል ቅስቀሳና አስተሳሰብ ተባብሶ ከኢህአዴግ የመራቅና የመነጠል መንፈሱ የተለየ ስፋትና ጥልቀት የታየበት ነበር። የትምህርት ስርአቱ ከሞላ ጐደል የጠባብና የትምክህተኛ ሀይሎች መናሃሪያ ሆኖ መቆየቱ፣ ወጣቱ በችግሮች ትንታኔና አፈታት ላይ በባለቤትነት እንዲሳተፍ ካለመደረጉ ☞

መሰረታዊ ጉድለት ጋር ተያይዞ የመነጠል ስሜቱ እንዲባባስ አድርጐ ነበር። እንደዚህ አይነቱ ስፋትና ጥልቀት ያለው የመነጠል ስሜት በምርጫው ዋዜማ የተፈጠረ ሳይሆን ለአመታት ሲከማች የነበረ ነው። ይኸው ስሜት በጠባብነትና ትምክህተኝነት ተባብሶ በምርጫው ወቅት ጐልቶ ቢወጣም ኢህአዴግ ከምርጫው በፊት በነበሩ አመታት ችግሩን ተገንዝቦ ለመፍታት ሲሞክረው የነበረ ነገር ግን ሳይፈታ የቆየ ችግር ነው።

ይህን የተቃውሞ ድምፅ የሰጠው መራጭ አላማው በዋናነት ህገ መንግስታዊ ስርአ-ቱን መናድ አልነበረም። በተለይም በገጠሩ አካባቢ የነበረው መራጭ የምርጫ ካርዳችንን በመጠቀም ለኢህአዴግ ማስጠንቀቂያ እንሰጣለን፣ በምርጫ አለመደገፋችንን ተገንዝቦ ስህተ-ቱን እንዲያስተውል እናስገድደዋለን የሚል አላማ ነበረው። ለኢህአዴግ የተቃውሞ ድምፅ ከሰጡት መራጮች መካከል በዋናነት በከተሞች በተወሰነ ደረጃም በገጠሮች ኢህአዴግን በሌሎች ቀይረን ሌሎቹ ይሻሉ እንደሆነ በተግባር እንሞክራቸው በሚል ድምፅ የሰጠ መራጭም እንደነበረ ይታወቃል። በሌላ አነጋገር ለተቃዋሚዎች ድምፅ ከሰጠው ህዝብ ውስጥ እጅግ በጣም የሚበዛው የዴሞክራሲ መብቱን እጅግ በሳልና የተራቀቀ ሊባል በሚችል ደረጃ ለመጠቀም የወሰነና በተግባርም የተጠቀመበት ሃይል ነበር ማለት ይቻላል። የምርጫ ካርድ ዞሮ ዞሮ ሃይለኛ መሳሪያ የሚሆነው ህዝቡ ለመሪዎቹ እንደአስፈላጊነቱ ማስጠንቀቂያ ወይም ማበረታቻ የሚሰጥበት፣ እንደሁኔታው የሚያስቀጥልበት ወይም የሚተካበት መሳሪያ በመሆኑ ነው። ህዝቡ የምርጫ ካርድን ሃይለኛነት ተገንዝቦ በአግባቡና በተራቀቀ አኳኋን የተጠቀመበት ነበር ማለት ይቻላል። ህገ መንግስታዊ ስርአቱ ራሱ ያጐናፀፈውን መብት በሰከነ መንፈስና ውጤት ያስገኝልናል ባለው አኳኋን በህገ መንግስታዊ ስርአቱ በተቀመጡ ሰላማዊና ህጋዊ መንገዶች የተጠቀመበት ክስተት ነው የነበረው። ይህ በአገራችን ስር እየሰደደ ካለው ዴሞክራሲ አኳያ አዲስና ማንም ያልጠበቀው እድገት ነው ሊባል ይችላል።

## ከምርጫ ውድድር ወደ አመፅ

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫው ውጤት እንደታወቀ እነሱው ራሳቸው ከገመቱት ☞





በእጅጉ የተሻለ ድምፅ በማግኘታቸው ተደስተው አርፈው አልተቀመጡም። አላማቸው ህገ መንግስታዊ ስርአቱን መናድ ነበርና ያገኙት ድምፅ ፌዴራል መንግስቱን ወይም የክልል መንግስታትን ተቆጣጥረው ይህንኑ ተልእኮ ለመፈፀም የሚያስችላቸው እንዳልሆነ ሲገነዘቡ ውጤቱን እንደማይቀበሉ አውጀው አላማቸውን ለመተግበር ተንቀሳቀሱ። ምርጫው ተጭ-በርብሯል የሚል መፈክር በማንሳት ከተቻለ በህዝብ አመፅ ስርአቱን መናድ ካልሆነም አመፅን በመሳሪያነት በመጠቀም በህገ መንግስታዊ ስርአቱ ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ደረጃ በደረጃ የመናድ ስራውን ለማከናወን ተንቀሳቀሱ።

ምርጫው ተጭበርብሯል የሚል መፈክር እንዲሁ የወቅቱ ሁኔታን በመታዘብ እንዳጋጣሚ ያነሱት መፈክር አልነበረም። ገና ምርጫው ሲጀምር ጀምሮ ምርጫው መጭበርበሩ አይቀርምና ሲጭበረበር ህዝቡን ለአመፅ እናነሳሳለን ብለው በይፋ አውጀው ሲዘጋጁበት የነበረ ጉዳይ ነው። ይልቁንም ይህንኑ በዝርዝር የሚያትት መፅሃፍ ከመሪዎቻቸው አንዱ በሆነውና የደርግ የቀይ ሽብር ዘመቻ አራማጅ በነበረው ነገደ ጐበዜ ተፅፎ በምርጫው ውድድር ሂደት ተሰራጭቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። የምርጫው ተጭበርብሯል መፈክር በምርጫው በነቂስ የተሳተፈውንና በቀላሉ የማይገመት ህዝብ ተቃውሞውን በገለፀበት ሁኔታ ህዝቡን ለአመፅ ለማነሳሳት ያገለግላል ብለው የነደፉት ስትራተጅ ማስፈፀሚያ መፈክር ነበር። ህዝቡ አቋሙን በህጋዊ መንገድ ገልፆ እያለ ውሳኔው በሌላ ሃይል በማንኛውም መንገድ ከተቀለበሰ መቆጣቱ አይቀርም። ይሁንና ኢህአዴግን ያልመረጠው የህብረተሰብ ክፍል ተቃውሞውን በድምፅ መስጫ ካርዱ ገልፆ ግቡን ያሳካ መሆኑን ተቃዋሚዎች በውል ተገንዝበውት ነበር ማለት አይቻልም። ከዚህም አልፎ ይህ መፈክር የአለምን ህብረተሰብንም ከጐናችን ያሰልፋል ብለው ገምተው ነበር። አንዳንዶቹ የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ጠንካራ ተቃዋሚ እንዲኖር የማድረግ በግልፅ የሚታወቅ አላማ የነበራቸው በመሆኑና ዴሞክራሲን እናስፋፋለን ስለሚሉ ምርጫው ተጭበርብሯል ብለን ካንገራገርን በመንግስት ላይ ተፅእኖ ያሳርፋሉ፣ አልፎ ተርፎም በኛ ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዳይወሰድብን ይከላከሉልናል የሚል ግምት ነበራቸው።

ተቃዋሚዎቹ መፈክራቸውን መርጠው ለአመፅ ሲንቀሳቀሱ ታሳቢ ያደረጉዋቸው በርካታ ነገሮች ነበሩ። በመጀመሪያ ደረጃ በምርጫው ሂደት ያነሳሱት ዋነኛ አንቀሳቃሽ ☞

ሃይላቸውንና እነሱን የመረጠውን ህዝብ የአመፅ መሳሪያ ማድረግ ይቻላል የሚል ግምት ነበራቸው:: በርግጥ ብዙዎቹ የመረጣቸው ህዝብ ኢህአዴግን እንደተቃወመ እንጅ እነሱን እንዳልመረጠ የአመፅ መሳሪያ ለመሆን ዝግጁ መሆኑ አጠያያቂ እንደሆነ ሳይገባቸው ቀርቶ ነበር ማለት አይቻልም:: ይሁንና በምርጫው ውድድር ሂደት የተፈጠረው ስሜት «ሳይበርድ» ወደ አመፅ ከመራነው እድል ይኖረናል የሚል ግምት እንደነበራቸው ግልፅ ነው:: ለዚህም ነው በተደጋጋሚ የህዝቡ ስሜት እንዳይበርድ መከላከል አለብን፣ የህዝቡ ስሜት ሳይበርድ አንድ ነገር ማድረግ አለብን ሲሉ የነበሩት:: ድምፅ የሰጣቸው ህዝብ ዘላቂ የፖለቲካ መሰረት ሊሆናቸው እንደማይችልና ወደ ነባራዊ አሰላለፉ ሳይመለስ ቶሎ ብለው የአላማቸው መሳሪያ ማድረግ እንዳለባቸው ተገንዝበው አመፅን በተቻለ ፍጥነት ለመፈፀም የተራወጡበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያትም ይኸው ነበር::

ከዚህ ባሻገር ተቃዋሚዎች የምእራቡ አለም በኢህአዴግ ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል፣ ኢህአዴግም  ሲሆን በተፅእኖ ተንበረክኮ ስርአቱን ክፉኛ የሚያዳክም ለውጥ እንዲቀበል ያደርጉልናል የሚል እምነት ነበራቸው:: አነሰ ቢባል ግን መንግስት በኛ ላይ ጠንካራ ህጋዊ እርምጃ እንዳይወስድ አንቀው ይይዙልናል የሚል እምነት ነበራቸው:: የአውሮ ህብረት ታዛቢ የነበረችውና በአሁኑ ሰአት በአደባባይ የተቃዋሚ ሃይሎች ጠበቃ መሆንዋን ያጋለጠችው አና ጎሜዝ የወሰደችውም አቋም ተቃዋሚዎች በዚሁ እምነታቸው እንዲፀኑ አድርጓቸዋል:: ኢትዮጵያ የውጭ ብድርና እርዳታ በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልጋት አገር መሆንዋና እነዚህ እርዳታ ሰጭና አበዳሪ መንግስታት በኢትዮጵያ ጠንካራ ተቃዋሚ እንዲኖር የሚፈልጉ መሆናቸው ተቃዋሚዎች በዚህ ረገድ  ለወሰዱት ግምት ሌላው መነሻ ነበር::

ተቃዋሚዎች በታሳቢነት የወሰዱት ሌላው ግምት ኢህአዴግ ተዳክሞ በመፈረካከስ ላይ ነውና ትንሽ ብንገፋው በቀላሉ ሊፈነገል ይችላል የሚል ነው:: ከገመቱት ውጭ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ድምፅ ማግኘታቸው ለዚሁ ግምት አንዱ መነሻቸው ነበር:: በወቅቱ ኢህአዴግ የቀየሳቸውን ስልቶች ከድክመትና ከመደናገጥ የመነጩ አድርገው መወሰዳቸውም ለግምታቸው ሌላው መነሻ ነበር:: ኢህአዴግ ምንም ቢሆን እርዳታና ብድር የሚሰጡትን ሃይሎች ገደል ግቡ ብሎ የሃይል እርምጃ አይወስድም፣ ከወሰደም እርዳታው ተቋርጦ ባጭር ጊዜ ውስጥ ይፍረከረካል የሚል ግምገማ ማስቀመጣቸው ተጨማሪ የግምታቸው

☞





መነሻ ነበር::

ከላይ የተገለፁትን ግምቶች ይዘው በቀጥታ ወደአመፅ ለመግባት በሚወራጩበት ወቅት ኢህአዴግ ተጭበርብሯል የተባለው ድምፅ የውጭ ታዛቢ ባለበት ይጣራ በማለቱ ተቃዋሚዎች ለጊዜው ግራ የተጋቡበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: ከዚህ በመነሳት በአንድ በኩል በዚህ የማጣራት ሂደት ውስጥ ከገባን የህዝቡ ስሜት ይበርዳል፣ በማጣራት የምናገኘው ጥቅም የለም የሚሉ ክፍሎች የነበሩ ሲሆን በሌላ በኩል በዚህ የማጣራት ሂደት ውስጥ ከገባን ደግሞ ይጣራ እየተባለ ባለበት ወቅት ወደአመፅ ብንገባ ህዝቡም አይቀበለንም፣ የምእራቡ አለም ድጋፍም አይገኝም ብለው የተከራከሩም ነበሩ:: በመጨረሻም እያቅማሙ ወደማጣራቱ ገብተው ሂደቱን ለማደናቀፍ ሞከሩ:: የማጣራት ሂደቱ ሲጠናቀቅ የተቃዋሚዎች አጋር የሆነችው አና ጎሜዝ ለአመፃቸው የሚሆን ቀዳዳ ለማቀበል ብትሞክርም ሌሎች ታዛቢዎች ግን ምርጫው አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩበትም በመሰረቱ ትክክለኛ እንደነበረ አረጋገጡ::

የማጣራቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ተቃዋሚዎቹ ለአመፃ የሚያደርጉትን ዝግጅት አጧጧፉ:: በዚህ መሰረት በአንድ በኩል ከአጋራቸው አና ጎሜዝ ጋር በማሴር የሽግግር መንግስት ማቋቋምን ማእከል ያደረገና በህገ መንግስቱ የተቋቋሙ ቁልፍ ተቋሞችን የሚንድ ህብረተሰቡ በስርአቱ ላይ ያለውን እምነት የሚያጠፋ ሃሳብ አቀረቡ:: የዚሁ ሃሳብ ግብ የስርአቱን ምሰሶዎች በመናድ፣ ህዝቡ በስርአቱ ላይ ያለውን እምነት በመሸርሸር ስርአ-ቱን ወደማያባራ ቀውስ በመክተት ደረጃ በደረጃ የመናድ ነበር:: ይህ ሃሳብ በኢህአዴግ ተቀባይነት እንደማይኖረው ሲረጋገጥ በመጨረሻው ሰአት ለይስሙላ ያደረጉት ድርድር እንደተጠበቀ ሆኖ የአመፅ መንገድን ተከትለው ነጐዱ::

## የኢህአዴግ ታሪካዊ ግምገማና የነደፋቸው ስልቶች

ምርጫው በተካሄደ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተሰብስቦ ሂደቱን በመገምገም የአጭርና የረጅም ጊዜ የመፍትሄ ሃሳቦችን ቀየሰ:: ኢህአዴግ በግምገማው ወቅት ካስቀመጣቸው ትክክለኛ ድምዳሜዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ::

☞

የተካሄደው ምርጫ እጅግ የተሳካና ታላቅ የዴሞክራሲ ክንዋኔ ነበር የሚል መደምደሚያው የመጀመሪያውና መሰረታዊው ነበር። ኢህአዴግ ከጠበቀው በላይ ህዝብ የተቃውሞ ድምፅ በሰጠበት ወቅት ታላቅ የዴሞክራሲ ድል ተገኝቷል ብሎ መገምገሙ ግር ያላቸው ወይም ይህን ግምገማ ለይስሙላ የተቀመጠ ግምገማ አድርገው የወሰዱት ጥቂቶች አልነበሩም። ኢህአዴግ ሂደቱ ታላቅ የዴሞክራሲ ድል ነበር ያለበት ዋናው ምክንያት ተቃውሞ ያለው ህዝብ በታሪካችን በተደጋጋሚ እንደታየው ወደ አመፅና ብጥብጥ ሳይገባ ህገ መንግስቱ ባስቀመጠው ስርአት በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ በምርጫ ካርድ ፍላጎቱን ለመግለፅ የቻለበት ሂደት ስለነበረ ነው። በስልጣን ላይ ያለውን ርቲ የሚደግፉ ወገኖች ብቻ ሳይሆን የሚቃወሙትም ተቃውሞዋቸውን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በተከተለ አኳኋንና በበሰለ መንገድ መግለፃቸው የዴሞክራሲ ስርአታችን ስር እየሰደደና እየተጠናከረ መሆኑን ስለሚያመላክት ነው። ተቃውሞ ማለት ብጥብጥ መሆኑ ቀርቶ የምርጫ ካርድን በመጠቀም የሚፈፀም ውድድር መሆኑ የዳበረ ዴሞክራሲ መገለጫ ስለሆነ ሂደቱ ስርአታችን በይበልጥ እየጐለበተና እየዳበረ መሄዱን ስለሚያረጋግጥ ነበር ኢህአዴግ ታላቅ የዴሞክራሲ ድል ነው ብሎ የደመደመው።

የኢህአዴግ ሁለተኛ መሰረታዊ ድምዳሜ ለተቃዋሚዎች ድምፁን ከሰጠው ህዝብ ውስጥ እጅግ የሚበዛው ኢህአዴግን ተቃወመ እንጂ ተቃዋሚዎችን አልደገፈም፤ ኢህአዴግን የተቃወመበት ዋናው ምክንያትም የኢህአዴግ ድክመቶች ስላስቀየሙት ነው የሚል ነበር። ድህነትን ለመዋጋት ያደረግነው ጥረት አመርቂ ውጤት ማስገኘት የጀመረው ዘግይቶ በመሆኑ በብዙዎች ዘንድ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንደፈጠረ፣ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ያሉብን ችግሮች ህዝቡን እንዳስቆጡ፣ ኢህአዴግ የህዝቡን ብሶት በአግባቡ አያዳምጥም የሚል መንፈስ እንደተፈጠረ፣ ህዝቡ በተለይም ወጣቱ የአገራችንን ችግሮች በመገምገም፣ መፍትሄዎችን በማስቀመጥና በመተግበር ረገድ በቂ ተሳትፎ የሌለው መሆኑ የመነጠል መንፈስ እንዳሳደረበትና ለትምክህተኛነትና ለጠባብነት አመለካከቶችም እንደተጋለጠ በግምገማው መግባባት ላይ ተደርሶበታል።

ኢህአዴግ ከዚህ በመነሳት በምርጫው ወቅት በተቃዋሚዎች የታየውን የሃይል አሰላለፍ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ ታክቲክና ስትራተጅ ቀየሰ። ለተቃዋሚዎች ድምፁን ☞





የሰጠ ህዝብ አሰላለፉን እንዲያስተካክል ማድረግ፣ ከአጭር ጊዜ አኳያ ደግሞ በሰላም ጉዳና እንዲቀጥል ማድረግ ዋነኛው ጉዳይ እንደሆነ ተሰመረበት። ህዝቡ የሰላም ሃይልነቱ እስከ-ተረጋገጠ ድረስ ተቃዋሚዎች አመፅ እንደማያዋጣቸው እንዲገነዘቡ ለማድረግ እንደሚቻል ይህ ካልሆነም የአመፅ ሙከራውን በቀላሉ ማክሸፍና መቆጣጠር እንደሚቻል ተቀመጠ።

በዚህ ላይ በመመስረት በመጀመሪያ ህዝቡ በተለይም በገጠር አካባቢ የምርጫውን ሂደት እንዲገመግምና ብሶቶቹን እንዲያስቀምጥ ተደረገ። ህዝቡ ያደረገው ግምገማ ኢህአዴግ ካደረገው ግምገማ የተለየ ውጤት አልነበረውም። ሌላው ቀርቶ ኢህአዴግን የመረጠው ህዝብም ቢሆን ለኢህአዴግ ድምፅ ያልሰጠው ወገን የሚያነሳቸውን ቅሬታዎች እንደሚጋራ ልዩነቱ ኢህአዴግን የመረጠው ወገን ከቅሬታው በመነሳት ለተቃዋሚዎች ድምፅ መስጠት የባሰ ጉዳት ያስከትላል የሚል እምነት የነበረው መሆኑ እንደሆነ ግልፅ ሆነ። መስተካከል አለባቸው የሚላቸውንም ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝሮ አስቀመጠ። ኢህአዴግ በዚህ ላይ በመመስረት ወዲያውኑ መስተካከል የሚገባቸውን ነገሮች የሚያስተካክል እርምጃ በመውሰድ፣ በተራዘመ ሂደት የሚፈቱትን የሚፈቱበት ተጨባጭ አቅጣጫና እቅድ በመቀየስና ይህንኑ ለህዝቡ በማሳዬት፣ ትክክለኛ የሆኑትን ደግሞ ለምን ትክክለኛ እንደሆኑ ለህዝቡ ለማስረዳት ተንቀሳቀሰ። ኢህአዴግ የህዝቡን ድምፅ ለመስማት ዝግጁ እንደሆነና እንደአስፈላጊነቱም በዚያው ላይ ተመስርቶ አስፈላጊ ለውጦችን እንደሚያደርግ በተግባር ለህዝቡ ያረጋገጠበት እርምጃም ወሰደ።

ከዚህ ጋር በማያያዝ ለተቃዋሚዎች ድምፁን የሰጠው ህዝብ ድምፁ እንደማይቀማ ማረጋገጥ በዋነኛ ስልትነት ተቀምጦ ተግባራዊ ሆኗል። ተጭበረበረ የሚባለው ድምፅ የውጭ ታዛቢ ባለበት እንዲጣራ፣ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመጨረስ ኢህአዴግ ከመንገዱ ወጥቶ እንደሚንቀሳቀስ ህዝቡ በማያሻማ መንገድ እንዲገነዘብ ተደረገ። የማጣራት ስራ የተሰራውም ከተቃዋሚዎች ጋር ለመደራደር የተሞከረውም በዋነኛነት መራጩ ህዝብ በምርጫ ካርዱ ሃይለኛነት ላይ ያሳደረው ጠንካራና ትክክለኛ አቋም እንዳይሸረሸርና የተገኘው ታላቅ የዴሞክራሲ ድል ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ነበር።

የኢህአዴግ ትኩረት መሆን እንደሚገባው ሁሉ በህዝቡ ላይ የነበረ ቢሆንም የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮችና ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሃይሎችንና የውጭውን ህብረተሰብ ☞

የሚመለከትም ትክክለኛ ስልት አስቀምጧል። የተቃዋሚ ሃይሎች አመራሮች ከተቻለ አመፅ ከማካሄድ ወደኋላ እንደማይሉ ኢህአዴግ አንዳችም አይነት ጥርጣሬ አልነበረውም። ድምፁን የሰጣቸው ህዝብ የአመፅ ሃይል ስላልነበረ መብቱን በሰላማዊ መንገድ ያስከበረና ሊያስከብርም የሚፈልግ ስለነበረ ይኸው አቋም ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን እስከተጠበቀ ድረስ ተቃዋሚዎች ቢያምፁ እንደማያዋጣቸው ሊገነዘቡ ይችላሉ የሚል ግምት ግን ዝግ ሊደረግ የሚችል አልነበረም። በዚህ ላይ በመመስረት ከተቃዋሚዎች ጋር ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ዝግጁነት እንዳለ መግለፅ ከዚሁ ጐን ለጐን የህግ አስከባሪ ሃይሎች ተቃዋሚዎች በተናጠልም ሆነ ከሻእቢያ ጋር በመቀናጀት የሚሞክሩት አመፅ ካለ በእንጭጩ ለመቅጨት በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉም ተወስኖ ተግባራዊ ተደረገ።

ኢህአዴግ ከዚህ አኳያ የወሰዳቸው እርምጃዎች በተቃዋሚዎች ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤን የፈጠሩ አልነበሩም። የህዝቡን ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ለመመለስ እርምጃ መውሰዱ፣ ለድርድር ዝግጁ መሆኑ ወዘተ የመዳከም፣ የመፍራትና የመርበትበት ምልክቶች ተደርገው ነበር የተወሰዱት። የአመፅ አማራጭን ለማክሸፍ፣ ህዝቡን ወደትክክለኛ ጐራው በተቻለ ፍጥነት ለመመለስ የተወሰዱ ወቅታዊና ትክክለኛ እርምጃዎች ሳይሆኑ የሚያደርገውን ያጣ በመፍረክረክ ሂደት ላይ የሚገኝ ድርጅት የወሰዳቸው እርምጃዎች ተደርገው ነበር የታዩት።

የውጭ ሃይሎችን በተመለከተ ኢህአዴግ የወሰደው አቋም ሂደቱ ዴሞክራሲያዊና ትክክለኛ እንደነበር፣ ኢህአዴግ የህዝቡን ድምፅ ለማክበር (ለምሳሌ የአዲስ አበባን አስተዳደር ለተቃዋሚዎች ለማስረከብ ዝግጁ መሆኑን) ችግሮችን በሰከነና ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ፍላጐት እንዳለው በተግባር በማረጋገጥ በጐ ሚና እንዲኖራቸው ማበረታታት ይገባል የሚል ነበር። ዋናው ጉዳይ ከላይ የተጠቀሰው ሆኖ ሳለ ከዚህ አልፎ ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ተፅእኖ ከመጣ ምንም አይነት ተቀባይነት እንደማይኖረውና እርዳታና ብድር ቢቋረጥ ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ለመቋቋም የሚያስችል ዝግጅት እንዲደረግ ተወስኖ ተግባራዊ መሆን ቀጠለ።

## አመፁና መዘዙ

☞





ተቃዋሚ ድርጅቶች ገና ከመጀመሪያው በቀየሱት መንገድ መሰረት የአመፅ ሙከራ ከማድረግ አልተቆጠቡም። የአመፅ ሙከራውን በሚያካሂዱበት ወቅት ህዝቡ በተለይም የአዲስ አበባ ህዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ከጐናቸው እንደሚሰለፍ ገምተው ነበር። ጠንካራ የአመፅ ሙከራ ከተካሄደ ኢህአዴግ የውጭውን ተፅእኖ በመፍራት ይደራደራል፣ እጁን ይሰጣል፣ ምንም ቢሆን ጠንካራ የሃይል እርምጃ ለመውሰድ አይደፍርም ብለው ተማምነውም ነበር። በመጨረሻም የምእራቡ አለም በመሪዎቻችን ላይ እርምጃ ከተወሰደ ያስፈታናል፣ መንግስት የሃይል እርምጃ እንዳይወስድም ገትሮ ይይዝልናል የሚል ጠንካራ እምነት ይዘው ነበር። ከላይ የተጠቀሱትን እምነቶች በመያዝ ወደአመፅ ተግባር በሚገቡበት ወቅት አመፁ በእንጭጩ ተቀጭቶ ይሆናል ያሉት ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ ከፍተኛ ኪሳራ ደረሰባቸው።

ኢህአዴግ እንደገመተውና በትክክልም እንደገመገመው ህዝቡ የአመፅ ሃይል አለመሆኑን በተግባር አረጋገጠ። ኢህአዴግ እንደገመተው አንዳንድ ወጣቶች በትምህርት ቤትም ከዚያ ውጭም የተቃዋሚዎች ፀረ ሰላም ተግባር ሰለባ ቢሆኑም ወጣቱም ቢሆን ከዳር ዳር የተንቀሳቀሰበት ሁኔታ አልተፈጠረም። ለአመፅ ሙከራው መክሸፍ ዋነኛው ምክንያትም ይኸው ነበር። ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር ቢያጋጥም ኢህአዴግ ቀልድ እንደማያውቅ፣ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ህጋዊ እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ እንደማይልና ይህንን ለማድረግ ተፈላጊ ሆኖ የተገኘውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ በተግባር አረጋገጠ። የውጭ ሃይሎች ተቃዋሚዎች እንደገመቱትና እንደተመኙትም ባይሆን መሪዎቹን ለማስፈታት የመንግስትን ጠንካራ አቋም ለመቀየር ተንቀሳቅሰዋል፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ተፅእኖዎችም ለማሳረፍ ሞክረዋል። ኢህአዴግ ለዚሁ ተፅእኖ ሳይንበረከክ በአቋሙ ፀንቶ በመቆሙና በኢኮኖሚ መስክም ተዘጋጅቶ በመቆየት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ ፈጣን እድገቱ እንዲቀጥል በማድረጉ ከአመፅ አኳያ ሲታይ ተቃዋሚዎች ከውጭ ሃይሎች ምንም ነገር ተጨባጭ ጥቅም እንደማያገኙ ተደርጓል።

ያሰቡትና የገመቱት ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ አመፀኞቹ ሽንፈት ከተከናነቡ በኋላም ቢሆን ብዙዎቹ በጥፋት መንገዳቸው ቀጥለዋል። የቅንጅት ነውጠኛ አመራር፣ ኦነግ፣ አብነግና መሰሎቻቸው በሻእቢያ አስተባባሪነት ግንባር ፈጥረው ለመንቀሳቀስ እየሞከሩ ናቸው።

☞

ህዝቡ የአመፅ ሃይል አለመሆኑን በተግባር ባረጋገጠበት በአሁኑ ወቅት የሚከናወን የትጥቅ ፍልሚያ በዋነኛነት አንቀሳቃሾች ላይ የታጠረና ከሽብርተኝነት ሊያልፍ እንደማይችል ግልፅ ነው:: የህዝቡን የሰላምና የልማት ጥማት በመቃወም በጥፋት መንገድ መንቀሳቀሳቸውን እስከቀጠሉ ድረስ በነሱና ድምፁን በሰጣቸው ህዝብ መካከል ያለው ልዩነት በእጅጉ እየሰፋ እንደሚሄድና ኢህአዴግ በቀየሰው መንገድ በመንቀሳቀስ ህዝቡን ወደትክክለኛው ጐራው ለመመለስ የተመቻቸ ሁኔታ እንደሚፈጠር በተግባር በመታየት ላይ ነው:: በምርጫው ሂደት ተሚሙቆ የነበረው የዋነኛ አንቀሳቃሾቻቸው ስሜት ከአመፁ መክሸፍ ጋር ተያይዞ ተስፋ መቁረጥን አስከትሎ እንደለመዱት ብዙዎቹ አኩርፈው ዳር መቀመጥን እንደሚመርጡ በተግባር በማስመስከር ላይ ናቸው:: በመሆኑም በሻእቢያ አስተባባሪነት የጀመሩት ጉዞ እንኳን ህዝቡን በርካታ አንቀሳቃሾቻቸውንም ይዞ ለመራመድ የሚያስችላቸው ሆኖ አልተገኘም::

ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን የያዙትን ይዘው በሻእቢያ ዙሪያ መሰባሰባቸውም ቢሆን ዋጋ ያልከፈሉበት አልሆነም:: አሰላለፉ ጠርቶ በመውጣቱ አሰባሰብነው ያሉትን ሃይል የሚበትንባቸው ሊሆን እንደሚችልም በተግባር እየታየ ነው:: የቅንጅት ነውጠኞች በም-ርጫው ሂደት ከነበሩዋቸው ዋነኛ መፈክሮች አንዱ ኢህአዴግ ኤርትራን ለሻእቢያ ሸጧል፣ ከሻእቢያ ጋር ተሞዳሙዷል የሚል መፈክር ነበር:: በአሁኑ ሰአት ያንን ጩኸታቸውን ዋጥ አድርገው የሻእቢያ ቀጥተኛ ተላላኪዎች ሆነው መሰለፋቸው በትምክህተኛ አመለካከት የተወጠረውን አንቀሳቃሽ ሃይላቸውን በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ከትቶታል:: እርስ በርሱ እንዲናከስና አንዱ አንጃ በሌላው ላይ እንዲዘምት አድርጎታል:: እነዚህ ነውጠኞች ህገ መንግስቱን ከሚቃወሙባቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 የብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በማረጋገጥ ኢትዮጵያን ይበትናል የሚል ነበር:: አሁን ግን ያን ሁሉ ጩኸት ዋጥ አድርገው ኢትዮጵያን ለመበታተን ከተሰለፉ ሻእቢያ፣ ኦነግና ኦብነግ ጋር አብረው መሰለፋቸው የፈጠሩት ህብረት «የኢትዮጵያ» የሚል ቃል እንኳ እንዳይገባበት እነኦነግ በመቃወማቸው ይህንኑ ለመቀበል የተገደዱበት ሁኔታ መፈጠሩ እንደዚሁ የትምክህት ጐራን ክፉኛ ያወዛገበና የከፋፈለ ጉዳይ ሆኗል::

ህብረቱ በጠባቦቹ አካባቢም ተመሳሳይ ቀውስን አስከትሏል:: የነፍጠኛ ስርአትን ☞





አወግዛለሁ፣ ለብሄር ብሄረሰቦች መብት ቆሜያለሁ የሚለው ኦነግ የብሄሮችን መብት በአደባባይና በግልፅ ከሚቃወሙ ወገኖች ጋር ሆኖ ይህንኑ ህገ መንግስቱን ለመቃወም መሰለፉ በኦነግና መሰሎቹ ካምፕ ውስጥ ከፍተኛ ውዥንብርን አስከትሏል:: በሌላ አነጋገር ጠባቦችና ትምክህተኞች ግንባር ሲፈጥሩ አንዳንዴ ሁለት ሲደመርበት ሁለት አራት ወይም ከዚያ በላይ መሆኑ ቀርቶ ሁለት ወይም ከዚያ በታች እንደሚሆን በተግባር በመረጋገጥ ላይ ይገኛል:: ይህም ህብረታቸው አቅም ከሚጨምርላቸው ይልቅ ሊቀንስባቸው እንደሚችል ተግባራዊ ማረጋገጫ ነው::

እነዚህ የጥፋት ሃይሎች በሻእቢያ አስተባባሪነት በሽብር ተግባር ላይ በመሰማራት ሊያስከትሉት የሚችሉት ጉዳት የለም ባይባልም ይኸው ሂደት በኢትዮጵያ ፋይዳ ያለው የተቃውሞ የፖለቲካ ሃይል ሆነው የመውጣታቸውን እድል ክፉኛ እንደሚያጨልም ግልፅ ነው:: ህዝቡ ሰላምና ልማትን ሲፈልግ እነሱ የጥፋትና የሽብር መንገድ ይዘው በሚጓዙበት ወቅት ከህዝቡ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነው መቀጠላቸው አይቀሬ ነው:: ጠባቦችና ትምክህተኞች ስርአቱን ከመጥላት ውጭ ምንም አይነት የጋራ አቋምና አመለካከት ሳይኖራቸው የሚፈጥ-ሩት ህብረት የትምክህትና የጠባብነት ካምፖችን ውዥንብር ውስጥ ከቶ ከማዳከም አልፎ የሚያስገኝላቸው ጥንካሬ አይኖርም:: እናም ሂደቱ እንደፖለቲካ ሃይሎች የሚሚሸሹበት (marginalized) የሚሆኑበት ሂደት እንደሆነ በግልፅ ያመለክታል:: ኢህአዴግ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ጠንካራ የህዝብ ግንኙነት ስራ ከሰራ በነሱና በህዝቡ መካከል የማይታለፍ ጠንካራ አጥር መገንባት ይችላል::

ነውጠኞቹ ከላይ የተጠቀሰውን የሽብርና የፖለቲካ መሚሸሽ አቅጣጫ ይዘው በሚጓዙበት ወቅት ሌሎቹ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ አላማችንን እናራምዳለን ብለው ወደ ርላማም ገብተው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከኢህአዴግ ጋር እየተደራደሩ መስራት ጀምረዋል:: በሂደቱም ህገ መንግስቱንና የአገሪቱን ህጐች እንደሚያከብሩና እንደሚያስከብሩ ፈርመው በይፋ አውጀዋል:: እነዚህ ሃይሎች በይፋ የገለፁት ይኸው አቋም በበጐ ገፅታው የሚታይና በሂደትም ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሙሉ ልብ የተቀበለና የሚያከብር ተቃዋሚ ሊፈጠር የሚችልበትን መንገድ የሚያመላክት ነው ሊባል ይችላል::

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ ድርጅቶች የህገ ወጥ ትግል መስመርን ☞

ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እርግፍ አድርገው ትተውታል ብሎ በርግጠኝነት መናገር አይቻልም:: በውስጣቸው የአመፀኞቹ ደጋፊዎችና ተላላኪዎች እንዳሉ በየወቅቱ እየተገለጠ ያለ ጉዳይ ነው:: ህጋዊና ህገ ወጥ መንገድን እያጣቀሱ ከመሄድ ስልት አሁንም መቶ በመቶ እንዳልተላቀቁ የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ:: ዋናው ሃይላቸው ከአመፀኞቹ ጋር የነጐደውን ሃይል እንጅ ጠንካራ የሰላም አቋም ያለው ህዝብ አድርገው የማይወስዱና አቋሞቻቸውን ነውጠኞችን ለማስደሰት ቢያንስ ላለማስቀየም በሚያስችላቸው አኳኋን ከመቃኘት ሙሉ በሙሉ ነፃ እንዳልወጡ የሚያመለክቱ ነገሮች አሉ::

እነዚህ ሀይሎች በይፋ ባወጁት የሰላም መንገድ መራመዳቸው ለአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደትም ለራሳቸውም እንደሚበጅ ጥርጥር የለውም:: በምርጫው ያገኙትን ወንበር ይዘው በሰላማዊ ትግል በሂደት እየጐለበቱ የመሄድ እድል ይሰጣቸዋል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ በሰላማዊ ትግልና በአመፅ መካከል መንጠልጠልን ከመረጡ ግን ከምንም ሳይሆኑ ቀርተው በሁለት ወንበሮች መካከል ለመቀመጥ እንደሚፈልግ ሰው መውደቃቸው አይቀሬ ይሆናል:: ምርጫው የራሳቸው ቢሆንም ትክክለኛውን ምርጫ ቢወስዱ ለዴሞክራሲ ሂደታችን የማይናቅ አስተዋፅኦ ያበረክታልና ኢህአዴግም በአንድ በኩል የሰላም መንገዱን አጥብቀው እንዲይዙ የሚያበረታታ ስራ መስራት በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ህገ ወጥ ተግባር ሲገቡ ያለማመንታት በህጋዊ መንገድ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስድ ማሳዬት ይገባዋል::





# የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ

ከሐዋ ከድር

በአገራችን ውስጥ የሚካሄድ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንቅስቃሴ አስተማማኝ የሚሆነው የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶችና አገር ተረካቢ የሆኑትን ወጣቶች በበቂ ማሳተፍና ተጠቃሚ ማድረግ ሲችል ብቻ ነው:: እነዚህን የህ-ብረተሰብ ክፍሎች ወደ ጎን የተወ ማናቸውም አይነት ጥረት ግቡን ማሳካት አይችልም፤ የተወሰነ ውጤት ማስመዝገብ ቢችልም እንኳ ዘላቂነት አይኖረውም:: በልማቱም ሆነ በዴሞክራሲው መስክ ሴቶችንና ወጣቶችን ማሳተፍና ከሚገኘውም ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ መሰረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዳይ በመሆኑ በፅናት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል::

በአገራችን ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ ከሚገኘው የህዝብ ብዛት ግማሹን ቁጥር የሚይዙት ሴቶች እንደሆኑ ይታወቃል:: ይህ ማለት ደግሞ እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ህፃናት ግማሹ፣ ለስራ ብቁ ናቸው ከሚባሉት ከ14-64 እድሜ ያላቸው ዜጎችም ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ናቸው ማለት ነው:: ከብዛታቸው ሌላም ሴቶች በማህበረሰብም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ ይታወቃል:: በአገሪቱ በሚዘከሩ አኩሪ የታሪክ ምእራፎች ሁሉ ሴቶች ከወንዱ እኩል ተሳትፈዋል፤ በህብረተሰቡ ላይ በደረሱ ችግሮችም እኩል ተጠቂዎች ናቸው::

የአገራችን ሴቶች በአገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ በነበረው ፀረ ዴሞክራሲ ስርዓት በተነሳም ለድርብ ተቆና ተዳርገው ኖረዋል:: ስርዓቱ የወንዱን ፆታ የበላይ ስለደረገው ሴቶች በፆታ የበላይነቱ የተነሳ አድልዎና በደል ሲፈፀምባቸው ኖረዋል:: የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ማህበረሰቡን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመምከርና የመ-

☞

ወሰን መብት እንዳይኖራቸው ተከልክለው፤ በተለያዩ ጎጅ ባህላዊ አስተሳሰብና ድርጊት ሲጠቁ ኖረዋል፡፡

ሴቶች በአገሪቱ ውስጥ በሚኖር ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ የሰላም እጦት.....ወ.ዘ.ተ. ክፉኛ የሚጎዱ በመሆናቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረግ ጥረት ተጠቃሚዎች ስለሚሆኑ በእንቅስቃሴው ላይ ንቁ ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የአገራችን ሴቶች አስተማማኝ የለውጥ ሃይሎች እንደሆኑ በርግጠኝነት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ወጣቱንም ስንመለከት በህብረተሰቡ ውስጥ ካለው ልዩ ቦታ አኳያ በአሁኑ ወቅት አገራችን በተያያዘችው የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ከፍተኛ ተልእኮ ተሸክሞ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባው ይታመናል፡፡ ከማእከላዊ ስታስቲክስ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ከአገሪቱ ህዝብ 28% ያህሉ ወጣት (በአገሪቱ የወጣቶች ፖሊሲ መሰረት እድሜው ከ15-29 የሆነ) ነው፡፡ በምርት ተግባር ላይ ይሰማራል ከሚባለው ከ15-64 አመት እድሜ ክልል ከሚገኘው የአገራችን ህዝብ ደግሞ 49.2% ወጣት ሲሆን ይህም 87.7 % በገጠር 12.3% ደግሞ በከተማ ይኖራል፡፡

ከዚህ መረጃ ወጣቱ የአገሪቱን እድል በመወሰን ላይ ቁልፍ ሚና እንዳለው እንረዳለን፡፡ ወጣቱ በገጠር በግብርና ስራ፣ በከተሞች በተለያዩ ማምረቻ ድርጅቶች፣ በመንግስት መ/ቤቶችና በሌሎች መስኮች ተሰማርቶ በጉልበቱና በእውቀቱ አገሩን በማገልገል ላይ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ የማእከላዊ ስታስቲክሱ ሪፖርት እንደሚያመለክተው በከተሞች በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ምርታማ ዘርፎች ከተሰማራው አምራች ዜጋ ወጣቱ በቅደም ተከተል 67%ና 65% ድርሻ ይዞ የሚገኝ ሲሆን በገጠር በግብርና ስራ ተሰማርቶ ከሚገኘው ህዝብ ውስጥም ከግማሽ የሚልቀው ወጣት አርሶአደር ነው፤፡፡ በጠቅላላ በአገሪቱ በመንግስት መ/ቤቶች ተቀጥሮ ከሚሰራው ውስጥ 35.4%፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ከሚሰራው ደግሞ 40.5% ወጣት ነው፡፡





ወጣቱ ግን የልማት አቅም መሆን ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ውስጥ ባሉ ችግሮች ሁሉ ቅድሚያ ተጠቂም ነው፡፡ በሰላም እጦት የምርት ተግባር ሲስተጓጎል፤ የመማር፣ የመመራመር ሂደቱ ሲታወክ ወጣቱ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስበታል፡፡ በአገሪቱ የጦርነት አደጋ ሲያንዣብብ የድረስ ጥሪ የሚቀርበው ለወጣቱ፣ በጦርነቱ የሚጎዳውም ወጣቱ ነው፡፡ እንደ ኤች. አይ.ቪ. ኤድስ የመሳሰሉ ወረርሽኞች ኢላማቸው አድርገው የሚያጠቁት ወጣቱን፤ ከማንም በላይ ድህነት ጎጅውን የሚሰራውም በወጣቱ ላይ ነው፡፡ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ጥናት በአገራችን ካለው ስራ አጥ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ 67% ያህሉ ወጣት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ በሚከሰት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ችግሮች የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ ወጣቱ ትውልድ ነው፡፡

ስለሆነም ወጣቱም እንደሴቶች ሁሉ ወሳኝ የልማት አቅም ከመሆኑ ሌላ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መጠነ ሰፊ ችግሮች እንዲፈቱ ስለሚፈልግና በዚህም ተጠቃሚ ስለሚሆን በአገራችን የሚካሄድ የልማትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንቅስቃሴ ወጣቱን የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል፡፡ በአጠቃላይም በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄድ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ሴቶችና ወጣቶች ብቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቁልፍ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄ ሆኖ ይገኛል፡፡

በዚህ ረገድ እንደሌሎች የልማትና የደሞክራሲ ጥያቄዎች ሁሉ ባለፉት አመታት ሰፊ ስራዎች እንደተከናወኑና አበረታች ውጤቶችም እንደተገኙ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ ተጠቃሽ የሆኑ በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ ባለፉት ስርዓቶች በጦርነት ስትታመስ በነበረችው አገራችን ውስጥ ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል በከፋ ሁኔታ የችግሩ ሰለባ የነበሩት ሴቶችና ወጣቶች በመላ አገሪቱ ሰላም በመስፈኑ የላቀ ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ በሌላም በኩል ባለፉት 15 አመታት በገጠርም ሆነ በከተሞች ከተካሄዱት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችም ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆኑበት ሁኔታ መኖሩ

የሚካድ አይደለም፡፡

ሴቶችን በሚመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ የእኩልነት ጥያቄያቸው ህገመንግስታዊ ዋስትና አግኝቷል፤ አገራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ እንዲሁም ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገ የቤተሰብ ህግ ወጥተው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ በየደረጃው ባሉ ህግ አውጪና አስፈፃሚ አካላት በተለያየ የሃላፊነት ቦታ የሴቶች ተሳትፎ በየጊዜው እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት በፌዴራል ርላማ 29%፣ በክልል ምክርቤቶች በአማካይ 40%፣ በወረዳዎች ደግሞ ከ30 % የሚሆነው የህዝብ ተወካዮች መቀመጫ በሴቶች የተያዘበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ ሴቶች በአገራቸውና በየአካባቢያቸው የሚኖራቸውን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ በኩል መልካም ጅምር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በልማቱም መስክ የሴቶችን ችግሮች መፍታት ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የግብርናና የከተማ ልማት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም የሴቶች ገቢና ኢኮኖሚያዊ ህይወት እድገት ማሳየት ጀምሯል፡፡ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶችም ጥሩ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ገበታ ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ በ1ኛ ደረጃ 45%፣ በሁለተኛ ደረጃ 35%፣ በከፍተኛ ትምህርት ደግሞ 22% ሴቶች እንደሆኑ ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በጤና አገልግሎት በኩልም በገጠርና በከተሞች በመሰፋፋት ላይ የሚገኙ ሴቶች ተኮር የሆኑ የክትባት አገልግሎቶች በስፋት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔና የስነተዋልዶ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ብዛት ከአመት አመት እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በሌላም በኩል በገጠርና በከተሞች በመገንባት ላይ ያሉት የመሰረተ ልማቶች የሴቶችን የስራ ሸክም በማቃለል ረገድ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በተለይም ደግሞ በገጠር የተካሄዱት የንፁህ መጠጥ ውሃ ግንባታዎች ረጅም ርቀት ተጉዛ ውሃ ከወንዝ ስትቀዳ የነበረችዋን የገጠሯን ሴት ድካም በማቃለል በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በወጣቶች በኩልም በአገሪቱ በሚካሄድ የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም

☞





እንቅስቃሴዎች ወጣቶች የሚኖራቸውን ሚናና ከዚህም ሊያገኙት የሚገባውን ጥቅም አስመልክቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አገራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ወጥቷል፡፡ ባለፉት 15 አመታት ውስጥ በአገራችን ከፍተኛ እድገት የተመዘገበበት የትምህርት አገልግሎት ከሁሉ አስቀድሞ ተጠቃሚ ያደረገው ወጣቱን ነው፡፡ በሁሉም የትምህርት ደረጃ በተለይም ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ፣ በቴክኒክና ሙያና በከፍተኛ ትምህርት ረገድ የታየው ሰፊ እድገት ወጣቱ በእውቀትና በክህሎት እንዲበለፅግና የተሻለ ኑሮ እንዲኖር በር ከፍቶለታል፡፡ በየአመቱ ከቴክኒክና ሙያና ከከፍተኛ ትምህርት እየተመረቁ ወደ ስራ አለም የሚሰማሩ ወጣቶች ቁጥር እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በጤና አገልግሎት መስክም ወጣቱ ተጠቃሚ የሆነባቸው በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በአጠቃላይም በአገሪቱ ውስጥ በመመዝገብ ላይ የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ እድገት ወጣቱ ሰፊ የስራ እድል እንዲያገኝ፣ በተለያዩ መስኮች ተሰማርቶ ኑሮውን እንዲያሻሽል ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል፡፡

እንደነዚህ አይነት ከአመት አመት መሻሻል የሚታይበት ሁኔታም ቢኖርም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት አይቻልም፡፡ ቀደም ሲል በተለያዩ አካላት የተካሄዱትም ሆነ በቅርቡ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአማራና በትግራይ ክልል የተካሄዱት ጥናቶች በገጠርም ሆነ በከተሞች የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶች ከፍተኛ ችግሮች እንዳሉባቸው ያስረዳሉ፡፡ በሴቶችና በወጣቶች ኢኮኖሚና ማህበራዊ ህይወት ላይ መሰረታዊ ለውጥ አልመጣም፣ አሁንም የስራ አጥነትና አስተማማኝ የገቢ እጦት ችግሮች በስፋት አሉባቸው፡፡ በፖለቲካው መስክም በሚፈለገው መጠን የሚሳተፉበት ሁኔታ ገና አልተፈጠረም፡፡ ከነዚህ በመነሳትም ተስፋ የመቁረጥና የመገለል ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡

እነዚህ ችግሮች በጊዜ እስካልተፈቱ ድረስ ተስፋ ቆራተነቱና የባይተዋርነቱ አስተሳሰብ እየተባባሰ ይሄዳል፤ የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያላረጋገጠ

☞

የልማትና የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ለድል መብቃት ስለማይችልም በአገራችን የተጀመረው የእድገት ጉዞ መሰናከሉና መውደቁ የማይቀር ይሆናል። ስለሆነም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙ ሴቶችንና ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መፍታት ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ሆኖ ይገኛል። ከዚህ አኳያ ሲታይ በመንግስት በኩል በቅርቡ የሴቶችና የወጣቶች የእድገትና የለውጥ ኬጅ እንደዲዘጋጅ መደረጉ አንድ ታላቅ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ይሆናል።

ኬጁ የተዘጋጀው በፌዴራል የሴቶች ጉዳይና የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትሮች አማካይነት ሲሆን ሌሎች አግባብ ያላቸው ሚኒስትሮችና የተለያዩ የፌደራል መ/ቤቶች እንዲሁም የክልል ሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎችም ከጥናቱ ጀምሮ እስከ የኬጅ ቀረፃው ድረስ ተሳትፈውበታል። በአገራችን ውስጥ ለሴቶችና ወጣቶችን የተለየ ትኩረት በመስጠት ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ዝርዝር አቅጣጫ ሲቀየስ ይህ የመጀመሪያው በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል።

## የሴቶችና የወጣቶች
## የእድገትና የለውጥ ኬጁ መሰረታዊ ይዘት

ኬጁ ለሴቶችና ለወጣቶች ተለያይቶ የተዘጋጀ ሲሆን በጥቅሉ ሲታይ ዋነኛ አላማው በገጠርና በከተማ ያሉ ሴቶችና ወጣቶች በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በብቃት ተሳታፊና ከውጤቱም ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማረጋገጥ እንደሆነ እንገነዘባለን። በሌላ አባባል ኬጁ የሴቶችንና የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት የተነደፈ የድርጊት

☞





መርሃ ግብር ነው ማለት ይቻላል።

በኬጁ በዝርዝር የተመለከቱት ተግባራት ቀደም ሲል በተለያዩ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ላይ ሲነሱ የነበሩ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ የሴቶችንና የወጣቶችን ችግሮች ከመፍታት አኳያ ተቃኝተውና እንደ አንድ ኘሮግራም ተቀርፀው የቀረቡ በመሆናቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታመናል። የተዘጋጀው ኬጅ እንደ የድርጊት መርሃግብርነቱ በቀጣይ በየደረጃው እየተዘረዘረ ስራ ላይ እንደሚውል የሚጠበቅ ቢሆንም በኬጁ የተመለከቱትን ዋና ዋና ተግባራት እዚህ ላይ ማንሳት ስለ ኬጁ ይዘት ለመረዳት አስፈላጊ ይሆናል። ኬጁ በገጠር የሚኖሩ ሴቶችና ወጣቶች ያሉባቸው ችግሮች በከተማ ከሚኖሩት የሚለይበት ባህሪ እንዳለ ግምት ውስጥ በማስገባት ከየችግሩ አኳያ ለያይቶ ለማቅረብ ይሞክራል።

በገጠር በኢኮኖሚው መስክ የሴቶችንና የወጣቶችን የመሬት ተጠቃሚነት ዋስትና የማረጋገጥ፣ ሴቶችና ወጣቶች ከግብርና ውተ ባሉ የእደ ጥበብ፣ አነስተኛ የንግድ ስራ በመሳሰሉ መስኮች በመሰማራት ገቢያቸውን የሚያሳድጉበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ አጠናክሮ መቀጠል፣ ለዚህም የሚያስፈልግ የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ ሴቶችና ወጣቶች የኤክስቴንሽን፣ የግብይት ስርዓትና የገጠር ፋይናንስ...... አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ በኬጁ ተቀምጧል።

በማህበራዊ መስክም የገጠር ሴቶችና ወጣቶች የትምህርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲጎለብት፣ መከላከልን ማእከል ባደረገው የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑና በኤች. አይ.ቪ. ኤድስና በስነተዋልዶ በመሳሰሉት ሴቶችንና ወጣቶችን በሚመለከቱ ችግሮች ላይ ለውጥ የሚያመጡ ስራዎች በትኩረት እንዲሰሩ፤ የገጠር ሴቶችን የስራ ጫና የሚያቃልሉ የተለያዩ ኘሮግራሞች እንዲተገበሩ፤ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ፣.... ለማድረግ የሚያስችሉ ዘርዘር ያሉ ተግባራት በኬጁ ተመልክተዋል።

በፖለቲካዊ መስክ የገጠር ሴቶችና ወጣቶች በማህበራት ተደራጅተው ጥቅማቸውን ለማስከበር መንቀሳቀስ እንዲችሉ፤ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላት ውስጥ ሴቶችና

☞

ወጣቶች በአመራር ሰጭነት የሚኖራቸው ተሳትፎ እንዲጎለብት ማድረግ የመሳሰሉ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በከተሞችም በተመሳሳይ መንገድ የሴቶችንና ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራት ተመልክተዋል፡፡ በተለይም በኢኮኖሚው መስክ ስራ አጥነትን ለማቃለል የሚያስችሉ የስልጠናና የስራ ፈጣሪነት አቅጣጫዎች ተቀይሰዋል፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የሚስፋፉበትና በመስኩ እስካሁን የነበሩባቸው ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ተቀምጧል፡፡ በማህበራዊ መስኩም በትምህርትና በጤና የሚሰራው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የከተማ ወጣቶችን የመዝናኛ ፍላጎት ለማሟላትና ወጣቱ ከመጥፎ ሱሶችና ድርጊቶች እንዲርቅ ለማድረግ የሚያስችሉ ኘሮግራሞች ዘርዘር ብለው ቀርበዋል፡፡ በፖለቲካዊ መስኩም እንደገጠሩ ሁሉ የወጣቶች የተደራጀ እንቅስቃሴና የአመራር ሰጭነት ተሳትፎቸው የሚጠናከርበት መንገድ እንዲኖር የሚያደርጉ ተግባራት በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

በኬጁ የተካተቱት ተግባራት ግልፅ አላማ፣ ግብና የአፈፃፀም አቅጣጫ የተቀመጠላቸው ቢሆኑም በተሟላ መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሰፊ ዝግጅትን ይጠይቃሉ፡፡ በየትኛውም ህብረተሰብ የለውጥና እድገት አላማ ያለው ፕሮግራም ስለወጣ ብቻ የሚፈለገው ለውጥ ይሳካል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የማንኛውም ፕሮግራም ስኬት ሊረጋገጥ የሚችለው በአስተማማኝ አኳኋን በተግባር ላይ የሚውልበት ሁኔታ ሲፈጠር እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ኬጅ መዘጋጀቱ እስከዛሬ የነበረውን ችግር ለመፍታት በጎ ጅምር ቢሆንም በኬጁ የተመለከቱትን ተግባራት በተሟላ መንገድ ስራ ላይ በማዋል የአገራችን ሴቶችና ወጣቶች በኢኮኖማያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑበት የበለፀገ ህብረተሰብ ተገንብቶ የማየትን ራእይ እውን ማድረግ ይገባል፡፡ ኬጁን በፍጥነትና በጥራት እንዲፈፀም በአስፈላጊው መስክ ሁሉ ብቁ እንቅስቃሴ ሊደረግ ይገባል፡፡

☞





በተለይም ከራሳችን ልምድ ስንነሳ በኢህአዴግም ሆነ በመንግስት ደረጃ እስካሁን የኘሮግራም፣ የእቅድ፣ የአቅጣጫ፣ የስትራተጅ..... ችግሮች አልነበሩም፣ አሁንም ጭራሹን የሉም ባይባልም በአፈፃፀም ላይ ግን ከፍተኛ ችግር እንደነበር አሁንም ቢሆን ችግሩን በሚገባ ተሻግረነዋል ማለት እንደማይቻል የሚያከራክር አይሆንም፡፡ በአፈፃፀም ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በተሟላ መንገድ መፍታት እስካልተቻለ ድረስ አሁን የተዘጋጀውን የሴቶችና የወጣቶች ኬጅ ስራ ላይ ማዋልና የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ለዚህ ደግሞ ኬጁን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ሚና ያላቸው ፈፃሚ አካላት በሙሉ በጊዜ የሚጠበቅባቸውን ዝግጅት በማሟላት ወደ ተግባር መገባት ይጠበቅባቸዋል፤ ወሳኙ ጉዳይ ተግባር ነውና፡፡ ምንም እንኳ አሁን የተዘጋጀው ኬጅ በአይነቱ ለየት ያለና በሴቶችና በወጣቶች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በተሟላ መንገድ ለመፍታት በሚያስችል አኳኋን የቀረበ ቢሆንም በፍጥነት በተግባር ላይ መዋል ካልቻለ ባለፉት ጊዜያት ሲሰጡ ከነበሩት ግን ደግሞ ስራ ላይ ካልዋሉት ባዶ ተስፋዎች የተለየ እጣ ፈንታ አይኖረውም፡፡ በዚያው መጠንም የሴቶችንና የወጣቶችን ተስፋ ቆራጭነት የሚያጠናክር ይሆናል፡፡ ስለሆነም በየክልሎች የተጀመረው ዝግጅት በፍጥነት መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ የጊዜ ጉዳይ የህልውና ጉዳይ የመሆኑ ሃቅ በአሁኑ ወቅት ከማንም በላይ ሴቶችና ወጣቶችን ሳይውል ሳያድር በልማቱና በመልካም አስተዳደር መስክ በብቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ወይም ባለማድረግ የሚገፅ እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባ ይሆናል፡፡

ስራው በዋነኛነት የሚሰራው ሴቶችና ወጣቶች በሚኖሩበት በቀበሌ ደረጃ በመሆኑ በፍጥነት ኬጁ ወደ ታች መውረድና በአጠቃላይ ምልዓተ ህዝቡ በተለይም ደግሞ ሴቶችና ወጣቶች በጉዳዩ ላይ እንዲመክሩበት ማድረግ፤ ለተግባራዊነቱም ሁሉም የየበኩላቸውን ሚና ለመወጣት በብቃት የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

☞

## ኬጄን በመተግበር ረገድ
## ከሴቶችና ከወጣቶች ምን ይጠበቃል?

የአገራችን ሴቶችና ወጣቶች አሁን ለሚገኙበት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግር የዳረጋቸው መሰረታዊ ምክንያት ችግሮቹን ለመፍታት በቂ ጥረት አለመደረጉ ብቻ ሳይሆን ዋነኛው ራሳቸው ሴቶችንና ወጣቶች ያሳተፈ የመፍትሄ አቅጣጫ ባለመኖሩ ነው፡፡ የሴቶችና የወጣቶችን ችግር ለማቃለል የሚፈልግ፣ ችግሮቹን መፍታት የሚያስችል አላማና የድርጊት ኘሮግራም አለኝ የሚል ማናቸው አካል በርግጥም ለጉዳዩ በፅናት መነሳቱ ከሚረጋገጥባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንድና ዋነኛው የጉዳዩ  ባለቤቶች የሆኑትን ሴቶችና ወጣቶችን የመፍትሄው አካል አድርጓል ወይ የሚለው ይሆናል፡፡ ራሱን የሴቶችና ወጣቶች ሞግዚት አድርጎ ችግራቸውን እፈታለሁ የሚል እሱ ሃሳዊ መሲህ ከመሆን ዘሎ የለውጥ ሃይል ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ ኬጁን በመተግበር ረገድ ግልፅ ስትራተጅ መከተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ኬጄ ተግባራቱን ብቻ ሳይሆን ችግሩን በመፍታት በኩል ሊኖር የሚገባውን ስትራተጅ፣ ተግባራቱን በመፈፀም በኩል ዋነኛና ደጋፊ ሚና ያላቸውን ሃይሎች ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህም በየፈርጁ ችግሮቹን ለመፍታት ዋነኛ ሃይሎች ራሳቸው ሴቶችና ወጣቶች እንደሆኑ በማያሻማ መንገድ ተቀምጧል፡፡

ሴቶችና ወጣቶች ኬጁን በመተግበር ሂደት ላይ በብቃት መሳተፍ ይችሉ ዘንድ ከሁሉ አስቀድሞ በራሳቸው ተሳትፎ ላይ በቂ ግንዛቤ የሚይዙበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ ችግሩን ሌላ አካል እንዲፈታላቸው ከመጠበቅ የተረጅነት አስተሳሰብ ሊላቀቁ ይገባል፡፡ ለዚህም ሴቶችና ወጣቶች የሚሳተፉባቸው የተለያዩ መድረኮች እንዲዘጋጁ ማድረግና በችግሮቹና በመፍትሄዎቻቸው ላይ በዝርዝር የሚመክሩበት ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በችግሮቻቸው ምንነትና የአፈታት መንገዱ ላይ የሚደርሱበትን መግባባት መሰረት  በማድረግ ወደ ተግባር መግባት ይችሉ ዘንድም

☞





ራሳቸውን ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በእርግጥም የሴቶችና የወጣቶችን ችግር ማቃለል የሚቻለው ሴቶችና ወጣቶች የመፍትሄው አካል ሆነው ሲንቀሳቀሱ ነው፡፡ በኬጄ የተዘረዘሩ ተግባራትን በማከናወን በኩል ከራሳቸው ከሴቶችና ወጣቶች የተሻለ ውጤታማ መሆን የሚችል አካል የለም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡ ከሴቶችና ወጣቶች ውጭ ያሉ አካላት በሙሉ የደጋፊነት ሚና ብቻ ነው መጫወት የሚችሉት፡፡ ኬጄ ይህንንም በማያሻማ አኳኋን አስቀምጦአል፡፡ ከደጋፊ አካላትም ውስጥ ዋነኛው መንግስት ሲሆን የእሱም ድርሻ ውሱን ከመሆን የሚያልፍ አይደለም፡፡ ከመንግስት አንፃር ሲታይ ሌሎች አካላት በኬጄ አፈፃፀም ላይ የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ብዙም ትርጉም የሚኖረው አይሆንም፡፡

ስለሆነም ኬጄን በመተግበር፣ ችግሮቻቸውን በመፍታት በኩል ወሳኝ ሚና ያላቸው ራሳቸው ሴቶችና ወጣቶች እንደሆኑ በመገንዘብ ለኬጄ ተግባራዊነት በባለቤትነት መን-ቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከሁሉ አስቀድሞ ኬጄን ማወቅ፣ በኬጄ ላይ በቂ ውይይት በማድረግ ሊሻሻል፣ ሊታከል ወይም ሊቀየር በሚገባው ጉዳይ ላይ በንቃት በመሳተፍ ኬጄን ማዳበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በአጠቃላይ ከሁሉም ሴቶችና ወጣቶች በተለይም ደግሞ ከምሁራን ሴቶችና ወጣቶች ሰፊ ተሳትፎ ይጠበቃል፡፡

በዚህ ረገድ የአገራችን ምሁራን፣ ሴቶችና ወጣቶች ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በራሳቸው ጉዳይ ላይ ለመምከርና ለወገኖቻቸው  ሙያዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት አመቺ ሁኔታ መፈጠሩን በማስተዋል ይህንን እድል ለመጠቀም መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዳር ላይ ቆሞ ችግሮች ለምን ተፈጠሩ ብሎ በመቆጨት፣ ሊሰሩ ሲገባቸው ባልተሰሩ ጉዳዮች ላይ ከርቀት አስተያየት በመስጠት የሚያመጡት ለውጥ እንደሌለ በመገንዘብ ራሳቸውን በተግባር ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት አካል ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

መንግስት እንደ ዋነኛው ደጋፊ ሃይል አመቺ ፖሊሲና ህጎችን በማውጣት፣ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት.....በመሳሰሉት መስኮች እገዛ ያደርጋል፡፡

☞

ፈረስ ያደርሳል እንጂ..... እንዲሉ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች በብቃት መሳተፍና ያሉባቸውን ችግሮች በመፍታት ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን በማድረግም በርግጥም የአገራችን ሴቶችና ወጣቶች በአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅቃሴ ብቁ ተሳታፊና ከውጤቱም ተጠቃሚነታቸው እንደሚረጋገጥ አጠራጣሪ አይሆንም፡፡🖉





# የፀረ-ሽብርተኝነት ትግሉና የሃይሎች አሰላለፍ በሶማሊያ

ከታደሰ ገ/ወልድ

ባለፉት ጥቂት ወራት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህብረት የተባለው ስብስብ ሞቃዲሾንና አካባቢዋን በቁጥጥር ስር በማድረግ መላ ሶማሊያን የመቆጣጠር ፍላጐት ከማሳየቱ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን አገሮች ጨምሮ መላውን የአለም ህብረተሰብ ያሳሰበ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ይህንን ክስተት ለመረዳት በሶማሊያ ያለውን የሃይል አሰላለፍ፣ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ድል ከምን እንደመነጨ፣ የአለም ህብረተሰብ በሶማሊያ ጉዳይ ላይ እየወሰደ ያለውን አቋምና፣ እነዚህ ጉዳዮች በአገራችን ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖና የኢትዮጵያን ፖሊሲ ደረጃ በደረጃ ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

## 1. የሃይሎች አሰላለፍ በሶማሊያ

በሶማሊያ የሚታየው የሃይሎች አሰላለፍ እጅግ ውስብስብና በየጊዜው የሚቀያየር ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መላ ሶማሊያንና እያንዳንዱን ሃይል የሚሸፍን ትንተና ማቅረብ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ይገኛል፡፡ የሶማሊያን የፖለቲካ ሂደት በሚገባ ለመረዳት ዋና ዋና ሃይሎችንና ማእከላቱን ብቻ ማየት በቂ ስለሆነ ፅሁፉ በነዚህ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

### 1.1. የሶማሊያ የሽግግር መንግስት

የኢጋድ አገሮች በአለም ህብረተሰብ ድጋፍ ለበርካታ አመታት ያደረጉት የሰላም ጥረት ተሳክቶ የሚበዙትን የሶማሊያ ጐሳዎችና በነዚህ ዙሪያ የተደራጁትን የታጠቁ

☞

ሃይሎች ያካተተ የሽግግር መንግስት ከሁለት አመታት በፊት ተቋቁሟል፡፡ ይህ መንግስት በአሁኑ ወቅት የመላው የአለም ህብረተሰብ እውቅናና በተወሰነ ደረጃም ድጋፍ የተቸረው በመሆኑ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ አቅም ያለው መንግስት ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሽግግር መንግስቱ የራሱን የሆነ የተጠናከረ የመከላከያና የፖሊስ አቅም ስላልገነባ፣ ይህ ነው የሚባል የገቢ ምንጭ የሌለውና እስካሁን ድረስ ከተስፋ ያለፈ ተጨባጭ የኢኮኖሚ እርዳታ የማያገኝ በመሆኑ፣ እንዲሁም በሽግግር መንግስቱ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሃይሎች ከርስ በርስ ሽኩቻ ነፃ ስላልሆኑ ደካማ የፀጥታ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መሰረት ያለው መንግስት ሆኖ ይታያል፡፡

በሶማሊያ ዋና ከተማ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የጦር አበጋዞች የሽግግሩ መንግስት አባላት የነበሩ ቢሆኑም ከመንግስቱ አፈንግጠው የራሳቸውን እቅድ ነድፈው ሲንቀሳቀሱ በመቆየታቸው በዋናው ከተማ የቆየው የተጠናከረ የአክራሪዎች እንቅስቃሴ የሽግግር መንግስቱን ወደ ሞቃዲሾ ሊያስገባ የሚያስችል ስላልነበረ የሽግግር መንግስቱ ጊዜያዊ ዋና ከተማ በመጀመሪያ ወደ ሞቃዲሾ በተጠጋች ጆሃር በተባለች ከተማ ቀጥሎም ከሞቃዲሸ ራቅ ወዳለች ባይዳዋ በምትባል ከተማ የሆነበት ሁኔታ መፈጠሩ የድክመቱ አንድ መገለጫ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሽግግር መንግስቱ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ባሉበት ወቅት ለተወሰኑ ወራት በስደት ከተቀመጠበት ናይሮቢ ከተማ ተነስቶ በሶማሊያ ውስጥ በቋሚነት መቀመጥ መቻሉ እንደ አንድ ጠንካራ ጐን ይታያል፡፡

### 1.2 የሶማሊላንድ አስተዳደር

በቅኝ አገዛዝ ዘመን ሶማሊያ ሁለት ቅኝ ገዥዎች ተከፋፍለው የተቆጣጠሯት አገር ነበረች፡፡ በዚህ መሰረት ሰሜን ሶማሊያ በእንግሊዞች ቅኝ አገዛዝ ስር የነበረች ሲሆን የተቀረው የሶማሊያ ግዛት በጣሊያኖች ቁጥጥር ስር ነበር፡፡ ቅኝ አገዛዝ ሲወገድም ሰሜን ሶማሊያ በጥቂት ሳምንታት ቀድማ ነፃ የወጣች ሲሆን ሁለቱ ክፍሎች ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲዋሃዱ

☞





ተወስኖ አንድ አገር ለመሆን በቁ፡፡ በሲያድ ባሬ አገዛዝ ወቅት በመንግስቱ ላይ በቅድሚያ ያመፀው አካባቢ ይኸው የሰሜን ሶማሊያ አካባቢ ሲሆን፣ የሲያድ ባሬ መንግስት ሲወድቅም የአካባቢው ህዝብ ወዲያውኑ ነፃነቱን አወጀ፡፡ አሁን ሶማሊላንድ በሚል ስም ራሱን በራሱ በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ እጅግ የሚበዛው የአካባቢው ህዝብ ከቀረው የሶማሊያ ክፍል ጋር አብሮ መኖርን እንደማይፈልግ በተለያዩ አጋጣሚዎች አረጋግጧል፡፡

የሶማሊላንድ አስተዳደር ባለፉት 10 አመታት ከየትኛውም የሶማሊያ አካባቢ በተሻለ ሁኔታ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት፣ ተደጋጋሚ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች የተካሄዱበት፣ ኢኮኖሚው በአብዛኛው በውጭ የሚኖሩ የአካባቢው ተወላጆች በሚልኩት ገንዘብና ከኢትዮጵያ ጋር ባለው የድንበር ንግድ ላይ ተመስርቶ ያንሰራራበት ሁኔታ በመፈጠሩ በብዙ ታዛቢዎች ዘንድ መልካም ስምና ዝናን አግኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢውን ነፃነት የተቀበለ መንግስትም ሆነ አለም አቀፍ ድርጅት ስለሌለ በኢኮኖሚና በዲፕሎማሲ መስክ እርዳታን ለማግኘት ሳይችል ቀርቷል፡፡ ከሶማሊያ መንግስት ጋር በሚደረግ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር የአለም ህብረተሰብ ነፃነቱን ለመቀበል ዝግጁ ሆኖ ባለመገኘቱ፣ በሶማሊያ የተቋቋመ ጠንካራ ማእከላዊ መንግስትም የሌለ በመሆኑ የአካባቢው ነፃነት እንደተንጠለጠለ መቆየቱ እንደ ደካማ ጐን የሚታይ ሆኗል፡፡ በአቅራቢያው ከሚገኝ የፑንትላንድ አስተዳደር ጋር የድንበር ውዝግብ ያለው መሆኑና በምስጢር የተደራጁ አክራሪዎች የሚፈታተኑት መሆኑም ሌላው ደካማ ጐኑ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አካባቢ በተግባር እንደነፃ መንግስት እየሰራ ያለና በሽግግሩ መንግስትም ውስጥ ያልተወከለ አካባቢ ነው፡፡ በበርካታ ታዛቢዎች ዘንድ በሶማሊያ የሰላምና የዴሞክራሲ ሞዴል ተብሎ የሚወሰድ በሌላው የሶማሊያ አካባቢ በሚካሄዱት ቀጣይ ውዝግቦች ተሳታፊ ያልሆነ አካባቢ ነው፡፡

### 1.3 የፑንትላንድ አስተዳደር

የፑንትላንድ አካባቢ ህዝብም ከሶማሊላንድ ህዝብ ቀጥሎ በሲያድ ባሬ መንግስት ላይ ያመፀ በአሁኑ ጊዜም የራሱን ጊዜያዊ አስተዳደር መስርቶ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ህዝብ

☞

ነው፡፡ ከሶማሊላንድ የሚለየው ነገር ቢኖር ከሌላው የሶማሊያ አካባቢ ጋር በፌዴሬሽን ወይም በኮንፌዴሬሽን ተባብሮ መኖር የሚፈልግ መሆኑና በሽግግር መንግስቱ ውስጥ መወከሉ ነው፡፡ ይልቁንም የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት የዚሁ አካባቢ ተወላጅና ከዚህ ቀደም የፑንትላንድ አስተዳዳሪ የነበሩ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ይህ አካባቢ የሽግግር መንግስቱ ጠንካራ መሰረት ያለበት አካባቢ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይሁንና የሽግግር መንግስቱ ጊዜያዊ ዋና ከተማውን ከፑንትላንድ ርቆ የመሰረተ በመሆኑና የፑንትላንድ አስተዳደር ሰፊ ውስጣዊ ነፃነቱን አሳልፎ ለመስጠት የቸኮለበት ሁኔታ ስለማይታይ አካባቢው ከሽግግር መንግስቱ ጋር ጠንካራ ተቋማዊ ትስስር ፈጥሯል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ፑንትላንድ በአንፃራዊነት የተረጋጋ አካባቢ ቢሆንም ከሶማሊላንድ ጋር የድንበር ውዝግብ ያለው መሆኑና በህቡዕ የተደራጁ የአሸባሪ ሃይሎች የሚፈታተኑት አካባቢም ነው፡፡

### 1.4 የሞቃዲሾ ሃይሎች

በሞቃዲሾ የሚገኘው የሃይሎች አሰላለፍ ከየትኛውም የሶማሊያ አካባቢ በባሰ ሁኔታ የተወሳሰበ ነው፡፡ የሲያድ ባሬ መንግስት መገርሰስን ተከትሎ ከተማዋ የተለያዩ ንኡሰ ጐሳዎችን መሰረት ባደረጉ የጦር አበጋዞች ተከፋፍላለች፡፡ በአካባቢው የነበረውን የተለያዩ ሰዎች ንብረት ወርሶ በመያዝ የከበሩ ነጋዴዎችና ንብረት ሳይወርሱ የከበሩ ነጋዴዎችም የየራሳቸው ታጣቂ ሃይል አደራጅተው ከተማዋንና አካባቢውን ከፋፍለው ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡ ስራ አጡን ወጣት በጫት በመደለል በታጣቂነት አሰልፈው እጅግ የሚዘገንን ጋጠ ወጥ ስራ በህዝቡ ላይ ሲፈፅሙ ኖረዋል፡፡ ህዝቡም ከጊዜ ወደ ጊዜ በነዚህ ሃይሎች ላይ ያለው ምሬትና ተቃውሞ እየጨመረ ሄዷል፡፡

የሞቃዲሾ ስርአት አልበኝነት እየተባባሰበት በሄደ መጠን አንዳንድ የአካባቢው የሃይማኖት መሪዎች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ሰላምና የህግ የበላይነትን ለማስፈን ሞክረዋል፡፡ ከመካከለኛው ምስራቅ በሚያገኙት ገንዘብ በመታገዝ የትምህርትና (በዋናነት

☞





የሃይማኖት ትምህርት) የጤና አገልግሎት ለመስጠትም ሞክረዋል፡፡ በዚሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የህዝቡን ድጋፍ እያገኙ በመሄዳቸው ፍርድ ቤቶች የራሳቸውን ሚሊሽያ በማቋቋም የቁጥጥር አድማሳቸውን ለማስፋት የሚንቀሳቀሱ ሆነዋል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖም ከሚሰጣቸው የገንዘብ እርዳታ ጋር ተያይዞ ከሶማሌ ህዝብ ሃይማኖታዊ እምነት ጋር የማይሄዱ የአክራሪ እስልምና አመለካከት እየተስፋፉ ሄዷል፡፡ በሸሪዓ ላይ የተመሰረተ እስላማዊ መንግስት በሶማሊያ መቋቋም አለበት የሚል አመለካከት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ አካባቢ ስር እየሰደደም መጥቷል፡፡

በዚሁ ሂደት አልኢታሃድ አል እስላሚ የተባለ አከራሪ ድርጅት ተቋቁሞ በሶማሊያና በኢትዮጵያ የሽብር ተግባራት ሲያከናውንና ከአለም አቀፍ አሸባሪ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የዛሬ አስር አመት ገደማ በኢትዮጵያና ሶማሊያ ድንበር መሽጐ፣ በአፍጋኒስታን ከሶቭየቶች ጋር ሲዋጉ የነበሩ አፍጋን አረቦች እየተባሉ ከሚታወቁ ሽብርተኞች የመጡ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸውን ሰዎች አሰልፎ አገራችንን ለማተራመስ ተንቀሳቅሷል፡፡ይህን መነሻ በማድረግ በወቅቱ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይል ወደ ሶማሊያ ዘልቆ በመግባት ከፍተኛ ውድቀት እንዲደርስባቸው አድርጓል፡፡ አክራሪዎቹ ከዚያን ጊዜ በኋላ ወታደራዊ ሃይላቸው በመዳከሙ መናሃሪያቸውን ሞቃዲሾና አካባቢውን በማድረግ ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር በደባልነት ሲኖሩና አቅማቸውን ሲገነቡ ቆይተዋል፡፡ ባላቸው አለም አቀፍ የሽብርተኝነት ትስስር ምክንያትም በምስራቅ አፍሪካ በተለይም በኬንያ የተከናወኑትን አስከፊ የሽብር ተግባር ለፈፀሙ የአልቃይዳ ሰዎች መጠለያ ሰጥተው በመንከባከብ ላይ ይገኛሉ፡፡

የሶማሊያው ሁኔታ ይህን የመሰለ አቅጣጫ ይዞ ሲጓዝ ከቆየ በኋላ ባለፉት ጥቂት አመታት የሻእቢያ የአፍሪካ ቀንድ የማተራመስ ስትራተጅ ታክሎበታል፡፡ ሻእቢያ ለአልኢታሃድና ለተወሰኑ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሚሊሺያዎች የመሳሪያና የስልጠና ድጋፍ ከመስጠቱም ባሻገር በምንደኝነት ያሰለፋቸውን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተለይም ኦነግና አብነግን በሶማሊያ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንደልብ መስረግ ይችሉ ዘንድ በሶማሊያ

☞

ውስጥ በሚካሄድ በማንኛውም ግጭት ከአልኢታሃድና ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር አብረው እንዲሰለፉ አዟል። በመሆኑም የአገራችን ሽብር ፈጣሪ ሃይሎች በሞቃዲሾ የሃይሎች አሰላለፍ ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ ይዘዋል።

በሞቃዲሾ ያሉት ሃይሎች በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያመሳስሏቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ከሻእቢያ ምንደኞችና ከአልቃይዳ ሽብርተኞች ውጭ ያሉት ሃይሎች በጠቅላላ የአንድ ጐሳ አባላት ሲሆኑ በዚሁ ጐሳ ስር በተካተቱት በርካታ ንኡስ ጐሳዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከዚያም ባሻገር ሁሉም በተለያዩ ምክንያቶች የሽግግር መንግስቱን ይቃወማሉ። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የእስላማዊ መንግስት መቋቋምን ስለሚፈልጉ በዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሰረተውን የሽግግር መንግስት ይቃወማሉ። አልኢታሃድ ከሶማሊያም አልፎ በአፍሪካ ቀንድ እስላማዊ መንግስት የማቋቋም አጀንዳ ስላለው የሽግግር መንግስቱን ይቃወማል። የጦር አበጋዞቹ ዘርፈው የያዙትን ንብረት ሰላም ከሰፈነ ሊያጡት እንደሚችሉ ስለሚገምቱና የአካባቢውን ወደቦችና አውሮፕላን ማረፊያዎች በመቆጣጠር ከፍተኛ ገቢ ስለሚያገኙና ማእከላዊ መንግስት ቢቋቋም ይኸው የገቢ ምንጭ ሊደርቅ ስለሚችል የሽግግር መንግስቱን መጠናከር ይቃወማሉ። በመሆኑም ምንም እንኳ ሰላም ለማስፈን ሁሉም የታጠቁ ሃይሎች በሽግግር መንግስቱ ውስጥ እንዲካተቱ በተደረገው ጥረት ብዙዎቹ የሞቃዲሾ የጦር አበጋዞች በሽግግር መንግስቱ ውስጥ ቢካተቱም በተግባር ግን ከዚሁ መንግስት አፈንግጠው መንግስቱን ለመናድ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

## ፪. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ድል

የሽግግር መንግስቱ እንደተቋቋመ በሞቃዲሾ ያለው የሃይሎች አሰላለፍ አመች ስላልነበረ ጊዜያዊ ዋና ከተማውን በሞቃዲሾ አቅራቢያ በምትገኘው የጆሃር ከተማ በማድረግ ከሁሉም የሶማሊያ አካባቢዎች ድጋፍ ለማግኘትና ፈራርሶ የነበረውን የሶማሊያ ማእከላዊ መንግስት እንደገና ለመገንባት ጥረት አድርጓል። በዚሁ መሰረት የሞቃዲሾ

☞





ተወላጅ የሆኑ የሽግግር መንግስቱ አባላትን ወደ ከተማው በማስማራት ተስፋ የሚጣልበት እንቅስቃሴ ሲያካሂድ ቆይቷል። አልኢታሃድና አንዳንድ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ለመቋቋም ለዘብተኛ አቋም አላቸው የሚባሉ የሃይማኖት መሪዎችን እስከመግደል የደረሰ ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል። በዚህም ሳይወሰኑ የሽግግር መንግስቱ ወደሞቃዲሾ እንዳይገባ በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ሲሰሩ ቆይተዋል።

በዚህ መሃል የሞቃዲሾና የአካባቢው የጦር አበጋዞች የጋራ ግንባር በመፍጠር እየተጠናከረ የመጣውን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሃይል ለማቋቋም ጥረት ማድረግ ጀመሩ። ፀረ አክራሪነትና ሽብርተኝነት ግንባር ፈጥረናል በማለት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለመዋጋትና በነሱ ከለላ የተሰጣቸውን የአልቃይዳ ሽብርተኞች ለመዋጋት ቆርጠው መነሳታቸውንም አወጁ። የአሜሪካ መንግስት በሶማሊያ ተጠልለው የሚገኙ የአልቃይዳ ሽብርተኞችን ለመያዝ ካለው ፍላጐት በመነሳት የጦር አበጋዞችን በገንዘብ እንደደገፈ ይጠረጠራል። ይህ ክስተት ለጊዜውም ቢሆን ለጦር አበጋዞቹ ግንባር የተጠናከረ መስሎ እንዲታይ ምክንያት በመሆኑ የሽግግር መንግስቱ በሰፈረበት በጆሃር ከተማ የነበረው የጦር አበጋዝ ጭምር ግንባሩን ተቀላቀለ። ከዚህ በኋላ የሽግግር መንግሰቱ ጆሃር ላይ የሰፈረው የራሱ የመከላከል አቅም ይዞ ሳይሆን የጆሃር አካባቢ የጦር አበጋዞች ላይ በመተማመን ስለነበረ ጆሃርን ለቆ ወደ ባይዶዋ ለመግባት ተገደደ። ይህ የጦር አበጋዞች ግንባር ከሽግግር መንግስቱ ያፈነገጡ ነገር ግን በሽግግር መንግስቱ ታቅፈው የነበሩ ሃይሎችን ያካተተ በመሆኑ የሽግግር መንግስቱን አዳከመው። በመሆኑም የሽግግር መንግስቱ የአሜሪካ መንግስት ለጦር አበጋዞቹ ሰጥቷል የተባለውን እርዳታ ከመቃወሙም ባሻገር በሂደት ያፈነገጡትንና በሞቃዲሾ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ላይ ጦርነት ያወጁትን የጦር አበጋዞች ከሽግግር መንግስቱ እስከማባረር ድረስ አመራ።

በመሆኑም የማታ ማታ በሞቃዲሾ የተካሄደው ጦርነት የተወሰነ የአሜሪካ መንግስት ድጋፍን በመጠቀም በአንድ በኩል የጦር አበጋዞች ግንባር ሲሰለፍ በሌላ በኩል ደግሞ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች፣ አልኢታሃድና የአልቃይዳ አጋሮቹ፣ ሻእቢያና ምንደኞቹ የተሰለፉበት

☞

ጦርነት ሆነ፡፡ የሃይል ሚዛኑ ወደ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ እየደፋ ሲሄድ የከተማውም ህዝብ በይበልጥ ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር እየተሰለፈ ሄደ፡፡ የሞቃዲሾ ህዝብ በአንድ በኩል የጦር አበጋዞቹ በፈጠሩት ስርአተ አልበኝነት በመመረርና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ቢያንስ ሰላምና የተወሰነ የማህበራዊ አገልግሎትን ያስገኙልናል ከሚል ፍላጐት በመነሳት ፍርድ ቤቶቹን ሲደግፍ፣ በሌላ በኩል በአሜሪካ ላይ በተፈጠረው ጥላቻ ከአሜሪካ ጋር ወግነዋል በተባሉት የጦር አበጋዞች ላይ ያለውን ተቃውሞ አጠናክሯል፡፡ በመጨረሻም የህዝቡን ድጋፍ ያገኘው ይኸው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሃይል የጦር አበጋዞችን አስወግዶ ከሞላ ጐደል ከተማዋን ለመቆጣጠር በቅቷል፡፡

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹና አጋሮቻቸው በሞቃዲሾ ላይ ያገኙትን ድል በሌሎች የሶማሊያ አካባቢዎችም ለመድገም ፈጣን እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ራሳቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማደራጀት በማሰብ የተበታተኑትን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አንድ ላይ የሚያጣምር ጠንካራ ህብረት ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ ህብረቱ ሲጀመር በተነፃፃሪ ለዘብተኛ ናቸው የሚባሉ ሃይሎችን በአመራር ደረጃ አስቀምጦ የነበረ ቢሆንም ብዙም ሳይቆይ በተሻለ ደረጃ የተደራጁት አልኢታሃድና የአልቃይዳ አጋሮቻቸው አመራሩን ለመቆጣጠር ቻሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በተለያዩ የሶማሊያ አካባቢዎች የዘረጉትን የህቡእ መዋቅር በመጠቀም በየአካባቢው የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ ማድረግም ቀጠሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ የሶማሊያ ጐሳዎችና ንኡስ ጐሳዎች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ከሰላምና ከማህበራዊ አገልግሎት ጋር በማያያዛቸው፣ እንደዚሁም በሞቃዲሾ የበላይነት ያገኙት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአንድ ንኡስ ጐሳ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው የዚሁ ንኡስ ጐሳ የበላይነት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ አማካኝነት እንዳይጫንባቸው በመስጋት የራሳቸውን ፍርድ ቤት ለማቋቋም በማሰባቸው በርካታ ፍርድ ቤቶች በተለያዩ አካባቢዎች ለመቋቋም በቅተዋል፡፡ ይህ በተለይም ከሶማሊላንድ፣ ከፑንትላንድና የሽግግር መንግስቱ ከሰፈረበት ባይዳዋ አካባቢ ውጭ ባሉት ቦታዎች ጐላ ባለ መልኩ ታይቷል፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹና አጋሮቻቸው ድላቸውን ለማስፋፋት የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ

☞





መስሎ የታየበት ሁኔታም ተከሰተ፡፡

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹና አጋሮቻቸው በዚሁ መልኩ እየተጠናከሩ ባሉበት ወቅትም ቢሆን በውስጣቸው ያሉ ዋና ዋና ቅራኔዎች ጐልተው መውጣት ጀምረዋል፡፡ እነዚህ ቅራኔዎች በሁለት ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቅራኔው በብዙዎቹ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችና በአልቃይዳና አልኢታሃድ መካከል ያለ ቅራኔ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሁለቱ ወገኖች በሶማሊያ እስላማዊ መንግስት በማቋቋም ጉዳይ ላይ የሚስማሙ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ፍርድ ቤቶች በአፍሪካ ቀንድና በመላው አለም የጅሃድ ጦርነት ማካሄድን አይደግፉም፡፡ አጀንዳቸው በሶማሊያ ውስጥ የታጠረ ነው፡፡ በመሆኑም እነ አልአታሃድ ከመላው አለም ጋር ያጋጩናል የሚል ስጋት አላቸው፡፡ እነዚህ የጅሃድ ሃይሎች የፍርድ ቤቶች ህብረት አመራርን በመጨበጣቸው ብዙዎቹን በተነፃፃሪ ለዘብተኛ ሊባሉ የሚችሉ ፍርድ ቤቶችን አስኮርፏል፡፡ ይህ በአሁኑ ወቅት በመጀመር ላይ ያለ ቅራኔ ለወደፊቱ እየሰፋ እንደሚሄድ ይገመታል፡፡

ፍርድ ቤቶቹ በየንኡስ ጐሳው ዙሪያ ተመስርተው የጋራ ግንባር የፈጠሩ ሃይሎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በሞቃዲሾ ዙሪያ የተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ሃውያ ተብሎ በሚጠራው የሶማሊያ ጐሳ ዙሪያ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ከሃውያ ጐሳም ውስጥ በእንቅስቃሴው የላቀ ሚና ያላቸው አይር ተብሎ በሚታወቅ ንኡስ ጐሳ ዙሪያ ናቸው፡፡ በሶማሊያ የቆየውና አሁንም ያለው የጐሳና ንኡስ ጐሳ ሽኩቻ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዙሪያም በግልፅ ይታያል፡፡ ሃውያ ያልሆኑት የሶማሌ ጐሳዎች የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሲያቋቁሙ በዋነኛነት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሽፋን የሃውያ ተፅእኖ እንዳያርፍባቸው በመስጋት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በሃውያ ንኡስ ጐሳዎች መካከል ለረጅም ጊዜ በሞቃዲሾና በአካባቢዋ ጦርነት ይካሄድ ስለነበረ ብዙዎቹ የሃውያ ንኡስ ጐሳዎች የአይር ንኡስ ጐሳ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሽፋን የበላይነቱን እንዳይጭንባቸው ስጋት አላቸው፡፡ ይህ ስር የሰደደ የጐሳና ንኡስ ጐሳ ቅራኔ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተጠናክረው በወጡበት በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ጐላ ብሎ መታየት ጀምሯል፡፡

☞

## 3. ሶማሊያና የአለም ህብረተሰብ

በሶማሊያ ሰላምን ለማስፈን የሚደረገው ጥረት የሶማሊያ ጎረቤት አገሮች ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱበት ነው:: በዚሁ መሰረት በኬንያ ሊቀመንበርነት ኢትዮጵያና ጅቡቲ የሚገኙበት ኮሚቴ ተቋቁሞ የሰላም ጥረቱን በአካባቢው አገሮች ስምና በአፍሪካ ህብረት ስም ሲመሩና ሲያንቀሳቅሱ ቆይተዋል:: የቀረው የአለም ህብረተሰብም ይህንኑ ጥረት በተለያዩ ደረጃዎች ሲደግፍ ቆይቷል::

የአካባቢው አገሮች የሰላም ጥረት በሁለት ምእራፍ ተከፍሎ እንዲፈፀም ነበር የታሰበው:: በመጀመሪያው ምእራፍ በሶማሊያ ማእከላዊ መንግስት ተቋቁሞ ነፃነትዋን ካወጀችው ሶማሊላንድ ውጭ ያለውን የሶማሊያ አካባቢ እንዲቆጣጠርና እንዲያረጋጋ ለማድረግ ነበር የታሰበው:: ይህን አላማ ለማሳካት በነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ጎሳዎች በሙሉ በእኩልነት የሚወከሉበትና የየጎሳው ተወካዮች የመረጡት የሽግግር ርላማ እንዲቋቋም ተደርጓል:: ጎሳዎች በሚወከሉበት ወቅት በነሱ ዙሪያ የተደራጁ የጦር አበጋዞችም እንዲወከሉ ተደርጓል:: በሞቃዲሾ ዙሪያ የነበሩት አፈንጋጭ የጦር አበጋዞች በሽግግር መንግስቱ እንዲወከሉ የተደረገውም በዚሁ ምክንያት ነው:: በዚሁ አኳኋን የተቋቋመው ርላማ ለስድስት አመታት የሚቆይ ፌዴራላዊ የሽግግር መንግስት እንዲያቋቁም ተደርጓል::

የሽግግር መንግስቱ ከተቋቋመ በኋላ በየአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን እንዲያሰፍን፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያቀርብ በማድረግና ስርአተ አልበኝነትን በማስወገድ ሶማሊያ የሽብርተኞች መሸሸጊያ የሆነችበት ሁኔታ ከስሩ እንዲቀየር፣ ህዝቡ አማራጭ እያጣ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን እንደ አማራጭ የሚያይበት ሁኔታ እንዲቀየር ማድረግ የስትራተጅው ዋነኛ አካል ነው:: ሁሉም ጎሳዎችና ታጣቂዎች በመንግስቱ ውስጥ እንዲካተቱ መደረጉ ለሰላሙ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ተገምቶ ነበር:: በዚህ ላይ መንግስቱ የውጭ እርዳታ አግኝቶ የራሱን ገቢ መሰብሰብ እስኪጀምር ድረስ በውጭ ገንዘብ መንግስታዊ አገልግሎቶችን





መስጠት እንዲጀምር በሂደትም የራሱ የመከላከያና የፖሊሲ ሃይል እንዲገነባ ታስቦ ነበር:: መንግስቱ የራሱን የመከላከያ አቅም እስኪገነባ ድረስ የውጭ የሰላም አስከባሪ ሃይል ገብቶ መንግስቱን እንዲጠብቅና የሶማሊያን የመከላከያ ሃይል እንዲገነባም ታስቦ ነበር::

በምእራፍ አንድ የሚሰሩ ስራዎች ሲጠናቀቁና እየተጠናቀቁ ባሉበትም ወቅት በሶማሊላንድ አስተዳደርና በሶማሊያ የሽግግር መንግስት መካከል ድርድር ተካሂዶ የሶማሊላንድ ጉዳይ የመጨረሻ እልባት ያገኛል ተብሎ ተገምቷል:: ጉዳዩ በድርድር እንጅ በጉልበት እንደማይፈታም በግልፅ እንዲቀመጥ ተደርጓል::

ይህ የአካባቢው አገሮች የቀየሱት ስትራተጅ በኢጋድና በአፍሪካ ህብረት ሙሉ ድጋፍ ሲያገኝ በአለም ህብረተሰብም ደረጃው የሚለያይ ድጋፍ አግኝቷል:: ወደተግባር በሚገባበት ወቅት ግን ተጨባጭና ፈጣን እርዳታ ሊገኝ አልቻለም:: የልማት እርዳታን በመሰጠት ረገድ ዋናውን ሚና ይጫወታል ተብሎ ተገምቶ የነበረው የአውሮ ህብረት ገንዘቡን በተለያዩ ሰበብ አስባቦች በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ሳይለቅ ቆይቷል:: ሌሎች እርዳታ ሰጭ ሃይሎችም የሽግግር መንግስቱን ሊያጠናክር የሚችል ተጨባጭ እርዳታ በወቅቱ ሳይሰጡ ቆይተዋል:: ይህም የሽግግር መንግስቱ በወቅቱ እንዳይጠናከር አንድ መሰረታዊ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል::

የአፍሪካ ህብረት የሽግግር መንግስቱን ለመጠበቅና የመንግስቱን የመከላከል አቅም ለመገንባት ቢወስንም የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ድርጅት በሶማሊያ ላይ ቀደም ሲል ያስቀመጠውን የጦር መሳሪያ ማእቀብ ባለማንሳቱ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም:: ማእቀቡ ሳይነሳ የጦር መሳሪያ የታጠቁ የሰላም አስከባሪዎች ወደ ሶማሊያ ለመግባትም አይችሉም፣ የሽግግር መንግስቱ አቅምም ሊገነባ አይችልም:: የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ማእቀቡን ለማንሳት ዝግጁ ያልነበረው አባላቱ የየራሳቸው ስጋትና አጀንዳ ስለነበራቸው ነው:: አሜሪካ ከሞቃዲሾ አበጋዞች ጋር በመሆን በሞቃዲሾ ዙሪያ የተጠለሉትን የአልቃይዳ ሽብርተኞችን ማደን እንደዋነኛ አጀንዳ ይዞ ስለነበር የሽግግር መንግስቱን ሰላም አስከባሪዎች በማስገባት ለማጠናከር ትኩረት የሰጠችውና በተሟላ መንገድ የደገፈችው ጉዳይ አልነበረም::

ከዚያም ባሻገር የአልቃይዳ ሽብርተኞችን ከማደን አልፎ በሶማሊያ መረጋጋት ጉዳይ ላይ ጊዜና ገንዘብ ለማውጣት ዝግጁ አልነበረችም። ሌሎቹም ሃያላን መንግስታት በተለያየ ምክንያት ተመሳሳይ አቋም የወሰዱበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው።

ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መጠናከር በኋላ ግን የአሜሪካና አውሮፓ አቋም ተስተካክሎ ከአፍሪካ ህብረትና ከጐረቤት አገሮች አቋም ጋር አንድ አይነት እየሆነ መጥቷል። የመሳሪያ ማእቀቡ ተነስቶ ሰላም አስከባሪ ሃይሎች እንዲገቡና የሽግግር መንግስቱ የመከላከያ አቅሙን እንዲገነባ የማድረጉ ሃሳብ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ ስለሆነ ይኸው ስትራተጅ ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ ይገመታል። በተመሳሳይ መልኩ የሽግግሩ መንግስትና የሽግግር መንግስቱ ቻርተር ከፍተኛ ድጋፍ እያገኙ ስለመጡ የሽግግር መንግስቱ የተሻለ የገንዘብ እርዳታ የሚያገኝበት ሁኔታ በመመቻቸት ላይ ይገኛል።

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች መጠናከር ከላይ የተጠቀሰውን ለውጥ ከማስከተሉ በተጨማሪ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አንድ ወጥ ሃይል ባለመሆናቸው ከለዘብተኞቹ ጋር የሽግግር መንግስቱ ድርድር እንዲያካሂድ የሚለው ሃሳብ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። ለዘብተኞቹ የእስላማዊ መንግስት ማቋቋም አጀንዳቸውን ትተው የሽግግር መንግስቱንና ዴሞክራሲያዊ ቻርተሩን ተቀብለው እንዲደራደሩ ማድረግ የሚል አቋም በአፍሪካ ህብረት ብቻ ሳይሆን በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤትም ተይዟል። በሌላ አነጋገር በጐረቤት አገሮችና የአፍሪካ ህብረት በአንድ በኩል በትላልቅ አገሮችና የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በሌላ በኩል የነበረው የአመለካከት ክፍተት በአሁኑ ወቅት ከሞላ ጐደል ሙሉ በሙሉ የተዘጋበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

## 4. የሶማሊያ ሰላምና የኢትዮጵያ አቋም

ከላይ የተገለፀው በጐረቤት አገሮች ተቀይሶ በአሁኑ ወቅት ከአፍሪካ ህብረት አልፎ መላው የአለም ህብረተሰብ የተቀበለው የሶማሊያ የሰላም ስትራተጅ ኢትዮጵያ ሙሉ

☞





በሙሉ የምትደግፈው ብቻ ሳይሆን በመቀየሱም ላይ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተችበት ስትራተጅ ነው ። ይልቁንም ኢትዮጵያ ይህንን ስትራተጅ የምታራምደው ከራሷ ጥቅም በመነሳት ነው በሚል ዙሪያ ይነዛ የነበረው ፕሮፖጋንዳና ጥርጣሬ በአሁኑ ወቅት ተቀርፎ መላው አለም የተቀበለው ስትራተጅ የሆነበት ደረጃ ላይ መደረሱ ለኢትዮጵያ ታላቅ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ድል ተደርጎ ሊታይ ይገባዋል።

ከላይ የተቀመጠው መሰረታዊ ስትራተጅ እንደተጠበቀ ሆኖ በሶማሊያ ያሉት ዋና ዋና ሃይሎችን በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግስት ዝርዝር ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። ለዘለቄታው በሶማሊያ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚቻለው የሽግግር መንግስቱን በማጠናከር በመሆኑ ኢትዮጵያ ለዚሁ መንግስት ያልተቆጠበ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች። ከሽግግር መንግስቱ ጋር ጠንካራ ወዳጅነት ለመመስረት ችላለች። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ይህንን መንግስት ለመናድ ወደ ባይዶዋ ከተንቀሳቀሱ ይህንን አደጋ ለመቋቋም አስፈላጊውን ወታደራዊ እርምጃ እንደምትወስድም አሳውቃለች። ዋናው መፍትሄ የሽግግር መንግስቱ ራሱን መከላከል የሚችልበት አቅም እንዲገነባ ማድረግ መሆኑን ኢትዮጵያ በጥብቅ ታምናለች። ኢትዮጵያ ሰራዊቷን ወደሶማሊያ አስገብታ የምትከላከልበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነም ታምናለች። ይሁንና የሽግግር መንግስቱ ራሱን የመከላከል አቅሙን ከመገንባቱ በፊት ከተናደ የሶማሊያ የሰላም እድል ስለሚጨልም ይህ እንዲሆን መፈቀድ የለበትም፣ ይህ እንዳይሆንም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወታደራዊ እርምጃ እስከመውሰድ ድረስ መሄድ ተገቢ ነው ብላ ታምናለች። የአለም ህብረተሰብ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንዲኖራት የማይፈልግ ቢሆንም የሽግግር መንግስቱ ራሱን መከላከል ተስኖት እንዲናድም አይፈልግም። ይህ አደጋ የሚከሰት ከሆነም ሊያስቆመው የሚችል ሃይል የኢትዮጵያ ብቻ እንደሆነ ይገነዘባል። የአለም ህብረተሰብም አመለካከት በዚህ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ አቋም ጋር የተቀራረበ ነው ማለት ይቻላል።

ሶማሊላንድን በተመለከተ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን የምትደግፍ ብትሆንም የሶማሊላንድ ነፃነትን ለመቀበል አልፈለገችም። በመጀመሪያ

☞

ደረጃ ባለፉት የኢትዮጵያ መንግስታት ሶማሊያን ለመበታተን ሲሰሩ የነበሩ በመሆናቸው የኢህአዴግ መንግስት ከነሱ በመሰረቱ የተለየ አቋም እንዳለው ለማሳየት ሲባል ቀድሞ የሶማሊላንድን ነፃነት መቀበልም ሆነ ይህንኑ የተቀበለ ብቸኛ አገር ሆኖ መታየት ተገቢ ነው ተብሎ አልታየም። በሁለተኛ ደረጃ የሶማሊላንድ ጉዳይ ከሌሎች የሶማሊያ አካባቢ ህዝቦች ጋር በመግባባት ካልተፈታ በስተቀር በሶማሊያ በአጠቃላይም ሆነ በሶማሊላንድ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም። ስለሆነም በኛ በኩል ጉዳዩ ከላይ በተጠቀሰው ስትራተጅ መሰረት በሰላም ሂደቱ ሁለተኛ ምእራፍ በድርድር ሊፈታ ይገባል የሚል አቋም ተይዟል።

ከላይ የተጠቀሰው ትክክለኛና ሚዛናዊ አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ የሶማሊላንድ ህዝብ የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ገንብቶ ከኢትዮጵያ ጋር በመልካም ጉርብትና ለመኖር ቆርጦ የተነሳ ስለሆነ ይህንን በጐ አላማውን ለማሳካት በሚያደረገው ጥረት ለነፃነቱ እውቅና ከመስጠት በመለስ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አስፈላጊና ተገቢም ነው ተብሎ ታምኖበታል። በመሆኑም ይፋ እውቅና ከመስጠት በመለስ የአገራችን አቅም በፈቀደው መጠን ለመደገፍ የኢኮኖሚ ትብብሮችና ትስስሮችን ለማጠናከር የሚያስችል ስራ ተሰርቷል። አካባቢው የተረጋጋ እንዲሆን ከማድረግም አኳያ ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ግንኙነት የበኩሉን ድርሻ እንዳበረከተ ይታመናል።

ፑንትላንድ በአሁኑ ወቅት ሰፋ ያለ የውስጥ አስተዳደር ይዞ የሚንቀሳቀስ ቢሆንም የሽግግር መንግስቱ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ነው። ስለሆነም ይህ አካባቢ ተረጋግቶ እንዲቀጥል የሚደረግ ድጋፍና የኢኮኖሚ ትስስር ከሽግግር መንግስቱ ጋር የፈጠርነው መልካም ግንኙነት አንድ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ነው። አካባቢው የሰላም ቀጠና ሆኖ ለአክራሪዎችና ሽብርተኞች፣ ለሻእቢያ ምንደኞች መናኸሪያ እንዳይሆን የሚደረገው ድጋፍ በሶማሊያ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሰፍን ከሽግግር መንግስቱ ጋር በመሆን የሚሰራው ስራ አካል ነው ማለት ይቻላል።

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ ሁለት የተሳሰሩ አቅጣጫዎችን መከተል

☞





አስፈላጊ ሆኖ ይታያል። በአንድ በኩል በፍርድ ቤቶቹ ህብረት ውስጥ አክራሪዎቹ የያዙት የበላይነት ለአብዛኛዎቹ የማይበጅ መሆኑን እንዲገነዘቡና በሂደትም አክራሪዎቹ እንዲነጠሉና እንዲዳከሙ ማድረግ። እስከዚያው ድረስ የፍርድ ቤቶቸ ህብረት በአክራሪዎቹ እየተመራ የሽግግር መንግስቱን እንዳይንድ በተረጋጋ ሁኔታ ላይ ያሉትን የሶማሊላንድና የፑንትለንድ አካባቢ እንዳያናጋ መከላከል ያስፈልጋል። የአለም ህብረተሰብ የጅሃድ አራማጆችን በጥብቅ እንደሚቃወም በማያወላዳ መልኩ መግለፁ ከዚሁ አላማችን ጋር አብሮ የሚሄድ ይሆናል። በዚህ ላይ በመመስረት ኢትዮጵያ እነዚህ ሀይሎች በሞቃዲሾና አካባቢው ባገኙት ወታደራዊ ድል ተገፋፍተው የሽግግር መንግስቱን ለመናድ ወይም በፑንትላንድና ሶማሊላንድ ላይ ጥቃት ለመፈፀም ከተንቀሳቀሱ ኢትዮጵያ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ወታደራዊ እርምጃ እንደምትወስድ መግለፅ ዘመቻቸውን ጋብ እንዲያደርጉ ረድቷል። በሶማሊያ ያሉት የሰላም ቀጣናዎች እንዳይናጉ አስተዋፅኦ አድርጓል። የአለም ህብረተሰብ በተቀበለው ስትራተጅ መሰረት የሽግግር መንግስቱ ራሱን ለመከላከል የሚያስችለው አቅም መገንባት ሲጀምርም ኢትዮጵያም የበኩሏን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ ትሆናለች። በሂደትም የኢትዮጵያ ጣልቃ ገብነት አላስፈላጊ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል። በሌላ አነጋገር ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁነታችንን በማረጋገጥ ይህንኑ እርምጃ መውሰድ አላስፈላጊ እንዲሆን ማድረግ የሚለው ስትራተጅያችን ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት እድል ይፈጠራል።

ከላይ የተጠቀሰው አቅጣጫ እንደተጠበቀ ሆኖ አብዛኛዎቹ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችና ደጋፊያቸው የጅሃድ ጦርነት ሃይሎች ስላልሆኑ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያጣላቸው ነገር አይኖርም። ራሳቸውን ከጅሃድ ቡድኖች እንዲያፀዱ መርዳት ከዚህ ጋር ተያይዞም በሽግግሩ መንግስት ቻርተር ዙሪያ ከሽግግር መንግስቱ ጋር ተደራድረው በሰላም ሂደቱ የሚታቀፉበት ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ይሆናል። ኢትዮጵያ እነዚህን ሃይሎች በጠላትነት እንደማታይ፣ ይልቁንም ራሳቸውን ከአክራሪዎቹ ካገለሉ በሰላም አጋርነት እንደምትወስዳቸው ግልፅ ማድረግና በዚሁ ዙሪያ መንቀሳቀስ ተገቢ ሆኖ ይታያል። በመሆኑም መንግስት በአሁኑ ወቅት ሁለቱን አቅጣጫዎች አቀናጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። የጅሃድ ጦረኞች ☞

እንደሚያስወሩት በሶማሊያ ጉዳይ ላይ እስካሁን ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ሳይኖረው ወታደራዊ ዝግጁነቱን በማረጋገጥና ከላይ የተጠቀሰውን ስትራተጅ አቀናጅቶ በመተግበር ለሰላም የላቀ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በሶማሊያ ሰላም ጉዳይ ላይ የምታራምደው አቋም በአንድ በኩል ከሶማሊያ ህዝብ ጋር ባለን የመልካም ጉርብትና ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የራሳችን ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ካላት ፍላጎት ይመነጫል።

በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ቢሰፍን ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ በእጅጉ ተጠቃሚ ይሆናል። ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ ስንል እንዲያው ለማለቱ ያህል የምንለው አይደለም። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የራሳችን ዜጎች ከሶማሊያ ህዝብ ጋር በቋንቋ፣ በባህልና በጐሳ ትስስር በቅርብ የተቆራኙ ናቸው። ጐረቤት ህዝቦች በመሆናችን ሶማሊያ ብትረጋጋ በንግድ ልውውጥ ልናገኝ ከምንችለው ጥቅም ባሻገር እጅግ በርካታ የሶማሊያ ወደቦችን ለመጠቀም ያስችለናል። ብዙዎቹ የሶማሊያ ወደቦች ሞቃዲሾን ጨምሮ ለብዙዎቹ የአገራችን አካባቢዎች ከየትኛውም ሌላ አማራጭ የቀረቡና የተሻሉ ናቸው። ስለሆነም በሶማሊያ ሰላም እንዲሰፍን የምናደርገው ጥረት ከመልካም ጉርብትና ተጠቃሚ ስለሆንና ከወንድሞቻችን የጐረቤት ህዝቦች ጋር ተስማምተን ተግባብተን መኖር እንደምንችልና እንደሚገባንም ስለምናውቅ ነው።

ሶማሊያ ውስጥ ሰላም ከሌለ ጉዳቱ ለኛም ይተርፈናል። ስርአተ አልበኝነቱ አለም አቀፍ የጅሃድ ጦረኞች በሶማሊያ ተጠልለው አካባቢያችን በሽብርተኝነት እንዲያተራምሱ እድል ይሰጣቸዋል። ስርአተ አልበኝነቱ በተግባርም እንደታየው ህዝቡ ጨንቆት ሰላም ያስገኙልን ይሆናል በሚል ተስፋ ብቻ ከባህሉና ከአመለካከቱ ጋር የማይሄዱ አክራሪዎችን እንዲደግፍ ያደርገዋል። የዚህም ጦስ ለኛና ለሌሎች ጐረቤቶችም የሚተርፍ ነው። ስርአተ አልበኝነቱ ሌላው ቀርቶ ሻእቢያም ምንደኞቹን በሶማሊያ በኩል እንዲያሰማራ በር ከፍቶለታል። ይህንን የተወሳሰበ የፀጥታ አደጋ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የሚቻለው በሶማሊያ ስርአተ አልበኝነቱ ተወግዶ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ተመስርቶ ሰላም የሰፈነ እንደሆነ ብቻ ነው። ስለሆነም በሶማሊያ ሰላም እንዲሰፍን በቁርጠኝነት የምንታገለውና





አስፈላጊውንም መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆነው በአንድ በኩል ከሶማሊያ ህዝብ ጋር ካለን አጋርነትና ወንድማማችነት የሚመነጭ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የራሳችን ሰላምና መረጋጋት ከሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ጋር ተቅርብ የተቆራኘ ስለሆነ ነው።

በሶማሊያ በሚካሄደው ፀረ-ሽብርተኝነት ትግልና በዚሁ ዙሪያ በተፈጠረው የሃይሎች አሰላለፍ የኢትዮጵያ ድርሻ ገንቢና ግልፅ ነው። ከሶማሊያ ህዝብ ጋር ካላት አጋርነትና ከራስዋም ሰላም በመነሳት ግልፅና ትክክለኛ የሰላም ስትራተጅ ነድፋ ይህንም ከጐረቤት አገሮችና ከአፍሪካ ህብረት ጋር በመሆን ተግባራዊ ለማድረግ ተንቀሳቅሳለች። በሂደትም በሃያላን መንግስታትና በተባበሩት መንግስትና በአፍሪካና ኢትዮጵያ አቋም መካከል የነበሩ ክፍተቶች እንዲወገዱ ለማድረግ ችላለች። በመሆኑም ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የምታራምደው አቋም የመላው የአለም ህብረተሰብ ድጋፍ ያለው አቋም ነው ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድና ከፑንትላንድ አስተዳደሮችና ህዝቦች ጋር ከሽግግር መንግስቱና ደጋፊዎቹ ጋር ጥብቅ የወዳጅነት ግንኙነት ለመመስረት በመቻልዋም እጅግ ከሚበዛው የሶማሊያ ህዝብ ጋር አብራ ተሰልፋለች ማለት ይቻላል። ብዙዎቹ የሸሪዓ ፍርድ ቤት አባላትና ደጋፊዎችንም ቢሆን በጠላትነት እንደማትመለከት፣ ይልቁንም በሰላም ሂደቱ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ለማበረታታትና ለመደገፍ ዝግጁነቷን በመግለፅ ከጥቂት የጅሃድ ጦረኞች በስተቀር የሁሉም የሶማሊያ ህዝቦች ወዳጅ መሆንዋን አረጋግጣለች።

የጅሃድ ጦረኞች የተቀዳጁቸው ጊዜያዊ ድሎች እንደተጠበቁ ሆነው መላው የአለም ህብረተሰብ፣ የአፍሪካ ህብረትና የተባበሩት መንግስታት ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ የሚበዛው የሶማሊያ ህዝብ ጠላቶች በመሆናቸው ድላቸው ዘላቂ እንደማይሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በውስጣቸው ባለው ቅራኔ መባባስ ሂደት ለዘብተኞቹ የህዝቡን ጐራ እየተቀላቀሉ የጅሃድ ጦረኞቹ ይበልጥ እየተዳከሙ እንደሚሄዱም መገመት ይቻላል። የሶማሊያን ሂደት በጊዜያዊ ክስተቶች ሳናምታታ መሰረታዊ አሰላለፎችን ታሳቢ አድርገን ስናየው በቅድሚያ የሶማሊያን ሰላም ወዳድ ህዝብ በመቀጠልም የወዳጁን

የኢትዮጵያንና የሌሎች የሰላም ሃይሎችን አይቀሬ ድል የሚያበስር፣ የጅሃድ ጦረኞችና የአጋራቸው የሻእቢያ አይቀሬ ሽንፈትን የሚያመላክት ነው ማለት ይቻላል።✐





# ከኢህአዴግ አምባ

# ለመልካም አስተዳደር እመርታ ...

ከኢህአዴግ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ

በቁጥር 2 የአዲስ ራዕይ እትም በዚህ አምድ ላይ «ለጉባኤያችን ስኬት ብቁ ዝግጅት» በሚል ርዕስ በአጠቃላይ ስለ ኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤዎች በተለይም ደግሞ ስለ ስድስተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ግብና ከአባላት ምን እንደሚጠበቅ ለውይይት መነሻ የሚሆን ፅሁፍ እንደቀረበ ይታወሳል። ዛሬም በተመሳሳይ ርእስ ላይ እናተኩራለን።

በኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ በመስከረም ወር ለሚካሄደው ጉባኤ የሚደረገው ዝግጅት ከሞላ ጐደል በሚፈለገው አቅጣጫ በመካሄድ ላይ ሲሆን እነሆ በጉባኤው ዋዜማ ወቅት ላይ እንገኛለን። በዚህ የዋዜማ ወቅት ላይ ትኩረት ከሚደረግባቸው ተግባራት ውስጥ መላ አባላት ጉባኤው በሚመክርባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አስቀድመው መወያየትና ግልጽ አስተሳሰብና አቋም መያዝ፤ ጉባኤው በሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች መሰረት በሁሉም መስክ ውጤታማ እንቅስቃሴ ለማድረግ በብቃት መዘጋጀት የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው።

ለዚህም በዚህ እትም የጉባኤው ዋነኛ አጀንዳዎች እንደሚሆኑ በሚጠበቁት ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ለውይይት መነሻ የሚሆኑ መሰረተ ሃሳቦች እናቀርባለን።

## 1. የልማትና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም ውስጠ- ድርጅት ስራዎቻችን የሚገኙበት ሁኔታ

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በቅርብ ለሚከታተል በሁሉም መስክ በለውጥ ጐዳና ላይ እንደምንገኝ ለመረዳት አዳጋች ☞

አይደለም። በልማቱ፣ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውና የኢህአዴግን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ይዞታ በማጎልበት በኩል ባለፉት አመታት በተለይም ደግሞ በድርጅታችን ውስጥ ከተካሄደው የተሃድሶ ንቅናቄ ወዲህ በመጠን ብቻ ሳይሆን በአይነት የሚገለፁ በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል። ከተሃድሶአችን በኋላ ሁለት ጉባኤዎች የተካሄዱ በመሆኑ የ6ኛው ጉባኤያችን ትኩረት ከ5ኛው ጉባኤ በኋላ ባሉት ሶስት አመታት ውስጥ ባለው ሁኔታ ላይ የሚያርፍ ይሆናል።

ያለፉት ሶስት ዓመታት የኢህአዴግ ስትራቴጂና ታክቲኮች፣ የኢህአዴግ አመራር የአገሪቱን ችግሮች መፍታት የሚችል፤ አገሪቱን ለዘመናት ከተጫናት ድህነትና ኋላቀርነት በማላቀቅ ረገድ ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ ስለመሆኑ በብቃት የተፈተነበት ነበር። በሁሉም መስክ የተሳካ ነበር ማለት ባይቻልም በርግጥም ኢህአዴግ የለውጥ አመራር እንደሆነና በሁሉም መስኮች አበረታች ውጤት እንደተገኘ በተግባር ተረጋግጧል። ከዚህ አኳያ በየዘርፉ ምን ተሰራ? ምን ውጤት ተገኘ? ምንስ ይቀራል? በቀጣይ ምን ሊደረግ ይገባል? የሚሉትን ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ ያስፈልጋል። ይህንን በየዘርፉ ዘርዘር አድርጎ መመልከት ይገባል።

## 1.1. በልማት መስክ እመርታ ማስመዝገብ ተችሏል

የ5ኛ ድርጅታዊ ጉባኤያችንን ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ በተካሄደው ርብርብ ባለፉት ሶሰት አመታት አገራችን በፈጣን ልማት የተጓዘችበትና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እድገትም የተገኘበት ሁኔታ ተረጋግጧል። በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በሶስት አመቱ ውስጥ ጉልህ ለውጦች ታይተዋል። የኢኮኖሚያችን ዋነኛ አውታር በሆነው የግብርናው መስክ የተገኘው ውጤት ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የኢኮኖሚው ዘርፎች ጠንካራ መሰረት ጥሏል። ግብርናችን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አመራረት ገበያን ማእከል ወዳደረገ አመራረት የመሸጋገር ጅምር አሳይቷል። በገበያ በተለይም በአለም ገበያ የሚመራ የግብርና ልማት እንቅስቃሴ በሁሉም አካባቢዎች ተጀምሯል። ከግብርና ገጠር ልማት ጋር በጥብቅ በተቆራኘ አኳኋንና የግብርናና ገጠር ልማቱ የሚፈጥረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀምም የአገራችን ባለሃብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በተለያዩ መስኮች ኢንቨስት ማድረግ ችለዋል። በሁሉም ክልሎች በተለይም ደግሞ በትላልቅ ከተሞች ዙሪያ ሰፊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሚታይበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከግብርናውና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው መጠናከር

☞





ጋር በተያያዘም የውጭ ንግዳችንና የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን በሶስቱ አመታት ውስጥ ከፍተኛ እድገት አሳይቷል።

ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በመሰረተ ልማትና አገልግሎቶች መስክ የታየውም እድገት ከፍተኛ ነው። የትምህርትና የጤና ተቋማት እንዲሁም የአገልግሎቱ ጥራትና ስፋት በእጅጉ አድጓል። የመንገድ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ፣ የመብራት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ... አገልግሎቶችን በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠሮች ለማስፋፋት በተ-ደረገው ጥረት ፈጣን ለውጥ ማምጣት ተችሏል።

በአጠቃላይ ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ቀደም ሲል በነበሩት አመታት ያልታየ፣ ይታያል ተብሎም ተስፋ ያልተጣለበት ኢኮኖሚያዊ እድገት እውን ሆኗል። ለሶስት ተከታታይ አመታት በአማካይ ከ9.5% በላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ተመዝግቦአል። ይህ እድገት ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ነው። የአርሶ-አደሩ በአጠቃላይና በተለይም ደግሞ ሰፊ የሰብል ምርት አምራች የሆኑና በቂ ርጥበት ያለባቸው አካባቢ አርሶ አደሮች ገቢ በብዙ እጅ ጨምሯል። ባለሃብቱ በተለይም ደግሞ ልማታዊ ባለሃብቱ በንግድና በኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት ከተገኘው ኢኮኖሚያዊ እድገት ተጠቃሚ ሆኗል፤ ከኢኮኖሚ አድገቱ ጋር ተያይዞ እየዳበረ በመጣው የአገር ውስጥ ገበያ በሚችለውና በሚያዋጣው ሁሉ በመንቀሳቀስ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን አሳድጓል። የከተማው ነዋሪ ህዝብም ከእድገቱ ተጠቃሚ የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በአገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት የመመዝገቡንና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የመሆኑን ጉዳይ በትንታኔ ሳይሆን በየአካባቢው ያሉ ተጨባጭ መረጃዎችን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል። በየአካባቢው ሊቀርቡ የሚችሉ መረጃዎች ስፋትና ጥራት የሆነውን ያህል ቢሆንም ሊታለፍ የማይችል ሃቅ ይኖራል፤ በሁሉም መስክ፣ በአብዛኛው ቦታ ላይ የሚቆጠር ልማት፣ ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ የተሰራ አዲስ ነገር አለ። የገጠሩም ሆነ የከተማው ህዝብ የመግዛት አቅም በመጠኑም ቢሆን ጨምሯል፤ በፍፁም ድህነት ክልል የሚኖሩ ወገኖች ቁጥር ትርጉም ባለው ደረጃ ቀንሷል። እነዚህ በድምሩ በልማቱ መስክ እመርታ ለማምጣት በ5ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን የተቀመጠው ግብ መሳካቱን ያመላክታሉ።

እመርታው ሊገኝ የቻለው የተከተልነው የልማት ስትራቴጂና ፖሊሲ ትክክለኛ በመሆኑ ነው። ስራ ላይ የዋሉት የልማት ስትራቴጂና ፖሊሲዎች ሁሉም የልማት ሃይሎች /ህዝቡ፣ ባለሃብቱ፣ ምሁሩ፣ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ..ወዘተ/ በልማቱ ላይ

☞

እንደየድርሻቸው በብቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚም እንዲሆኑ የሚያበረታቱ በመሆናቸው ሁሉም ባላቸው አቅም የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተለይም ደግሞ ከአገሪቱ ህዝብ 85% በላይ የሆነው አርሶ አደር ጉልበቱንና መሬቱን በአግባቡ በመጠቀም የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የሚያስችል ውጤታማ አቅጣጫ መከተል መቻላችን፣ የአርሶ አደሩን የልማት ተነሳሽነት ለማጎልበት የሚያስችሉ ድጋፎች የሚያገኝበትን ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት ማድረጋችን፣....ወዘተ. ለተገኘው እድገት አይነተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል፡፡ በከተሞችም የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች እንዲሁም የመካከለኛና ከፍተኛ የምርትና ንግድ ድርጅቶች እንዲስፋፉ በማድረግ በኩል በየጊዜው በመንግስት የተሰጠው ትኩረት በተመዘገበው እድገት ላይ ያለው ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

በልማቱ መስክ እመርታ ተመዝግቦአል ማለት ግን የልማት ግቦቻችን በሙሉ በተሟላ መንገድ ተሳክተዋል፣ ከፍተኛው የእድገት ደረጃ ላይ ደርሰናል፣ በልማት ፖሊሲና እቅዶቻችን አፈፃፀም ሂደትም ሆነ በውጤቱ ላይ ምንም ችግር የለም ማለት አይደለም፡፡ በመሰረቱ እመርታ የቃሉ ትርጉም ዝላይ የሚለውን የሚያመለክት ሲሆን በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ደግሞ ከአንድ ሁኔታ ወይም ደረጃ ወደ አዲስ ሁኔታ፣ ወደተሻለ ደረጃ መሸጋገርን እንጂ የለውጥ መጠናቀቅን አያመላክትም፡፡ በመሆኑ ባለፉት ሶስት አመታት በልማቱ መስክ አበረታች ውጤቶች ቢታዩም ቀላል የማይባሉ ጉድለቶችም እንደነበሩ እንገነዘባለን፡፡

በዚህ ረገድ አንዱ ጉድለት የመጣው የግብርና እድገት በሁሉም አካባቢ የተመጣጠነ አለመሆኑ ነው፡፡ እድገቱ በዋነኛነት ትርፍ አምራች በሆኑትና በቂ ርጠበት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ የተገኘ ሲሆን የምግብ ዋስትና ችግር ባለባቸውና በአርብቶ አደር አካባቢዎች በሚፈለገው መጠን ለውጥ አልመጣም፡፡ በገጠር መሬት አልባ የሆኑና በልማቱ በብቃት ያልተሳተፉ በዚያው መጠንም ከልማቱ በበቂ ደረጃ ተጠቃሚ ያልሆኑ በርካታ ወጣቶች መኖራቸው ደግሞ ሌላው ጉድለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የገጠር ሴቶች በልማቱ በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፉና ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተሰራው ስራና የተገኘው ውጤት አናሳ ሆኖ ይገኛል፡፡ የግብርና ገጠር ልማት ስትራቴጂውን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በተሟላ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ላይ በየደረጃው የሚታዩት የአፈፃፀም ችግሮችም ቀጣይ ጥረትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በሌላም በኩል በከተሞች ያሉትን የልማት ችግሮች በመቅረፍ ረገድ የተሰራው ስራ ውሱን ሆኖ ይገኛል፡፡ ባለፉት ሶስት አመታት በከተሞች የቤቶች ልማትና በአነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች ዙሪያ የተሰራው ስራ በከተሞች የሚታየውን ሰፊ የስራ አጥነትና ☞





የመኖሪያ ቤት ችግርን በማቃለል በኩል ያለው አስተዋጽኦ አነስተኛ ነው፡፡ አሁንም የስራአጥነትና የመኖሪያ ቤት ችግር የከተሞቻችን ቁልፍ ችግሮች ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የከተማው ህዝብ ራሱ የመፍትሄው አካል ሆኖ እንዲንቀሳቀስና የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ በማስቻል በኩል የተሰራው ስራ እጅግ አናሳ ነው፡፡

በመሆኑም በልማቱ መስክ የመጣውን እመርታ በመጠቀም ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ ጥሩ ውጤት የተገኘባቸውን መስኮች በላቀ ትኩረት ማጐልበት፣ ጉድለት በሚታይባቸው መስኮች ደግሞ ፈጣን ለውጥ ለማምጣት መላ አቅማችንን ማረባረብ፣ ሁሉም የልማት ሃይሎች የጀመሩትን የልማት ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ፣ በቀጣይም የማስፈፀም አቅማችንን በላቀ ደረጃ መገንባት..... ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ አኳያ የአምስት አመት (1998-2002 ዓ.ም) የልማት እቅዱን በተሳካ አኳኋን መተግበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ስድስተኛው ጉባኤያችን በነዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ በመመከር ጠቃሚ አቅጣጫዎችን እንደሚቀይስ፣ በሁሉም መስክ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ውሳኔዎችን እንደሚያስተላልፍ ይጠበቃል፡፡

## 1.2. በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ መስክ እመርታ ማስመዝገብ የሚጠበቅብን ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡

ባለፉት አመታት በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መስክ በርካታ ስራዎች ተከናዉነዋል፣ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ዉጤቶችም ተገኝተዋል፡፡ በአገራችን ዴሞክራሲ ስር መሰደድ ይችል ዘንድ በሁሉም ደረጃ የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ፣ የዳበረ የፍትህ ስርዓት እንዲገነባ፣ የህዝቡ ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጐለብት፣ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላት ዘንድ የግልፅነት፣ ተጠያቂነትና ህዝብን አገልጋይነት መርህ እንዲሰፍንና የተግባርም መመሪያ እንዲሆን፣ በሁሉም መስክ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ... ወዘተ ለማድረግ የወጡትን ፖሊሲዎች ስራ ላይ ለማዋል በየአካባቢው አበረታች ጥረቶች ታይተዋል፡፡ ቀደም ሲል ከነበረው አንፃር ሲመዘንም በለውጥ ጐዳና ላይ መሆናችንን የሚያመላክቱ መልካም ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

እነዚህ ጥረቶች ግን ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ ከኖረው ፀረ-ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ☞

ድርጊት፣ በተለያየ መልክ ከሚከሰትና ነባራዊ መሰረቱ ምቹ ከሆነለት የጥገኝነት ፍላጐትና ተግባር ጋር በመታገል የተፈፀሙ በመሆናቸውና ሌሎችም የአፈፃፀም ችግሮች ታክለው የተገኘው ውጤት የሚጠበቀውን መሰረታዊ ለውጥ ያመጣ ነው ማለት አይቻልም። በመሆኑም በ5ኛው ጉባኤያችን በተወሰነው መሰረት በልማቱ የመጣውን አይነት እመርታ በመልካም አስተዳደር መስክ ማስመዝገብ አልተቻለም።

ከዚህ አኳያ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ያሉ የህግ አውጭ፣ ህግ ፈፃሚውና ህግ ተርጓሚ የመንግስት አካላት በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚጠበቅባቸውን ህገመንግሰታዊ ተልእኮ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ አግባብ ማከናወን ይችሉ ዘንድ የተጀመሩትን የማሻሻያ ኘሮግራሞች በተሟላ መንገድ ስራ ላይ ማዋል የማይታለፍ ተግባር ይሆናል። የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች በማያዳግም መንገድ እንዲፈቱ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚደመጡበትና ገዥው ፓርቲ ደግሞ በፖሊሲዎቹ አማካይነት አገሪቱን የመምራት ሚናውን የሚጫወትበት ፓላማዊ ስርዓት እንዲጎለብት...... ማድረግ የላቀ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል። በሌላም በኩል በየደረጃው በፈቃደኝነትና በተደራጀ መንገድ የሚካሄድ የህዝብ እንቅስቃሴ የሚጠናከርበት፤ በመላ አገራችን የሰፈነው ሰላም አስተማማኝ ሆኖ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ይገባል።

ስድስተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ መስክ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት ያልቻልንባቸው መሰረታዊ ችግሮች በመመርመር፤ ከፍ ሲል የተመለከቱትን ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎችና ሌሎችንም መሰረታዊ ጉዳዮች በማካተት በመስኩ እመርታ ለማምጣት በቀጣይ መስራት በሚገባቸው ተግባራት ዙሪያ ብቁ አመራር እንደሚሰጥ ይጠበቃል።

### 1.3. ውስጠ ድርጅት ስራችን እመርታ ማስመዝገብ ጀምሯል፤

በድርጅታችን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም አላማዎች ዙሪያ ምልዓተ ህዝቡን ለማንቀሳቀስና ከጎናችን ለማሰለፍ፤ ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለንን ግንኙት ለማጎልበት፣ ውስጠ ድርጅት የግንባታ ስራዎቻችንን ለማጠናከር እንዲቻል በ5ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ባለፉት ሶስት አመታት በአጠቃላይና በተለይም ደግሞ ባለፈው አንድ አመት ውስጥ በርካታ ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል።

☞





ለውስጠ ድርጅት ስራ የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፤ የድርጅት ጽ/ቤቶች ግልፅ ተልእኮ ይዘው በየደረጃው እንዲደራጁ ተደርጓል። የድርጅታችን የህዝብ ግንኙትና የድርጅት ስራዎቻችን የአፈፃፀም አቅጣጫዎችና መመሪያዎች ላይ ጉልህ ለውጦች ተደርገዋል። በአተር ጊዜ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም አላማዎቻችን ላይ ማወያየትና ሰፋፊ ስልጠናዎችን መስጠት ችለናል። አገራዊ አመራር የምንሰጥ ፓርቲ ከመሆናችን አኳያ ሲመዘን በጣም ጠባብ ሆኖ በቆየው የድርጅታችንን የአባላት ብዛትና ስብጥር ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ችለናል። በአገራችን ውስጥ ክልሎችን በመምራት ላይ ከሚገኙ አጋር ፖለቲካዊ ድርጅቶች ጋር ከመቼውም ጊዜ የተሻለ የመቀራረብና የመደጋገፍ ግንኙት ማዳበር ተችሏል። ባለፉት አመታት ተገቢ ትኩረት ባልሰጠናቸው ከምሁራን፣ ከልማታዊ ባለሃብት፣ በውተ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር የተጀመረው ግንኙትም ከወዲሁ አበረታች ውጤት ይታይበታል። ለመጀመሪያ ጊዜም በውተ አገር ከሚገኙ ተመሳሳይ አላማ ካለን ፓርቲዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል ስራ ጀምረናል።

አጠቃላይም በተሃድሶአችን የመለስናቸውን የውስጠ ድርጅትና የህዝብ ግንኙነት ስራ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ማድረግ ጀምረናል። እነዚህን የተሃድሶ አቅጣጫዎች በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት ተግባራዊ ባለማድረጋችን ምክንያት መፈጠር ጀምረው የነበሩትን የህዝብ ቅሬታዎችና ተያያረ ችግሮችንም መፍታት የምንችልበት ሁኔታ በማረጋገጥ ላይ እንገኛለን። ስለሆነም የውስጠ ድርጅት ስራችን በተለይም ባለፈው አንድ አመት ውስጥ እመርታ ማስመስገብ ጀምሯል ማለት እንችላለን።

ይህ ማለት ግን ጉድለቶች የሉም፤ የነበረብንን መሰረታዊ ችግሮች ሙሉ በሙሉ ተሻግረናቸዋል.... ማለት አይደለም። ከሁሉ በላይ መሻሻል የጀመሩትን የድርጅትና የህዝብ ግንኙነት ስራዎቻችንን በየደረጃው ተቋማዊ መልክ ማስያዝ፣ በዳበረ የአሰራር ስርዓት ማጠናከር ያስፈልጋል። በየደረጃው የአመራር አቅማችንን ማጎልበት፣ ቀጣይነት ያለው የአባላት ግንባታ ማካሄድ ይጠይቀናል።

ስድስተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ውስጠ ድርጅት ሁኔታችንን በዝርዝር በመገምገም የተጀመረውን እመርታ ቀጣይ ለማድረግ፤ በተሃድሶአችን የተቀመጡትን አቅጣጫዎች በላቀ ደረጃ ለመተግበርና የድርጅታችንን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች ካለፉት አመታት በተሻለ ለማሳካት የሚያስችሉ ውሳኔዎችን እንደሚያስተላልፍ

☞

ይጠበቃል፡፡

2. መተዳደሪያ ደንባችንን ማሻሻል፣

ጉባኤው እንደሚወያይበት ከሚጠበቀው አጀንዳ ሌላው በመተዳደሪያ ደንባችን ላይ የሚደረገውን ማሻሻያ ነው፡፡ በኢህአዴግም ሆነ በየብሔራዊ ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ሊደረጉ የማገባቸውን ማሻሻያዎች አስመልክቶ በጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለየጉባኤዎቹ ይቀርባል፡፡

እስካሁን ስራ ላይ ባለው መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሚጠበቁት ማሻሻያዎች ውስጥ የሚከተሉት ትኩረት እንደሚሰጣቸው ይጠበቃል፡፡

2.1 የአባላት ተልእኮ

እስከ ዛሬ ድረስ የነበረው የአባላት ተልእኮ በዋነኛነት የድርጅቱን ፖለቲካዊ መስመር ማወቅ፣ ለመስመሩ ታማኝ መሆንና ለተግባራዊነት በፅናት መታገል.... የመሳሰሉ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ የታጠረ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይሁንናም አሁን ከምንገኝበት ሁኔታ አንፃር የአባላት ተልእኮ የድርጅቱን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም አላማዎች ለመሳካት በሚያገለግል አግባብ መዘጋጀት እንዳለበት ይታመናል፡፡ በመሆኑም ከእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል አኳያ የተቃኘ፣ አጭርና ግልፅ በሆነ መንገድ የተቀረፀ ተልእኮ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ ለምሳሌ ያህል የአርሶአደርና የመምህራን አባላትን ተልእኮ ማየት ይቻላል፡፡

<u>የአርሶአደር አባል ተልእኮ</u>

1. በልማት ጥረትና በፍትሃዊ መንገድ ራሱንና አካባቢውን ማበልፀግ፣
2. ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቡን ማጎልበት፣ በቀበሌው ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲገነባ በግንባር ቀደምነት መሳተፍ፣
3. አዳዲስ የድርጅት አባላትን በጥራት መመልመል፣

☞





<u>የመምህር አባል ተልእኮ</u>

1. ራሱን ብቁ መምህር በማድረግ ከኬርየር ስርዓቱ ተጠቃሚ መሆን፣
2. የሚያስተምርበት ት/ቤት ክህሎትና መልካም ስነምግባር ያለው ዜጋ የሚያንፅ ጥሩ ት/ቤት እንዲሆን በግንባር ቀደምነት መንቀሳቀስ፣
3. በሚኖርበት ቀበሌ በልማትና መልካም አስተዳደር መስክ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን እንቅስቃሴ አቅሙ በፈቀደው መጠን መሳተፍ፣
4. የልማትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጥረትን የሚያደናቅፉ አስተሳሰቦች-ንና ድርጊቶችን መታገል፣
5. አዳዲስ የድርጅት አባላትን በጥራት መመልመል.

2.2 የአደረጃጀት ጉዳዮች

በመሰረቱ የአደረጃጀት ጉዳይ ከሁኔታዎች ጋር እየታየ በየጊዜው የሚሻሻል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን በስራ ላይ ያለው መተዳደሪያ ደንባችን ሊሻሻሉ የሚገባቸው በርከት ያሉ አንቀፆች እንዳሉት ይታመናል፡፡ ከነዚህ ውስጥም የድርጅት ጽ/ቤትና የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም ተግባርና ሃላፊነትን የሚመለከቱት ዋነኛዎቹ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡

የኢህአዴግም ሆነ የየብሄራዊ ድርጅት ጽ/ቤቶች የርቲው የድርጅትና የህዝብ ግንኙት ማእከል ሆኖ በሚሰራበት አኳኋን እንዲደራጅ ከዚህም ጋር የተያያዙ ተግባርና ሃላፊነቶች እንዲኖሩት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልፅ መደንገግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አባላት ተልእኮአቸውን በአግባቡ እንዲወጡና በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ እንዲገነቡ በማድረግ በኩል መሰረታዊ ድርጅት ቁልፍ መዋቅር ሆኖ ይገኛል፡፡ መተዳደሪያ ደንባችን ይህንንም በሚገባ ማንፀባረቅ ይጠበቅበታል፡፡

## ማጠቃለያ

## ከዚህም ከዚያም

# የማይበገር የንባብ---

«ጥሩ አንባቢ ከሆንክ ጥሩ ዜጋ ይወጣሃል» የሚለውን ጥቅስ የት እንዳነበብኩት ትዝ አይለኝም። ነገር ግን ታላቁ የሩሲያ ደራሲ ማክሲም ጎርኪ «የጥሩ ደራሲነቴ ምንጭ የንባቤ ውጤት ነው» ብሎ መፃፉን አስታውሳለሁ። ስማቸው የገነኑ ሳይንቲስቶች፣ ተመራማሪዎች፣ ፈላስፎች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ ደራሲዎች፣ ሰዓሊዎችና ሌሎችም ታላላቅ ስራ ለዓለም ያበረከቱ በሙሉ ጥሩ ተመልካቾች፣ አንባቢዎችና ነገን ለማየት የነበራቸው ጉጉት ውጤት ነው - የዕውቀናቸው ምንጭ።

የንባብ ልምድ በዳበረባቸው አገሮች ዜጎች በሃገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በንቃት ሲሳተፉ ይታያሉ። አዳዲስ ሃሳቦችን የማመንጨት፣ ራስን በትክክል ከመምራት አንስቶ ለሃገርና ለወገን ጠቃሚ ስራ እስከማበርከት የደረሱ በርከት ያሉ ሰዎች ማየት እንችላለን። ለዚህም ጃንን እንምረጥ።

ጃን ወደ ስልጣኔ መንኮራኩር ካሸጋገሯት ሰዎች አንዱ ካትሱ ነው። የጃን ስልጣኔ ፋና ወጊ የሚባሉት ሰዎች አስር ናቸው። ከአስሩ ተርታ ደግሞ አውራ የሚባለው ይሄው ካትሱ ነው። ካትሱ በምን ተዓምር የጃን ስልጣኔ ፋና ወጊ አውራዎቹ ተርታ ውስጥ ተሰለፈ? ከንባብ ልምድ ጋር ምን ያያይዘዋል? ጥቂቱን እነሆ፦

ጃን እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በተመሳሳይ ዘመንና ጊዜ በሯን ዘግታና ከዓለም ጋር ተፋታ ለ250 ዓመታት ኖረች። ይህ ዝግ ፖሊሲ መጨረሻው ሰዓት ላይ መላላት ሲጀምር በርካታ የጃን ወጣቶች የአውሮ ስልጣኔ ያማልላቸው ያዘ። የስልጣኔው ሚስጥርና ታምራቱን መመርመር ፈለጉ። ልባቸው እውቀትን ናፈቀ። ውስጣቸው በቁጭት ተንቀለቀለ። እናም የጃን የዝግ በር ፖሊሲ ሲደረመስ ወጣቶቹ በንባብ ፍቅር ተጠመዱ።

ከነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ ደግሞ ካትሱ ነው። «ካትሱ፣ አያቱ አይነ ስውርና ለማኝ ሰው ነበር» ሲሉ የህይወት ታሪኩን የፃፉ ሰዎች ያትታሉ። ካትሱ የአውሮ ስልጣኔ ጥማቱን

☞





ለማርካት መጀመሪያ የመረጠው መንገድ ቋንቋን ማጥናት ነው። ያኔ ጃን ውስጥ ኑሯቸውን የመሰረቱት ሆላንዶች ብቻ ስለነበሩ የነሱን ቋንቋ ማጥናት እንደ መጀመሪያ ምርጫው ያዘ። ሆኖም ሆላንዶቹ ነጋዴዎች ከመሆናቸው ባሻገር የትምህርት ደረጃቸው ብዙም የሚያኩራራ አልነበረም። ይህም የካትሱን የማወቅ ጥማት ሊቆርጥለት አልቻለም።

አንድ ሌላ መንገድ አሰበ፣ ካትሱ። የሆላንድ ቋንቋ መግሪያ የሚሆነውን መዝገበ ቃላት ማግኘት። መዝገበ ቃላቱን ፈለገ፣ አስፈለገ፣ በየትኛውም የጃን ገበያ ላይ የለም። ሲያስበው መምህሩ ዘንድ አለ። ውሰት ጠየቀ። እናም መዝገበ ቃላቱን በ2 ኮፒ ገለበጠው፤ በእጅ ፅሁፍ። ቀጠለና ከ2ቱ ኮፒ አንዱን የንባብ ጥማት ላቃጠላቸው ጃናዊያን በውድ ዋጋ ሸጠ። በዚህ ገንዘብ ደግሞ ሌላ መፅሃፍ ገዛ። የገዛው መፅሃፍ ስለጦር ዕቅድ የሚናገር ነበር። ምጥጥ አድርጎ አነበበው። ከዓመት በኋላ መፅሃፉን ለአከራዩ ሲመልስ በተመሳሳይ ሃሳብ ላይ የተፃፈ መፅሃፍ አገኘ። ለመግዛት ሲሞክር ዋጋው የበለጠ ውድ ሆነበት። ወዳጅ ዘመድ አስቸግሮ ገንዘብ ሰበሰበና ወደ መፅሃፍ ቤቱ አቀና። ነገር ግን መፅሃፉን ሌላኛው ሰው ገዝቶታል።

«ለመሆኑ ገዥው ማነው?» ሲል ጠየቀው ሻጩን። ነጋዴው መናገር አልፈለገም። ካትሱ ተናደደና «ካልነገርከኝ እገድልሃለሁ» ብሎ ነጋዴውን አስፈራራው። የታጠቀውን ሰይፍ መዝዞ እያሳየው።

«ጌታዬ መፅሃፉን የገዛው ሰው ሃብታም ብቻ ሳይሆን መኮንን (ሳሙራዬ) ነው» አለ ነጋዴው። የሰውዬውን አድራሻ አፈላልጎ ደረሰበትና ቤቱ ከች አለ፤ ካትሱ።

ሰተት ብሎ ገባ።

«ይህን መፅሃፍ በጣም እፈልገዋለሁና ለኔ ሽጥልኝ» ሲል ጠየቀ ካትሱ።

«አልሸጥም!» ሲል መለሰ መኮንኑ።

«እንግዲያውስ አከራየኝ?»

«አላከራይም!»

«እንግዲያውስ አውሰኝ?»

«መፅሃፉ ሁል ጊዜ ስለሚያስፈልገኝ ላውስህ አልችልም!»

የመኮንኑና የካትሱ ፍጥጫ ቀጠለ።

☞

«እንቅልፍ አትተኛም ወይ?» ካትሱ የጥያቄውን መልክ ዞር አደረገው::

«ሌሊትማ እተኛለሁ!» በመገረም መለሰ መኮንኑ::

«እንግዲያውስ... ማታ ማታ ከቤትህ እያመጣሁ አንተ ስትተኛ መፅሃፉን ወስጄ በማለዳ እንድመልስልህ ፍቀድልኝ... መያዣ እንዲሆንህ ይህን ገንዘብ እንካ»

የካትሱ ድርቅና የተሞላበት ልመና መኮንኑን አናደደው:: «መፅሃፌ ከቤቴ እንዲወጣ ጨርሼ አልፈቅድም!»

የመኮንኑ መልስ ካትሱን አስቆጣው:: ሰይፉንም ጨብጦ ነቀነቀው:: ጃፓኖች ክብራቸውን የሚነካ ነገር ሲደርስባቸው ወይም ጠላታቸውን መግደል ወይም በገዛ እጃቸው መሞት (ሃራኬሪ ይባላል መጠሪያው) ልማዳቸው ነው:: የካትሱ ሰይፉን ጨብጦ መነቅነቅ ክብሬ ተነካ ለማለት ነው:: መኮንኑም የካትሱ ድፍረትና መንቻካነት አብግኖታል:: እሱም ክብሬ ተነካ ብሏል:: እናም ተፋጠጡ:: በዚህ የመፋጠጥ ቅፅበት ውስጥ ካትሱ ሌላ መላ መጣለት::

«አንተ ስትተኛ እዚሁ እቤትህ ሆኜ ሌሊት ሌሊት መፅሃፉን እንዳነበው ትፈቅድልኛለህ ወይ?» የሚል ጥያቄም አማራጭም አቀረበ ካትሱ::

ካትሱ በዋዛ እንደማይተወው ገምቷል መኮንኑ:: ስለዚህ «እንደጥያቄህ ይሁን» አለው::

የካትሱ ቤት ርቀት አለው:: ሆኖም ለ6 ወራት ማታ ማታ እየመጣ እያነበበ፤ ጠዋት ጠዋት ወደ ቤቱ እየተመለሰ፣ ባለ 6 ጥራዝ መፅሃፉን አንብቦ ጨረሰ:: ይህም ብቻ ሳይሆን በእጁም ገልብጦታል:: ሃብታሙ መኮንን፣ የካትሱ ጥረትና ትጋት አስደነቀው:: ልክ መፅሃፉን አንብቦ በጨረሰ 6ኛ ወሩ ላይ «መፅሃፉ የሚገባህ ሰው ነህና ትወስደው ዘንድ ፈቅጄልሃለሁ» ብሎ ሰጠው:: ካትሱ የንባብ ጥማቱን እያረካ መሄድ ብቻ ሳይሆን የንባብ ግኝቱን በስራ ተረጎመው:: በመርከብ ስራና በመድፈኛ ጦር ውስጥ የፈጠራቸው አዳዲስ ሃሳቦችና ግኝቶች ጃፓንን ከታላላቆቹ ተርታ አሰለፏት:: አዳዲስ ግኝቶችን ከማፍለቁ ባሻገር የፖለቲካ አማካሪ፣ የስነ መንግስት ፈላስፋ፣ የፖሊሲ ሃሳብ አመንጪና ከሱ በኋላ ለተተኩ ትውልዶች የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ተገኘ:: ካትሱ በጥረቱ ራሱን ያበቃ የአንድ ለማኝ ልጅ ነው:: ነገር ግን ለአገሩ ጃፓን ወርቃማ ልጇ ነው::





# ሽብርና አሸባሪነት

የዛሬ 10 አመት ጆርጂያ ውስጥ የኦሎምፒክ ውድድር እየተካሄደ ነበር:: አሜሪካኖቹ እ.ኤ.አ የ1996ቱን ኦሎምፒክ (ጆርጂያ - አትላንታ ውስጥ የተካሄደውን) በታሪክ ወደር ያልነበረው ትልቁ ኦሎምፒክ ይሉታል:: የአትላንታው ኦሎምፒክ 3.5 ቢሊዮን ሰዎች በቴሌቪዥን እየተካታተሉት ነበር:: 15ሺ አትሌቶች 197 ሀገሮችን ወክለው በዝግጅቱ ላይ ተከፋይ ነበሩ:: የበርከታ አገሮች መሪዎችም ዝግጅቱን ለማድመቅ እዚያው ተገኝተዋል::

ጁላይ 27 1996 አ.ም (በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰው የዘመን አቆጣጠር እ.ኤ.አ ነው) 7 ሰአት ከ20 ደቂቃ አካባቢ በሴንታኔናል (Centennial) ኦሎምፒክ ርክ ያልተጠበቀ ፍንዳታ ተከሰተ:: ከፍንዳታው 5 ደቂቃ አስቀድሞ ለአሜሪካ ፖሊስ በስልክ መረጃ ቢ-ደርሰውም ፍንዳታውን ማቆም አልተቻለም:: ፍንዳታው መላውን አለም ያስደነገጠ ትዕይንት ነበር:: በወቅቱ 2 ሰዎች መሞታቸውንና 112 ሰዎች መቁሰላቸው ተዘግቧል::

ይህንን አስደንጋጭ የሽብር ድርጊት ማን ፈፀመው? ለምን የስፖርቱ መንደር ተመረጠ? ከዚህ የሚገኘው የፖለቲካ ይሁን ሌላ አጀንዳ ትርፍ ምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች በኦሎምፒክ መንደር የታደሙትን ስፖርተኞች፣ አሜሪካውያንና ፖለቲከኞችን ብቻ ያሳሰቡ አልነበረም:: 3.5 ቢሊዮን የሚሆኑ የኦሎምፒክ ሂደቱን በቴሌቪዥን የሚከታተሉ የሌሎች አገሮች ዜጎችንም ጭምር ነው:: በኦሎምፒክ መንደር ከተከሰተው ፍንዳታ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በአትላንታ ውቅያኖስ ላይ የጋየው የTWA 800 አውሮፕላን፣ በዚያው ሰሞን የተፈፀመ የባንክ ዘረፋ ከዚህ ጥቃት ጋር የተያያዘ መሆኑን የአሜሪካ የደህንነት ጉዳይ ሪፖርት ይገልፃል:: የ1996ቱ የሽብር ጥቃት አሜሪካኖችን ስለሽብርና አሸባሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ አድርጓቸዋል:: በርካታ የምዕራቡ አለም መንግስታት ጉዳዩ ነግ በኔ ነው በሚል የደህንነት ሃይሎቻቸውን በፀረ-ሽብር ምንነትና ባህሪያቱ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል::

ሽብርተኝነት ምንድነው? አሸባሪስ የሚባለው ማነው? የመሳሰሉ አንኳር ጥያቄዎች አንድ አይነት መግባቢያ የተደረሰባቸው ምላሽ አላገኙም:: የአሜሪካ የደህንነት ድርጅት

☞

ሽብርን ሲገልፅ «ህገወጥ በሆነ መንገድ አላማን በሀይልና በአመፅ ለማስፈጸም መሞከር» ይላል:: አያይዞም «የዜጎችን ሰላማዊ ህይወት ማወክ፣ በንብረቶቻቸው ላይ ጥቃት መፈፀም፣ ...» የመሳሰሉት ተግባራት ሽብርተኝነት መሆኑን ያስቀምጣል:: በርካታ አገሮች በመጠኑ የተለያዩ ትርጓሜ ለሽብርተኝነት ቢሰጡም በጋራ የሚያመሳስላቸው ነገሮች አሏቸው:: በዜጎች ህይወት፣ ሀብትና ንብረት ላይ፣ በህዝብ መገልገያ ተቋሞች፣ ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ውጪ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚፈፀም ጥቃት በሙሉ የሽብር ተግባር ነው::

የሽብር ተግባር ጎልቶ የወጣው ከ1795 ዓ.ም ወዲህ እንደሆነ በርከታ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ይህም ድህረ የፈረንሳይ አብዮት ተከትለው የመጡ የሽብር ተግባሮች መበርከት ስለሽብርና ሽብርተኝነት ራሱን የቻለ ጥናት እንዲጀመር አድርጓል:: ከ17ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 21ኛ ክፍለ ዘመን የሽብር ጥቃቶች እያደጉ መጥተዋል:: ስለሽብርና አሸባሪነት የሚሰጠው ትርጉምና ብያኔ በዚያው መጠን እየጨመረ ሄዷል:: እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ድረስ ስርአትን በመቃወም አማጺ የሚሆኑ በሙሉ በአሸባሪነት ተፈርጀው ይታዩ ነበር:: አሸባሪነትም ያንድ አገር የውስጥ ጉዳይ እንጂ ድንበር አቋራጭና አለማቀፋዊ ባህሪም አልነበረውም::

የ21ኛው ክፍለ ዘመን አሸባሪነት በብዙ መልኩ ከበፊቶቹ እንደሚለይ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይስማማሉ:: አለም በከፍተኛ ፍጥነት በቴክኖሎጂ እያደገች መሄዷ የአሸባሪነት ጉዞን ፈጣን አድርጎታል:: ካንድ አገር ጉዳይ ይልቅ አለማቀፋዊ መልክ ይዟል::

የኦሎምፒኩን መንደር ጥቃት ተከትሎ የአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስትር አሸባሪነትን በሁለት ዋና ጎራ መድቦታል:: የሀገር ውስጥና አለማቀፍ አሸባሪነት:: የሀገር ውስጥ አሸባሪዎች የሚባሉት በቡድን የተደራጁና ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ ሀገር በቀል አሸባሪዎች የቀኝ ክንፍና የግራ ክንፍ አሸባሪዎች ይባላሉ:: የቀኝ ክንፍ አሸባሪዎች የሚባሉት ለነጭ ዘር የበላይነት እንታገላለን የሚሉት ናቸው:: እነዚህ ቡድኖች የራሳቸውን የሚሊሻ ሃይል ከማቋቋም አንስቶ «የጋራ ፍርድ ቤቶች (Common Law Courts) እስከ መመስረት ደርሰዋል:: እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በሌላ ዘር ላይ ጥላቻን የሚያበቅሉ ተግባራትን እስከመፈፀም የደረሱ ናቸው:: የግራ ክንፍ አሸባሪዎች የሚባሉት ☞





መነሻቸው ካፒታሊዝምን መጥላት ነው:: በዚህ ምክንያት የናጠጡ ብሔራዊ ከበርቴዎችን እያሳደዱ ጥቃት የሚፈፅሙ ናቸው:: በአሜሪካ ደህንነት መስሪያ ቤት ግምገማ መሰረት በአሸባሪነታቸው የከፉት የቀኝ ክንፎቹ ናቸው::

አሜሪካን ራስ ምታት የሆነባት አገር በቀሉ አሸባሪነት አይደለም:: በተለይ የመረጃ ፍሰት በከፍተኛ ፍጥነት በጨመረበት አለም ውስጥ ስር እየሰደዱና እያደጉ የመጡ አሸባሪዎች አገር በቀሎቹ ሳይሆኑ አለማቀፋዊ መልክ የያዙት ናቸው::

አለማቀፍ ሽብርተኝነት አሜሪካን ብቻ ሳይሆን መላው አለምን እያሳሰበ የመጣ ድርጊት ሆኗል:: የአሜሪካ የደህንነት መስሪያ ቤት ከ1968 ጀምሮ የአለም አቀፍ አሸባሪነት ምልክቶች እየታዩ መምጣታቸውን ይገልፃል:: እስከ 1985 አ.ም ድረስ በአለም አቀፍ አሸባሪዎች ጥቃት 816 ሰዎች ሞተዋል:: ምናልባት እስከ መስከረም 11/2001 አንዱ ጥቃት ድረስ አለም አቀፍ አሸባሪነት የማንም ሀገር አሳሳቢ አጀንዳ አልነበረም:: የመስከረም አንዱ የአሸባሪዎች ጥቃት ከ3ሺ በላይ ሰዎችን ህይወት ሲቀጥፍ፣ ያደረሰው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ከ እስከ የሚባል አይደለም:: ከመስከረም አንዱ ጥቃት በኋላ በአሜሪካና ሸሪኮቿ ላይ እየተፈፀመ ያለው የሽብር ተግባር አሳሳቢ እየሆነ ሄዷል:: አለማቀፋዊ ሽብርተኝነቱ እየተጠናከረ በሄደ መጠን የፀረ- ሽብር ትግል እንቅስቃሴም ተጠናክሯል::

አለማቀፍ አሸባሪነትን በአውራነት እየፈፀመ ያለው አልቃይዳ ነው:: የመስከረም 11 የአለም ንግድ ድርጅትና የፔንታጎን ህንፃ ጥቃት፣ በታንዛኒያ ዳሬሰላምና በኬንያ ናይሮቢ የተፈፀሙ የሽብር ተግባሮችን አልቃይዳ እንደመራው አሜሪካ ታምናለች:: የ291 አፍሪካውያን ህይወት ሲቀጥፍ የ5100 ሰዎች አካል ለጉዳት አጋልጧል:: የአሜሪካ የደህንነት መስሪያ ቤት አልቃይዳ እስከ 2003 አ.ም ድረስ 19 የአጥፍቶ መጥፋት የሽብር ተግባር መፈፀሙን አስታውቋል::

የ2004ቱ የማድሪድ ጥቃት፣ በቀጣዩ አመት በለንደን የተፈፀመው፣ የኢንዶኔዥያ የሽብር ተግባርና በቅርብ ጊዜ በህንድ ሙምባይ ባቡር ላይ የተካሄደው ተጠናክረው የቀጠሉ የአልቃይዳ እጅ ያረፈባቸው የሽብር ተግባራት ናቸው::

አሸባሪዎቹ፣ የሽብር ተግባር የሚፈፅሙት፣ ያነገቡትን አጀንዳ የማስፈፀም አላማ ☞

ይዘው ብቻ ሳይሆን የአለምን ትኩረት ለመሳብና፣ በዚህም ምክንያት የሃይል አሰላለፍ ለውጥ እንዲፈጠር ለማድረግ ነው የሚል ሃሳብ ባንድ በኩል ይነሳል:: በሌላ በኩል ደግሞ የለም አሻበሪነትን ስራዬ ብለው የያዙ ሰዎች፣ አለም ባንድ የንድፈ ሃሳብ ሀዲድ ውስጥ እየቀለጠች መሄዷ፣ ያንድ ሀሳብ የበላይነት ያሰፍናል የሚል ስጋት ስላላቸው ነው ይባላል:: ወጣም ወረደ በሰለጠነ ዘመን ውስጥ ሃሳብን በሀይል ለመጫን የሚደረግ የሽብር ተግባር የትኛውም የአለም ህብረተሰብ አልተቀበለውም::

የአሸባሪነት ተግባር እየተጠናከረ መሄዱና በአሸባሪነት የሚሳተፉ ሰዎቸ ቁጥር መጨመር ሌላው አነጋጋሪ የሚያደርገው ነጥብ ነው:: ቀደም ባሉት ዘመናት በአሸባሪ ድርጅቶች የሚመለመሉ ወጣቶች፣ በተለያዩ ምክንያት ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ያጡ ሴቶችና ያልተማሩ ሰዎች ናቸው:: የአለም አቀፍ አሸባሪነት እየተጠናከረ መሄድ በሽብር ተግባር የሚሳተፉ ሰዎች የእድሜ፣ የትምህርትና የሙያ ስብጥር እየተለወጠ መሄዱን ያሳያል:: እነአልቃይዳና አጋሮቹ አሸባሪ ድርጅቶች የሚመለምሏቸው በርካቶቹ የምህንድስና፣ የኮምፒውተር፣ የኤር ክራፍት፣ የባዮሎጂና የሂሳብ እውቀት ያላቸው ምሁራን ናቸው:: አዲሶቹ ምልምሎች የተማሩ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የአሸባሪነት ጎራውን ሲቀላቀሉ ተጨማሪ ስልጠናዎች ይወስዳሉ:: አውሮፕላን ከማብረር ጀምሮ የተለያዩ ኬሚካሎችን ቀምሮ ፈንጂ እስከማድረግ ድረስ:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የመስከረም አንዱ ጥቃትና ሰሞኑን የእንግሊዝ ፖሊሶች የያዙት በፈሳሽ መልክ የተዘጋጀው ተቀጣጣይ ቦንብ ነው::

አሸባሪ ድርጅቶች የት ይሰለጥናሉ? መሳሪያ እንዴት ያገኛሉ? የሚለውን ጥያቄ በርካታ ሰዎች ያነሳሉ:: ለበርካታ አሸባሪ ድርጅቶች አንዳንድ አገሮች ከለላ በመስጠት ሚስጢራዊ የማሰልጠኛ ካምፖች እንደሚገነቡላቸው ይታመናል:: የጦር መሳሪያውንም ቢሆን እነዚህ አገሮች ያቀብላሉ:: እንዲሁም የፖለቲካ ቀውስና የተጠናከረ ማዕከላዊ መንግስት የሌላቸው አገሮች የአሸባሪ ድርጅቶቹ ማዕከላትና ምሽጎች ናቸው:: አፍጋኒስታን በታሊባን ስትመራ በነበረ ጊዜና መንግስት አልባዋ ሶማሊያ ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው:: አለም አቀፍ ማህበረሰብ አሸባሪነትን በፅኑ የሚኮንነው ቢሆንም፣ አሸባሪነትና አሸባሪዎችን





# ምንስ ይሳነናል

ለችግር ለበደል የኛ ፈጥኖ ደራሽ
የጉዟችን መሪ ... የተጎዳን ፈዋሽ
ብልሹን ቀያሪ ... መድህን ፅናታችን
ከኢህአዴግ ጋር ሆነን ... ብሩህ ነው ጉዟችን::
ሰላማችን ሰፍኖ ... ቀና አለ ራሳችን
ዴሞክራሲ አብቦ ... አማረ ቀያችን
የዕድገቱን መሰላል ... ለመውጣት ይዘናል
በኢህአዴግ መሪነት ... ምንስ ይሳነናል
ውሳኔው አሽቶ አዝመራው አማረ
ሁሉም በጉባዔ ለስኬት አበረ
ደመቀ ተስፋችን ተሳካ ግባችን
ይዘልቃል ይርቃል ... ብሩህ ነው ተስፋችን::
ዳር ተመልካች ገባ ... ያቆረው ተናጠ
ደፍርሶ እንዲጠራ ... ህዝቡም ድምፁን ሰጠ::
ዴሞክራሲ ጠልቆ ... ተስፋችን ደመቀ
የልማቱ ስኬት ... እያደረ ላቀ::
ጥፋት መከላከል በራስ መተዳደር
አደራን መፈፀም ለውጤት መጠንከር
ፅኑ ልዩነትን በፀጋ መቀበል
ፈልጎ መወሰን ፈቅዶ መተማመን
ቀድሞ ያላየነው በኢህአዴግ ሆነልን::

☞

ያለፈውን ስህተት በዝርዝር ገምግመን
ድክመት ጥንካሬን በትነን ለይተን
መማር የቻልነውን ከሁሉም ተምረን
ለሌላ እመርታ ቃል እንገባለን
በጉባዔ መክረን … ነገን እንዘልቃለን!!

ከድላይ